# በኢትዮጵያ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ እና የኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓቶች

# አገር አቀፍ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነቶች ምዝገባ አፈጻጸም መመሪያ

(ረቂቅ)

ቫይታል ስታቲ. ጥ.ም. መምሪያ
ሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት
አዲስ አበባ
ህዳር 1997

# በኢትዮጵያ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ እና የኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓቶች

# አገር አቀፍ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነቶች ምዝገባ አፈጻጸም መመሪያ

*(ረቂቅ)*

ቫይታል ስታቲ. ጥ.ም. መምሪያ
ሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት
አዲስ አበባ
ህዳር 1997

# ማ ው ጫ

## ምዕራፍ አንድ

1. አጠቃላይ ---------------------------------------------------------------- 1

1.1 መግቢያ ---------------------------------------------------------------- 1

1.2 የዋና ዋና ፅንሰ ሓሳቦች ፍቺና ማብራሪያ ------------------------------ 6

## ምዕራፍ ሁለት

2. ስለ ሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ------------------------ 14

2.1 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ዓላማዎች ---------------------------------- 14

2.2 በሕዝብ የክብር መዝገብ የሚመዘገቡ ኩነቶች ዓይነት ---------------- 14

2.3 ወሳኝ ኩነቶች የሚያስገኙት ጥቅም ---------------------------------- 15

2.4 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሕግ ---------------------------------------- 23

2.5 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ
የአፈጻጸም አደረጃጀት ------------------------------------------------ 25

2.6 የወሳኝ ኩነቶች አመዘጋገብ ስልቶች ------------------------------- 25

2.7 የወሳኝ ኩነት መዝገቦች ዓይነትና አቀማመጥ ------------------------ 28

2.8 በወሳኝ ኩነት መዝገቦች የሚሰበሰቡ መረጃዎች
ዓይነትና አመዘጋገብ ---------------------------------------------- 28

2.9 የወሳኝ ኩነት መዝገባ አፈጻጸም ------------------------------------ 31

2.10 የወሳኝ ኩነቶች መዝጋቢ ተግባርና ሃላፊነት ------------------------ 32

2.11 የወሳኝ ኩነት መዝገቦች እርማት አደራረግ ------------------------ 35

2.12 የወሳኝ ኩነት መዝገቦች አያያዝና አቀማመጥ ---------------------- 36

## ምዕራፍ ሶስት

3. የወሳኝ ኩነቶች መረጃ አመዘጋገብ ---------------------------------------- 38
3.1 የልደት ወሳኝ ኩነት መረጃ አመዘጋገብ ---------------------------- 38
3.2 የሞት ወሳኝ ኩነት መረጃ አመዘጋገብ ------------------------------ 55
3.3 የጋብቻ ወሳኝ ኩነት መረጃ አመዘጋገብ ---------------------------- 66
3.4 የፍቺ ወሳኝ ኩነት መረጃ አመዘጋገብ ------------------------------- 78

## ምዕራፍ አራት

4. ስለ ወሳኝ ኩነቶች የምስክር ወረቀቶች አዘገጃጀት ----------------- -------- 91
4.1 የወሳኝ ኩነቶች የምስክር ወረቀት ዓይነቶችና
የሚሰጡት ጥቅም ---------------------------------------- -------- 91
4.2 ለኩነቶች ምስክር ወረቀቶች የሚካተቱ መረጃዎች ዓይነት ---- -------- 93
4.3 የኩነቶች ምስክር ወረቀቶች አዘገጃጀት--------------------- -------- 94
4.4 የኩነቶች ወረቀቶች ለባለጉዳዮች የሚሰጡበት ሥርዓት------- -------- 95
4.5 የኩነቶች የምስክር ወረቀቶች እርማት አደራረግ--------------- -------- 95
4.6 የኩነቶች የምስክር ወረቀቶች አያያዝና አቀማመጥ---------- -------- 96

ዕዝል 1 - ዋና ዋና ብሄረሰቦች ስምና ኮድ ዝርዝር ------------------ -------- 97
ዕዝል 2 - የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ
ስታቲስቲክስ መዝገብ ቅጾች ----------------------------- -------- 98
ዕዝል 3 - የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ምስክር ወረቀቶች ---------- ------- 102

# ምዕራፍ አንድ

# አጠቃላይ

## 1.1 መግቢያ

የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ - በአንድ አገር ዜጎች ላይ ከልደት እስከ ዕልፈተ-ሕይወት የሚከሰቱ ወሳኝ ኩነቶችን (ክስተቶችን) እና ኩነቱ የሚመለከታቸውን ሰዎች የሥነ-ሕዝብና ማህበራዊ ባህርያትን፤ የግለሰቦችን ህጋዊ ማንነት በሚያስረዳ አሰራር በቀጣይነትና በቋሚነት በሕግ ድጋፍ የመመዝገብ፣ የማከማቸትና በዋነኝነት ለሕግና ለአስተዳደር አፈፃፀም ግለሰባዊ ወይም ጥቅል መረጃዎችን የማመንጨት እንዲሁም የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃዎችን የማጠናቀርና የማቅረብ፣ እነዚህንም ተግባራት በአገር አቀፍና በተዋረድ የአስተዳደር ዕርከኖች የሚያስፈጽመውን/ሙትን ተቋም/ማት በሕግ፣ በአስተዳደርና በድርጅታዊ አወቃቀር የማደራጀት ተግባራትን የሚያጠቃልል የመንግሥት ሥራ ነው፡፡

የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ አሠራር መሠረታዊ መነሻ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ነው፡፡ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የአንድን ግለሰብ ማንነት የሚገልጹ ሕጋዊና ግለሰባዊ ማስረጃዎችን በማስገኘት ዓላማ ላይ የተመሠረተ፣ ግለሰቦች ከልደት እስከ ሞት ድረስ በግላቸውና በማህበረሰብ አባልነታቸው የሚደርስባቸውን /የሚፈጽሟቸውን ኩነቶች (ልደት፣ ሞት፣ ጋብቻና ፍቺ) እና ከነዚህ ኩነቶች ጋር ተዛማጅ የሆኑ የሥነ-ሕዝብ፣ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ባህርያት መረጃዎችን ለምዝገባው ተግባር ሲባል በወጣው አስገዳጅ የምዝገባ ሕግና ደንብ መሠረት በተከታታይነትና በቋሚነት የመመዝገብ፣ ለግለሰቦች የኩነቶች ምስክር ወረቀት የመስጠትና መረጃውን የመጠበቅ እንዲሁም ለወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ መረጃ አሰባሰብ መረጃ ጥንቅር ግብዓት የሚሆኑ ግለሰባዊ መረጃዎችን የመሰብሰብ ተግባራትን የሚያጠቃልል የመረጃ አሰባሰብ ዘርፍ ነው፡፡ ይህም በወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ተግባር ላይ በመመሥረት ለህጋዊ፣ ለአስተዳደራዊና ለስታቲስቲካዊ የመረጃ ግብዓት አስፈላጊ ግለሰባዊ መረጃዎችን የማመንጨትና ለዚህም አስፈላጊውን አስተዳደራዊና ድርጅታዊ አወቃቀር የመዘርጋቱ ሥራ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት (Civil Registration System) በመባል ይታወቃል፡፡

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አስፈላጊነት መሠረታዊና ታሪካዊ መነሻ ግለሰቦች በዜግነታቸው በአገራቸው ኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ሙሉ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችላቸውን አልፎም በተለያዩ ጊዜያት በአገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ደረጃ የተደነገጉትን የሰብዓዊ፣ የማህበራዊና ፖለቲካዊ መብቶች ተፈፃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሕጋዊና ግለሰባዊ መረጃዎችን ለግለሰቦችና ለመንግስት ማስገኘት ነው፡፡ በሕዝብ የክብር መዝገብ ወሳኝ

ኩነቶችን የመመዝገብ ተግባር በዓለም ታሪክ ረጅም ዕድሜን ያስቆጠረ ቢሆንም የኩነት መረጃዎችን በህጋዊ የአመዘጋገብ አሠራር የመንግሥት ሕግ አካል ሆኖ ዕውን የሆነው በፈረንሳይ አገር በናፖሊዮን ሕግ (እ.ኤ.አ በ1804) የኩነቶች መከሰትን በይፋዊ/ህጋዊ ሰነድ (Official Record) የመያዙ ተግባር በሥርዓት ከተቀረፀበት ጊዜ አንስቶ ነው፡፡ በወቅቱ በፈረንሣይ ናፖሊዮን ሕግ በሲቪል ሕግ ውስጥ እንዲካተት የተደረገው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሕግ (Civil Registration Law) በበርካታ የምዕራብ አውሮፓ፣ የላቲን አሜሪካ፣ የመካከለኛው ምስራቅና የአፍሪካ ሀገሮች ተገልብጦ በሲቪል (ፍትሐ-ብሔር) ህጋቸው ተካቶ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የምዝገባ ሥርዓቱ አሠራር በየጊዜው ካሳየው ዕድገት በመነሳትም የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ህግ ራሱን የቻለ ሕግ ሆኖ በበርካታ ሀገሮች እንዲቀረጽና የምዝገባ አሠራሩም በህጉ ላይ ተመሥርቶ እንዲከናወን፣ ይህንንም የምዝገባ ተግባር የሚያስፈጽም ራሱን የቻለ መንግስታዊ ተቋም እንዲፈጠር የማድረጉ አሠራር በበርካታ ሀገሮች ሲተገበር ቆይቷል፡፡

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ይኸንኑ ታሪካዊ ሂደት መሠረት በማድረግ ወሳኝ ኩነቶች በተለይም ለመሠረታዊ ሰብአዊ መብቶች መከበር ካላቸው የጎላ ሚና አንጻርና ለአንድ ሀገር መንግሥት አግባባዊና ዘመናዊ የሕዝብ አስተዳደር፣ የሕግ ሥርዓት አቀራረጽና አፈጻጸም እንዲሁም የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ መረጃ አቅርቦት መሠረት ሊሆኑ እንደሚገባ በተለያዩ ጊዜያት ባወጣቸው ድንጋጌዎች፣ ስምምነቶችና ቴክኒካዊ መመሪያዎች ላይ በግልጽ አስቀምጦት ይገኛል፡፡ በተለያዩ አገሮች ለሥርዓቱም መቋቋም የቴክኒክና የፋይናንስ እገዛዎች ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

በኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገታቸው በከፍተኛ ደረጃ ላይ በደረሱ አገሮች የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት ዓለም አቀፍ የአመዘጋገብ የአሠራር መርሆዎችን ተከትሎ በተሟላ ሁኔታ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ በነዚህ በኢኮኖሚ በበለፀጉ አገሮች ከሥርዓቱ የሚገኙ መረጃዎች ለህግ፣ ለአስተዳደርና ለስታቲስቲክስ ብቸኛ የመረጃ ምንጭ በመሆን እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡ በአንፃሩ በሦስተኛው ዓለም አገሮች የምዝገባ ሥርዓቱን ለማቋቋም ሙከራዎች ቢኖሩም ከጥቂት አገሮች በስተቀር በአብዛኞቹ ምዝገባው በሚፈለገው ደረጃ ላይ አልደረሰም፡፡ በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ ሥርዓቱ ጭራሽ ካልተዘረጋባቸው እንዲያውም በአገር አቀፍ ደረጃ የምዝገባውን "አግባባዊ" አሠራር በመዘርጋቱ ረገድ ሙከራ ካላደረጉ ጥቂት የአፍሪካ አገሮች አንዷ ናት፡፡

የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አሠራርን በአንድ ሀገር ለመዘርጋት ዋነኛው መሠረት የምዝገባውን ህግ መቅረጽና መተግበር እንደሆነ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት በዘርፉ በተዘጋጁ መመሪያዎች ተገልጾ ይገኛል፡፡ በዚህ ረገድ በርካታ የአፍሪካ አገሮች የምዝገባ ህግ በማዘጋጀትና በመተግበር ረጅም ዕድሜ ያስቆጠሩ ቢሆኑም የምዝገባ ሥርዓቱ አግባባዊውን አሠራር ተከትሎ በተሟላ መልኩ ሊቋቋም አልቻለም፡፡ ይህም ሆኖ የምዝገባ ህግ በማውጣትና በመተግበር ረገድም እስከአሁን ዕውን ካልሆነባቸው ጥቂት የአፍሪካ ሀገሮች

ኢትዮጵያ አንዷ ናት፡፡ በኢትዮጵያ ምንም እንኳ በ1952 ዓ.ም. በወጣው የፍትሐ-ብሔር ሕግ ውስጥ ስለ ሕዝብ የክብር መዝገቦች በሚል ርዕስ ሥር የምዝገባ ሥርዓት አደረጃጀትና አፈጻጸም የሚጠቅሱ አንቀጾች (የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ አደረጃጀትን አያካትቱም) ቢካተቱም የምዝገባ አፈፃፀሙን የያዙት አንቀጾች ላለፉት 40 ዓመታት ተግባራዊ ሳይሆኑ ቆይተዋል፡፡ በመሆኑም ስለሰዎች ሕጋዊ ማንነትና ስለወሳኝ ኩነቶች መከሰት ጉዳይ የፍትህ አካላት በልማዳዊ አሰራር በቃል አስረጂ ወይም ለአስተዳደራዊ ሥራ በተዘጋጁ የመረጃ አቅርቦት አሠራሮች ሲሠሩ ቆይተዋል፣ በአሁኑም ዘመን በዚሁ መልክ እየተሠራበት ይገኛል፡፡ በሌላ በኩል አስተዳደራዊ ጉዳዮችን ለማስፈፀም ከመነጨ ፍላጎት በግለሰቦች ፈቃድ ላይ የተመሠረቱ የልደትና የጋብቻ የምስክር ወረቀቶችን የማዘጋጀትና የመስጠት የአስተዳደር ተግባር በአንዳንድ ትላልቅ ከተሞች (አዲስ አበባ፣ ድሬደዋ፣ ...ወዘተ) በሚገኙ ማዘጋጃ ቤቶች ለበርካታ ዓመታት ሲካሄድ ቆይቶአል፡፡ በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ከ1930ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ በዚህ መልክ የምስክር ወረቀት የመስጠት አሰራር እየተካሄደ ይገኛል፡፡

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት በአገሪቱ እንዲቋቋም በተለያዩ ጊዜያት እና በተለያዩ አካላት (የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚ/ር፣ የከተማ ልማት ሚ/ር፣... ወዘተ) የተናጠል ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ በተመሳሳይም የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ከረጅም ዓመታት ጀምሮ በተለይም በሀገሪቱ የወሳኝ ኩነቶች (የቫይታል) ስታቲስቲክስ መረጃዎችን ለመሰብሰብና ለማጠናቀር ከነበረው ፍላጎት አንፃር በአገሪቱ የወሳኝ ኩነቶች የምዝገባ አሠራር እንዲፈጠር ስታቲስቲካዊ የሙከራ ጥናቶችን ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ምንም እንኳ እነዚህ ናሙና የሙከራ ጥናቶች ወደፊት በአገር አቀፍ ደረጃ የሚቋቋመውን የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓትን በሕግ፣ በቴክኒክ፣ በአስተዳደርና በበጀት በኩል ሊገጥሙ የሚችሉ ችግሮችን ለማጥናት በሃሣብ ደረጃ ታቅደው የተጀመሩ ቢሆንም የተከሉት የአጠናን ስልት ግን በጥራታቸው የተሻሉ የወሳኝ ኩነት ስታቲስቲክስ ምጣኔዎችን ለማስገኘት የተዘጋጁ የሙከራ የናሙና አጠናን ዘዴዎችን ከመተግበር ያለፉ አልነበሩም፡፡ በመሆኑም ከነዚህ የስታቲስቲክስ መረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች በተገኙ መረጃዎች ላይ በመመሥረት የቫይታል ስታቲስቲክስ መረጃን የማጠናቀርና መተንተን ሥራዎች ተካሂዶ የተለያዩ ስታቲስቲካዊ ሪፖርቶችን ከማዘጋጀት ባሻገር ከአግባባዊው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ተግባርና ሥርዓት ጋር የተያያዙ የአደረጃጀትና የአመዘጋገብ ቴክኒካዊ ሰነዶችን ለማዘጋጀትና ልምዶችን ለማስገኘት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም በሙከራ ጥናቶቹ፡-

1/ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሕግ ዝግጅትና የአፈፃፀም ሥርዓትን ለመፈተሽ ያለመቻሉ፣

2/ በአገር አቀፍና በየአስተዳደር እርከኑ ከአገሪቱ የተለያዩ የአስተዳደር አደረጃጀት ህጎች ጋር የተገናዘበና የምዝገባውን ሥራ የሚያስፈጽም የአስተዳደር መዋቅር የመዘርጋት እንዲሁም የምዝገባውን አፈፃፀም ለመፈተሽ የሚያስችሉ ተግባራትን ያለማካተቱ፣

3/ በአግባባዊ ምዝገባ አሠራር ላይ በመመሥረት ከተመዘገቡ ግለሰባዊ ወሳኝ ኩነቶች ላይ የወሳኝ ኩነት ስታቲስቲክስ መረጃዎች አጠንቃቀርና ሪፖርት ዝግጅትን ለመፈተሽ ያለመቻሉ፣

4/ ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የተገኙ ግለሰባዊና ህጋዊ የኩነት መረጃዎች ለህብረተሰቡ የሚሰጡትን ጥቅም በተግባር ለመፈተሽና ለህብረተሰቡ ማስተማሪያ የሚሆኑ ልዩ ልዩ ቴክኒካዊ ጽሑፎችን ለማዘጋጀት የሚያስችል ሙከራ (በተለይም የመስክ) ማድረግ ያለመቻሉ፣ ተጠቃሽ ዋነኛ ድክመቶች ናቸው።

ከላይ ከተጠቀሱት ድክመቶች በመነሳት የሙከራ ጥናቶቹ አግባባዊ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ (Conventional Civil Registration) አሠራርን በአገሪቱ ለመዘርጋት የሚፈለገውን የንድፈ-ሃሳብና የልምድ ዕውቀት በሚጠበቀው መጠን እንዳላስገኙ ለመረዳት ይቻላል።

በአሁኑ ወቅት መንግሥት የሕዝቡን ኑሮ ለማሻሻል ለሚያደርገው ሕገ-መንግሥታዊ አደረጃጀት፣ ለፖለቲካ ሥርዓቱ ዝግጅት እንዲሁም በአገር አቀፍ ወይም በክልል አስተዳደር ደረጃ ለሚደረጉ ምርጫዎች አፈጻጸም እና አስተማማኝ የስነ-ሕዝብ ስታቲስቲክስ መረጃ አቅርቦት ፍላጎትን ከማሟላት አንጻር ሁለት ዋና ዋና ዓላማዎችን የሚያስፈጽም በህገ-መንግሥቱ አንቀጽ 103 እና አንቀጽ 55 (1) መሠረት የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 180/1991 በማቋቋም ሥራውን እንዲያከናውን ተደርጓል። ከኮሚሽኑ ዓላማዎች አንዱ "የሕዝብ እና የቤቶች ምዝገባ በመላ ሀገሪቱ እንዲቋቋምና እንዲሠራበት መሠረታዊ ጥናቶችን በማካሄድ የሚደራጁበትን መንገድ መቀየስ" እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 4(2) ተመልክቷል። ይኸንንም ዓላማ የማስፈፀም አንዱና መሠረታዊው ተግባር የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓቶችን በመላ ሀገሪቱ የሚዘረጉበትን መንገድ ማጥናትና እንዲዘረጉ ማድረግ ነው፡፡

የወሳኝ ኩነት (ቫይታል) ስታቲስቲክስ መረጃ ዘላቂውና አግባባዊው ምንጭ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት ነው፡፡ ይኸ የመረጃ አሰባሰብ ሥርዓት በአገራችን ገና ያልተቋቋመና የኩነቶች ምዝገባ ያልተጀመረ በመሆኑ ምክንያት የቫይታል ስታቲስቲክስ መረጃዎች በዋነኛነት ከሕዝብና ቤት ቆጠራ እና ከሥነ-ሕዝብ ናሙና ጥናቶች እንዲገኙ እየተደረገ ይገኛል፡፡ እንደሚታወቀው እነዚህ የቆጠራና የናሙና ጥናት የስታቲስቲክስ መረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች የቫይታል ስታቲስቲክስ መረጃዎችን በጊዜያዊ መንገድ ለአንድ ወቅት መረጃ ከማስገኘት ባሻገር በተለይም በአካባቢ አስተዳደር እርከን ደረጃ ለሚፈለጉ የአስተዳደር ዕቅዶች ዝግጅት፣ ለጤና እና ለሌሎች የማህበራዊ አገልግሎቶች ግብዓት የሚሆኑ ወቅታዊ፣ ቀጣይና ቋሚ እንዲሁም አስተማማኝ የወሳኝ ኩነቶች (ቫይታል) ስታቲስቲክስ መረጃዎችን የማስገኛ ምንጭ በመሆን ሊያገለግሉ አይችሉም፡፡

በመሆኑም የአገሪቱ የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ መረጃ አቅርቦት አሠራር ወደ አግባባዊው (Conventional) እና ዘላቂው የመረጃ አሰባሰብ ሥርዓት ማለትም የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት በሂደት እየተተካ መሄድ ይኖርበታል፡፡ በዚህ ረገድ ይህ አገር አቀፍ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነቶች አመዘጋገብ መመሪያ በአገሪቱ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ አሠራርን ለመመስርትና ለማሳደግ ከተዘጋጁ ልዩ ልዩ ሰነዶች አንዱና ዋነኛው ነው። መመሪያው በተለይ በክልል መስተዳድራት የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓቶችን ለማቋቋም በሚደረገው ጥረት በየአስተዳደር ዕርከኑ በምዝገባ ሥራው ላይ ለሚሳተፉ ልዩ ልዩ አካላት ከመረጃ አሞላል መመሪያነት ባለፈ ስለምዝገባው አግባባዊ አሠራር ግንዛቤ በማስጨበጥ እንዲረዳ በማሰብ ሰፋ ተደርጎ የተዘጋጀ ሰነድ ነው። በዚህ ረገድ በተለይም በዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን ወሳኝ ኩነቶችን በመመዝገብ ትልቁን ሀላፊነት የሚወስዱት የአካባቢ የወሳኝ ኩነት መዝጋቢዎችና የአካባቢ አስተዳደሮች የምዝገባ አሰራሩን መርህና ጽንሰ-ሀሳቡን በሚገባ ተረድተው ምዝገባውን በአግባቡ ለማከናወን በሚያደርገት እንቅስቃሴ መመሪያው ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል የሚል እምነት አለ። ይህ መመሪያ የተዘጋጀው በአገሪቱ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ህግ ከመውጣቱ አስቀድሞ በመሆኑ የምዝገባ ህጉ ሲወጣ ከህጉ ጋር በመገናዘብ እንደገና መታየትና መሻሻል እንደሚኖርበት ይታመናል።

## 1.2 የዋና ዋና ጽንሰ ሐሳቦች ፍቺና ማብራሪያ

### 1.2.1 ወሳኝ ኩነት

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አሠራርን አስመልክቶ በወጡ ልዩ ልዩ ቴክኒካዊ ጽሑፎችና መመሪያዎች እንደተገለጸው ወሳኝ ኩነቶች ተብለው የሚታወቁት በህይወት መወለድ (Live Birth)፣ የሽል ሞት (Foetal Death)፣ ሞት (Death)፣ ጋብቻ (Marriage)፣ ፍቺ (Divorce)፣ የጋብቻን መከናወን መሰረዝ (ጋብቻ እንዳልተከናወነ መቁጠር) (Annulment of Marriage)፣ ባልና ሚስትን ለጊዜው በህግ መለያየት (Legal Separation)፣ ጉዲፈቻ (Adoption)፣ በህጋዊ ጋብቻ ውስጥ ያልተወለደ ልጅን አባትነትን ወይም እናትነትን መቀበል (Recognition) ናቸው፡፡ ወሳኝ ኩነት የተባሉበትም ዋናው ምክንያት በየአገሮች ሕገ-መንግሥትና በዓለም አቀፍ ድንጋጌዎች የታወቁ የሰብዓዊ፣ የማህበራዊና ፖለቲካዊ መብቶችን ተፈጻሚ ለማድረግና ለመጠበቅ ወሳኝ የሆኑ ህጋዊ የግለሰብ ማንነት መረጃዎች ምንጭ በመሆናቸውና የአንድን አገር ሕዝብ ብዛትና ዕድገትን ስለሚወስኑ፤ ለሕብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ አገልግሎት አሰጣጥ ለሚዘጋጁ ዕቅዶች ዝግጅትና አፈጻጸም በአካባቢያዊ አስተዳደር አልፎም በግለሰቦች ደረጃ ተፈላጊና ወሳኝ መረጃዎች በመሆናቸው ነው፡፡ በዚህ መመሪያ መሠረት በኢትዮጵያ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓትን ለማቋቋም ቅድሚያ የተሰጣቸው ወሳኝ ኩነቶች በህይወት መወለድ፣ ሞት፣ ጋብቻና ፍቺ ናቸው፡፡

### 1.2.2 የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ትርጉም

የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች አመዘጋገብ አሠራርን በመከተል ማለትም ተከታታይ፣ ቋሚና አስገዳጅ የሆነ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና የፍቺ ኩነቶችንና ከኩነቶቹ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ግለሰቦች የሚመለከቱ የሥነ-ሕዝብ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ባህርያትን ለዚሁ ተግባር በተዘጋጁ መዝገቦችና ቅጾች የመመዝገብ፣ የማከማቸት እና ለሚፈልጉበት የህግ፣ የአስተዳደርና የስታቲስቲክስ መረጃ ፍላጎት የማደራጀትና አገልግሎትን የመስጠት ተግባር ነው። በጥቅሉ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ዓለም አቀፍ የኩነቶች አመዘጋገብ መርህን በመከተል በሕግ በተቋቋመና ሕጋዊ የአሠራር መመሪያ ባለው መንግሥታዊ ተቋም በተከታታይ፣ በቋሚና አስገዳጅ አሠራር ኩነቶች እንደተከሰቱ/ እንደተፈፀሙ በምዝገባ ህጉ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የመመዝገብ አሠራርን ተከትሎ የሚከናወን ተግባር ነው፡፡

### 1.2.3 የሕዝብ የክብር መዝገቦች

የሕዝብ የክብር መዝገቦች በፌደራል ወይም በክልል ደረጃ ወጥ በሆነ (በቅርጽም ሆነ በይዘት) ቴክኒካዊ አሠራር ተዘጋጅተውና በአንድ በሕግ የምዝገባ ሥራውን እንዲያካሂድ ወይም

እንዲያስተባብር በተቋቋመ አገር አቀፍ የምዝገባ መ/ቤት በሚተላለፍ ወጥ የቴክኒክና የአስተዳደር መመሪያ፣ በዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን ተቀምጠው በቀበሌ ነዋሪ በሆኑ ግለሰቦች ላይ ወይም በቀበሌው ውስጥ የሚከሰቱ የልደት፣ የጋብቻ፣ የፍቺና የሞት ኩነቶችና ከኩነቶቹ ጋር ግንኙነት ያላቸው ግለሰቦችን የሚመለከቱ የሥነ-ሕዝብ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ባህርያት መረጃዎች የሚመዘገቡባቸው ህጋዊ ሰነዶች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ የሕዝብ የክብር መዝገቦች የመንግስት ንብረት የሆኑና ወሳኝ ኩነቶች በትክክል መከሰታቸውን የሚያረጋግጡ የህግና የአስተዳደር ሕጋዊ ሰነዶች ናቸው፡፡ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ኩነቶች የመዝገብ ቅጾች ናሙና በዕዝል 2 ቀርቧል።

## 1.2.4 የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ምዝገባ

የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ምዝገባ ማለት የሕዝብ ብዛት ዕድገት ምጥነትን የሚወስኑ በዋነኝነት የልደትና የሞት እንዲሁም የጋብቻና ፍቺ ኩነቶችን በሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች የአመዘጋገብ ሥርዓት በቀጣይነትና በቋሚነት የመሰብሰብ፣ የማጠናቀር፣ የመተንተንና ውጤቱንም ለኢኮኖሚያዊ፣ ስነ-ሕዝባዊና ማህበራዊ ዕቅድ ዝግጅት፣ አፈጻጸምና የአፈፃፀም ግምገማ እንዲሁም ለጥናትና ለምርምር ተግባር ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን የማደራጀትና እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን የማሠራጨት ተግባር ነው፡፡

## 1.2.5 የወሳኝ ኩነት (ቫይታል) ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጾች

የወሳኝ ኩነት ስታትስቲክስ ሪፖርት ቅጾች በማዕከል ደረጃ ወጥ በሆነ (በቅርጽም ሆነ በይዘት) ቴክኒካዊ አሠራር ተዘጋጅተው የወሳኝ ኩነት ስታቲስቲክስ መረጃዎችን ከሕዝብ የክብር መዝገብና ከሌሎች ለምዝገባው ከቀረቡ ዶክመንቶችና ከአስመዝጋቢው በመጠየቅ መረጃዎች የሚሰበሰቡባቸው የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና የፍቺ ስታቲስቲክስ ሪፖርት ማድረጊያ ቅጾች ናቸው። እነዚህ ቅጾች በአንድ በተወሰነ ቀበሌ የተከሰቱ ወሳኝ ኩነቶችንና ከኩነቶች ጋር ግንኙነት ያላቸውን ግለሰቦችን የሚመለከቱ የሥነ-ሕዝብ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መረጃዎች ለወሳኝ ኩነት ስታቲስቲክስ መረጃ ጥንቅር በቀበሌው በተመደበ መዝጋቢ ተመዝግበው በአገር አቀፍ ደረጃ የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ መረጃዎችን ለሚያጠናቅረው፣ ለሚተነትነውና ለሚያሰራጨው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት የሚተላለፉባቸው ቅጾች ናቸው። በወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አሰራር የሚሰበሰቡ የኩነቶች ስታቲስቲክስ መረጃዎች በዋነኝነት ሁለት የመረጃ ማሰብሰቢያ አማራጭ አሰራሮችን በመከተል መረጃዎች ይሰበሰባሉ። አንደኛው መንገድ ራሱን የቻለ የወሳኝ ኩነት ስታትስቲክስ ሪፖርት ቅጾችን በማዘጋጀት የሚከናወን ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ከወሳኝ ኩነቶች መዝገቦች ጋር በአንድነት በአንድ የመዝገብ ቅጽ የሚቀርብበት ነው። ሁለቱ አሰራሮች የየራሳቸው ጠንካራና ደካማ ጎን ያላቸው ቢሆንም ከመረጃ አሰባሰብ፣ አጠነቃቀርና አጠቃቀም እንዲሁም አቀማመጥ አንጻር በመገምገም በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና

የኩነቶች ስታቲስቲክስ መረጃዎች በአንድነት በአንድ ቅጽ እንዲዘጋጁ ተደርጓል (ዕዝል 2 ይመለከቱ)።

### 1.2.6 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ እና የኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት (ቶች)

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ እና የኩነቶች ስታቲስቲክስ ምዝገባ አሰራር የሁለት መረጃ ስርዓቶች ጥምረት ውጤት ናቸው። እነርሱም የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት እና የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ምዝገባ ሥርዓት በመባል ይታወቃሉ። የሁለቱ ሥርዓቶች ድምር ውጤት ማለትም የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ እና የኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት በአንድ አገር ዜጎች ላይ ከልደት እስከ ዕልፈተ-ሕይወት የሚከሰቱ ወሳኝ ኩነቶችን (ክስተቶችን) እና ኩነቱ የሚመለከታቸውን ሰዎች የሥነ-ሕዝብና ማህበራዊ ባህርያትን፤ የግለሰቦችን ህጋዊ ማንነት በሚያስረዳ አሰራር በቀጣይነትና በቋሚነት በሕግ ድጋፍ የመመዝገብ፣ የማከማቸትና በዋነኝነት ለሕግና ለአስተዳደር አፈፃፀም ግለሰባዊ ወይም ጥቅል መረጃዎችን የማመንጨት እንዲሁም የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃዎችን የማጠናቀርና የማቅረብ፤ እነዚህንም ተግባራት በአገር አቀፍና በተዋረድ የአስተዳደር ዕርከኖች የሚያስፈጽመውን/ሙትን ተቋም/ማት በሕግ፣ በአስተዳደርና በድርጅታዊ አወቃቀር የማደራጀት ተግባራትን የሚያጠቃልል የመንግሥት ሥራ ነው፡፡

### 1.2.7 ልደት (በህይወት መወለድ)

አንድ ልደት "በህይወት ተወለደ" የሚባለው የእርግዝናው ጊዜ ከግምት ውስጥ ሳይገባ ሕፃኑ ከእናቱ ማሕፀን እንደወጣ ወዲያውኑ ሕይወት ያለው መሆኑ ከታወቀ ነው፡፡ ሕፃኑ ሕይወት ያለው መሆኑ የሚታወቀው ጽንሱ በማህጸን የቆየበት ወራት ከግምት ውስጥ ሳይገባ ከእናቱ ማህፀን በሚወጣበት ወቅት የሚተነፍስ ከሆነ ወይም እትብቱ ከመቆረጡ በፊት ወይም ከተቆረጠ በኋላ ሌላ በሕይወት የመኖር ምልክት (ለምሳሌ የልብ ትርታ፣ የጡንቻዎች እንቅስቃሴ፤ ...ወዘተ) ካሳየ ነው፡፡ ሕፃኑ በሕይወት የመወለድ ምልክት አሳይቶ ወዲያውኑ ቢሞት እንኳን "በሕይወት ተወለደ" ይባላል፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ምልክቶች ካልታዩ ሕፃኑ የተወለደው ሞቶ ነው ማለት ነው፡፡

### 1.2.8 ሞት

ሞት ተከሰተ የሚባለው አንድ በሕይወት ይኖር የነበረ ግለሰብ ወይም በሕይወት የተወለደ ሕጻን በበሽታ፣ በአደጋ ወይም ተለይቶ ባልታወቀ ምክንያት በሕይወት ያለ መሆኑን የሚያሳወቁ ምልክቶች ሙሉ ለሙሉ ለዘለቄታው ሲለቁትና እንደገና ነፍስ ለመዝራት የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

## 1.2.9 ጋብቻ

ጋብቻ ተፈጸመ የሚባለው አግባብ ባለው የቤተሰብ ህግ ጋብቻ ለመፈጸም ህጉ የሚፈቅድላቸው አንድ ወንድና አንዲት ሴት በሕጋዊ መንገድ ባል እና ሚስት መሆናቸው ሲረጋገጥ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ፍትሕ-ብሔር ሕግ ቁጥር 577 መሠረት ሶስት ህጋዊ የጋብቻ ዓይነቶች ተለይተዋል፡፡ እነርሱም ብሔራዊ/ሲቪል ጋብቻ፣ ሃይማኖታዊ ጋብቻ እና ባህላዊ/ልማዳዊ ጋብቻ በመባል ይታወቃሉ፡፡

### 1.2.9.1 ብሔራዊ ወይም ሲቪል ጋብቻ

አግባብ ባለው የቤተሰብ ህግ ጋብቻ ለመፈጸም ህጉ የሚፈቅድላቸው አንድ ወንድና አንዲት ሴት ጋብቻ ለመፈጸም ተስማምተው በአቅራቢያቸው ወደሚገኝ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽ/ቤት በመሄድ የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም ፊት በመቅረብ ህጉ በሚፈቅደው መሠረት ፈቃዳቸውን በፊርማ ሲያረጋግጡና የክብር መዝገብ ሹሙም ይህንኑ ፍቃዳቸውን ተቀብሎ የጋብቻውን ሥርዓት ከአስፈጸመ በኋላ በሕዝብ የክብር መዝገብ ላይ ጋብቻው ለመፈጸሙ ማስረጃ የሚሆን የጋብቻ የምስክር ወረቀት አዘጋጅቶ የሚሰጥበት የጋብቻ ሥርዓት ብሄራዊ ወይም ሲቪል ጋብቻ ይባላል፡፡

### 1.2.9.2 ሃይማኖታዊ ጋብቻ

አግባብ ባለው የቤተሰብ ህግ ጋብቻ ለመፈጸም ህጉ የሚፈቅድላቸው አንድ ወንድና አንዲት ሴት ጋብቻ ለመፈፀም መሟላት ያለባቸውን ሁኔታዎች በማሟላት እንደ ሃይማኖታቸው ወይም ከሁለቱ በአንደኛቸው ሃይማኖት ሥርዓት መሠረት የሚፀና ጋብቻ ለማቋቋም የሚያስችላቸውን ሥርዓት ሲፈጽሙ ሃይማኖታዊ ጋብቻ ተፈፀመ ይባላል፡፡ በሃይማኖት ሥርዓት መሠረት ጋብቻ ሊፈጸም የሚችልበትና የአፈጻጸሙ ሥርዓት እንደየሃይማኖቱ ይወሰናል፡፡ በሃይማኖት ሥርዓት የተፈፀመው ጋብቻ *በምዝገባ ህጉ* በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ (*በህጉ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ እዚህ ይግባ*) ውስጥ በአካባቢ የክብር መዝገብ ጽ/ቤት መመዝገብና ጋብቻው በመንግሥት ዕውቅና ማግኘቱን የሚያረጋግጥ የጋብቻ ምስክር ወረቀት ሊዘጋጅለት ይገባል፡፡ ጋብቻው በመንግስት የፀደቀ ለመሆኑ የሚረጋግጠውና በህግና በአስተዳደር ቦታዎች ለግለሰቡና ለመንግሥት ሊያገለግል የሚችለው ብቸኛ ህጋዊ ሰነድ የሚዘጋጀው በሃይማኖት ሥርዓት የተፈፀመው ጋብቻ በክብር መዝገብ ጽ/ቤት በተዘጋጀው የሕዝብ የክብር መዝገብ ተመዝግቦ የጋብቻ የምስክር ወረቀት ሲዘጋጅለት ብቻ ነው፡፡ ለአካባቢ ምዝገባ ጽ/ቤቱ አሠራር ያመች ዘንድ በምዝገባው ክልል የሃይማኖታዊ ጋብቻ ሥርዓት አፈፃፀሞች በጽሁፍ ለአካባቢው የክብር መዝገብ ጽ/ቤት አስቀድሞ የሚሰጡበትና የሚታወቁበት አሠራር ሊበጅ ይገባል፡፡ ለዚህም የክልሉ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽ/ቤት አስፈላጊውን የአፈፃፀም መመሪያ ያዘጋጃል፡፡

### 1.2.9.3 <u>ባህላዊ ወይም ልማዳዊ ጋብቻ</u>

አግባብ ባለው የቤተሰብ ህግ ጋብቻ ለመፈጸም ህጉ የሚፈቅድላቸው አንድ ወንድና አንዲት ሴት ጋብቻ ለመፈፀም መሟላት ያለባቸውን ሁኔታዎች በማሟላት በሚኖሩበት አካባቢ ባህል ወይም ልማድ ወይም ከሁለቱ ተጋቢዎች በአንዳቸው ባህል ወይም ልማድ መሠረት የሚጸና ጋብቻ ለማቋቋም የሚያስፈልገውን ሥርዓት ሲፈጽሙ ባህላዊ/ልማዳዊ ጋብቻ ተፈጸመ ይባላል፡፡ በባህል ወይም በልማዳዊ ሥርዓት ጋብቻ ሊፈጸም የሚችልበትና የአፈጻጸሙ ሥርዓት እንደአካባቢው ባህልና ልማድ ይወሰናል፡፡ በባህል ወይም ልማድ የተፈፀመው ጋብቻ *በምዝገባ ህጉ* በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ (*በህጉ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ እዚህ ይግባ*) ውስጥ በአካባቢ የክብር መዝገብ ጽ/ቤት መመዝገብና በመንግስት ዕውቅና ማግኘቱን የሚያረጋግጥ የጋብቻ ምስክር ወረቀት ሊዘጋጅለት ይገባል፡፡ ጋብቻው በመንግስት የፀደቀ ለመሆኑ የሚያረጋግጠውና በህግና በአስተዳደር ቦታዎች ለግለሰቡና ለመንግስት ሊያገለግል የሚችለው ብቸኛ ህጋዊ ሠነድ የሚዘጋጀው በባህላዊ/ልማዳዊ ሥርዓት የተፈጸመው ጋብቻ በክብር መዝገብ ጽ/ቤት በተዘጋጀው የሕዝብ የክብር መዝገብ ተመዝገቦ የጋብቻ ምስክር ወረቀት ሲዘጋጅለት ብቻ ነው። ለአካባቢ የምዝገባ ጽ/ቤቱ አሠራር ያመች ዘንድ በምዝገባው ክልል የባህላዊ ወይም ልማዳዊ የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት በጽሁፍ ለአካባቢ የክብር መዝገብ ጽ/ቤት አስቀድሞ የሚሰጥበትና የሚታወቅበት አሰራር ሊበጅ ይገባዋል፡፡ ለዚህም የክልሉ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽ/ቤት አስፈላጊውን የአፈጻጸም መመሪያ ያዘጋጃል።

### 1.2.10 <u>ፍቺ</u>

ፍቺ ማለት በብሔራዊ/ሲቪል ወይም በሃይማኖታዊ ወይም በባህላዊ/ልማዳዊ መንገድ ተመሥርቶ የነበረ ህጋዊ ጋብቻ ሙሉ ለሙሉ ሕጋዊ በሆነ መንገድ ማለትም በህግ በታወቀ የፍቺ ሥርዓት (ለምሣሌ በፍርድ ቤት ወይም በሃይማኖታዊ ወይም በባህላዊ/ልማዳዊ ሥርዓት) ሲፈርስና ሁለቱም ወይም አንዳቸው ባስፈለጋቸው ጊዜ ሌላ ባል/ሚስት ለማግባት የሚያስችላቸውን መብት የሚያስገኝ ድርጊት ነው፡፡

### 1.2.11 <u>የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም</u>

የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና የፍቺ ክስተቶችን እንዲመዘግብ *በምዝገባው ሕግ* ኃላፊነት የተሰጠውና ምዝገባውን በመፈፀም መንግሥትን እንዲወክል በሕግ ሥልጣን የተሰጠው ግለሰብ ነው፡፡ በወሳኝ ኩነት ምዝገባ ስርዓት አማካይነት የሚዘጋጁ ህጋዊና ግለሰባዊ መረጃዎች የአንድን አገር ዜጎች ከመንግስት ጋር በማገናኘት መሰረት የሚሆኑ ግለሰባዊ የህግ መረጃዎችን ለሁሉም የአገሪቱ ዜጎች የሚያስገኙ ከፍተኛ የመንግስት ሰነድ ከመሆናቸው አንፃር መረጃዎቹ እውቅና ማግኘትና መረጋገጥ የሚገባቸው በመስተዳድሩ ከፍተኛ የስልጣን

አካል ነው። ይህንንም ሃላፊነት የሚቀበለውን የመንግስት ስራ አስፈጻሚ ለይቶ የሚሾመው ይኸው የመስተዳድሩ ከፍተኛ የስልጣን አካል ነው።

በተለያዩ ሀገሮች የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም ሆነው የሚመደቡ ግለሰቦች እንደየአገሩ የአስተዳደር አወቃቀርና አደረጃጀት እንዲሁም የኢኮኖሚና የማህበራዊ የዕድገት ደረጃ ይለያያል፡፡ በበርካታ ሀገሮች የከተማ ከንቲባዎች፣ የአካባቢ አስተዳዳሪዎች፣ ዳኞች ወይም ሌላ የመንግሥት ሥራ አስፈፃሚ ተቋም ኃላፊዎች የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም ተግባርን ከዕለት ተዕለት ተግባራቸው ጋር አጣምረው እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡ በሌላም በኩል በአንዳንድ አገሮች የፖሊስ መኮንኖች፣ ሐኪሞች፣ ነርሶች፣ አዋላጅ ነርሶች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ የሕብረተሰብ መሪዎች፣ ...ወዘተ የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም ሆነው ያገለግላሉ፡፡ ከእነዚህም ብዙዎቹ የምዝገባውን ሥራ ከሌሎች ሥራዎቻቸው ጋር ደርበው ይሠራሉ ወይም ደግሞ ካላቸው ኃላፊነት ወይም ተሰሚነት አንፃር ሥራውን በበላይነት እንዲያስተባብሩ ተደርጐ የዕለት ተዕለት ሥራውን ሌሎች የምዝገባ ሠራተኞች እንዲሠሩት ይደረጋል፡፡ በዚህ መመሪያ መሠረት የወረዳ አስተዳዳሪዎች በገጠር ቀበሌዎች ለተመዘገቡ ወሳኝ ኩነቶች የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም በመሆን የሚያገለግሉ ሲሆን የማዘጋጃ ቤት ከንቲባዎች ደግሞ በከተማ ቀበሌዎች ለሚመዘገቡ ወሳኝ ኩነቶች የክብር መዝገብ ሹም በመሆን ያገለግላሉ።

## 1.2.12 <u>የወሳኝ ኩነት መዝጋቢ</u>

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ስርዓት አስተዳደራዊ አደረጃጀት መዋቅርን በመከተል በየአስተዳደር እርከኑ የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹሞች በመስተዳድሩ ከፍተኛ የስልጣን አካል እንዲሾሙ የሚደረግ ቢሆንም እነዚህ የምዝገባ ሹሞች ካለባቸው ተደራራቢ ስራና ኃላፊነት አንፃር የምዝገባውን የዕለት ተዕለት ተግባር እንዲያከናውኑ አይጠበቅም። ለዚህም ሲባል እንደአስፈላጊነቱ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የወሳኝ ኩነት መዝጋቢዎች በቀበሌ መስተዳድር ጽ/ቤት መዋቅር ውስጥ በሚደራጀው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ክፍል እንዲመደቡ ይደረጋል። የተሟላ የአደረጃጀት መዋቅርና የሰው ሀይል መደብ ባላቸው የከተማም ሆነ የገጠር ቀበሌዎች ለወሳኝ ኩነት ምዝገባ አዲስ የሰው ሀይል እንደመድቡ አይጠበቅም። እዚህ ላይ በቀበሌ መስተዳድሮች መዝጋቢዎችን በመመደብ ረገድ እንደመርህ ሊወሰድ የሚገባው ጉዳይ የኩነቶች መረጃዎች ለመስተዳድሩ የተለያዩ የማህበራዊና የኢኮኖሚ አገልግሎት አሰጣጥ ተግባራትና ለቀበሌው የስነ-ህዝብ መረጃዎችን በማስገኘት ካላቸው ወሳኝ ድርሻ አንጻር መስተዳድሮች ሥራዎችን በማቀናጀት በግልጽና የምዝገባ አሰራሩን በተከተለ መንገድ ለምዝገባው ቅርበት ላለው የሥራ ዘርፍ አልፎም ሰራተኛ የሥራ ድርሻን በመስጠት ባላቸው የሰው ሀይል የምዝገባውን ሥራ ማከናወን እንደሚገባ ነው።

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ዓላማ ግቡን እንዲመታ መዝጋቢው ኃላፊነቱን በትክክል መወጣት እንዲችል በዋነኝነት በቂ የሕግና የአስተዳደር ዕውቀት ሊኖረው ይገባል፤ ከዚህም በላይ

በመልካም ስነ-ምግባር የታነፀና በአካባቢው ህብረተሰብ ተሰሚነትና ተዓማኒነት ያለው እንዲሁም ለሥራ ተነሳሽ የሆነ ግለሰብ መሆን ይኖርበታል፡፡

### 1.2.13 የወሳኝ ኩነቶች አስመዝጋቢ

የወሳኝ ኩነቶች አስመዝጋቢ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻ ወይም የፍቺ ኩነቶች እንደተከናወኑ/እንደተከሰቱ *በምዝገባ ህጉ በተሰጠው የጊዜ ገደብ* ውስጥ በአካባቢ የምዝገባ ጽ/ቤት ተገኝቶ የማስመዝገብ ኃላፊነትና ግዴታ በሕግ የተሰጠው/የተጣለበት ግለሰብ ወይም የድርጅት ኃላፊ ወይም ተወካይ ነው፡፡ አስመዝጋቢው አንድ ወሳኝ ኩነት መከሰቱን፣ የክስተቱን ባህርያትና ከክስተቱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን ሰዎች የሥነ-ሕዝብ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ባህርያትን ለመዝጋቢው በወቅቱ እንዲያሳውቅ *በምዝገባ ህጉ ግዴታ* የተጣለበት ነው፡፡ አስመዝጋቢው የሚሰጣቸው መረጃዎች ለህግና ለአስተዳደር ጉዳዮች አፈፃፀም ከሚሰጡት ግልጋሎት በተጨማሪ ለወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ መረጃ ጥንቅር ግብዓት የሚሆኑ ግለሰባዊ መረጃዎች የሚሰበሰቡበት በመሆኑ መረጃው ህጋዊ መስፈርቶችን ያሟላ፣ ትክክለኛና በሕግ በተወሰነው የጊዜ ገደብ በተወሰነው ቦታ ቀርቦ የሚመዘገብ ሊሆን ይገባል፡፡

አንድ አስመዝጋቢ እንደ ኩነቱ ዓይነት በማስመዝገቡ ሂደት ምን ሁኔታዎችን ማሟላት እንዳለበት፣ የአፈፃፀም ግዴታዎቹም ምን እንደሆኑ *በምዝገባ ሕጉ* በግልጽ የሚቀመጡ ቢሆንም አስመዝጋቢው እነዚህን የአመዘጋገብ ሥርዓቶች እንዲያውቃቸው መደረግ አለበት፡፡

### 1.2.14 ጠቋሚ

ጠቋሚ ማለት አንድ ወሳኝ ኩነት መከሰቱን፣ የክስተቱን ባህርያትና ከኩነቱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን ሰዎች የሥነ-ሕዝብ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ባህርያትን ለምዝገባ ጽ/ቤት በወቅቱ የሚያሳውቅና በሕግ የማስመዝገብ ኃላፊነትና ግዴታ የተጣለበት አስመዝጋቢ በወቅቱ ቀርቦ ኩነቱን እንዲያሳውቅ ጥቆማ እንዲያደርግ በምዝገባ ጽ/ቤት ኃላፊነት የተጣለበት የምዝገባ ክልል ነዋሪ ግለሰብ ወይም የድርጅት ኃላፊ ወይም ተወካይ ነው፡፡ ለሥራው መቃናትና ለመረጃዎቹ ጥራት ማግኘት ሲባል በእያንዳንዱ የምዝገባ ክልል አንድ ወይም ከዚያ በላይ ቁጥር ያላቸው ጠቋሚዎችን መመደብ ያስፈልጋል፡፡ በምዝገባው አሠራር የጠቋሚዎች ኃላፊነት በግልጽ *በምዝገባ ህጉ* የሚገለጽ ከመሆኑም በላይ ስለ ምዝገባ ሕጉ አስፈላጊው ሥልጠና ይሰጣቸዋል፡፡

### 1.2.15 መደበኛ መኖሪያ ቦታ

መደበኛ መኖሪያ ቦታ ማለት አንድ ግለሰብ ለስድስት ወራትና ከዚያ በላይ ያለማቋረጥ የኖረበት ወይም ስድስት ወር ባይሞላውም ለዘለቄታው ለመኖር በማሰብ እየኖረበት ያለ ወይም

ደግሞ መደበኛ መኖሪያ ከሌለው ኩነቱ በተከሰተበት ወቅት እየኖረበት ያለው ትንሹ የአስተዳደር እርከን ማለትም የቀበሌ አስተዳደር ነው፡፡

በወሳኝ ኩነቶች አመዘጋገብ ሥርዓት መሠረት "ኩነቶች" በሚመለከታቸው ግለሰቦች መደበኛ መኖሪያ ቦታ ወይም በተከሰቱበት ቦታ የመመዝገብ አማራጮች አላቸው፡፡ በመሠረቱ አንድን ኩነት በተከሰተበት ቦታ መመዝገብ ኩነቱ *በምዝገባ ሕጉ በሚደነገገው* የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲመዘገብና መረጃውም ወቅታዊ እንዲሆን ያስችላል፡፡ በአንፃሩ ኩነቱን በመደበኛ መኖሪያ ቦታ መመዝገብ ኩነቱ ከሕግ አንፃር ካለው ጠቀሜታ በተጨማሪ ተዛማጅ የግለሰቦች የሥነ-ሕዝብ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ባህርያትን አጣርቶ ለመመዝገብና መረጃውን ለአጠቃቀም ምቹ ለማድረግ ይረዳል፡፡ አንድን ኩነት በመደበኛ መኖሪያ ቦታ መመዝገብ አልፎ አልፎ ሊያስቸግር ይችላል፡፡ ለምሳሌ ኩነቱ የተፈጸመባቸው ግለሰቦች ከአንድ በላይ መኖሪያ ቦታዎች ያላቸው (ወታደሮች፣ ተማሪዎች ወይም ተዘዋዋሪ ነጋዴዎች፣ ... ወዘተ) ወይም ደግሞ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ የሚኖሩ ማለትም መደበኛ መኖሪያ ቦታ የሌላቸው ወይም በጊዜያዊነት ጥገኛ ሆነው የሚኖሩ ግለሰቦች ሊሆኑ ይችላል፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ኩነቶችን በመደበኛ መኖሪያ ቦታ መመዝገብ ያስቸግራል፡፡ ይህም ሆኖ ኩነቶች በተቻለ መጠን በመደበኛ መኖሪያ ቦታ መመዝገባቸው ተመራጭነት አለው፡፡ ሆኖም አንድን ወሳኝ ኩነት በተከሰተበት ቦታ መመዝገብ የግድ ከሆነ ያሉት አማራጮች የምዝገባውን ሪኮርዶችና ማስታወቂያዎች ወደ ግለሰቡ መደበኛ መኖሪያ ቦታ በወቅቱ መላክ ወይም ደግሞ በስተመጨረሻ በጥቅል ተጠናቅረው የሚዘጋጁ የስታቲስቲክስ መረጃዎችን መደበኛ መኖሪያ ቦታን መሠረት አድርገው እንዲወጡ ማድረግ ነው፡፡ በዚህ የምዝገባ መመሪያ መሠረት ወሳኝ ኩነቶች "ኩነቱ" በሚመለከታቸው ከታች በተመለከቱ ግለሰቦች መደበኛ መኖሪያ ቦታ ላይ ተመስርተው ይመዘገባሉ፡፡

- ልደት - በህፃኑ/ኗ እናት መደበኛ መኖሪያ ቦታ
- ሞት - በሟች መደበኛ መኖሪያ ቦታ
- ጋብቻ - በሙሽራው ወይም በሙሽሪት *(በአንደኛቸው ቢሆን ይመረጣል)* መደበኛ መኖሪያ ቦታ
- ፍቺ - በባል ወይም በሚስት *(በአንደኛቸው ቢሆን ይመረጣል)* መደበኛ መኖሪያ ቦታ

# ምዕራፍ ሁለት

## ስለ ሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ

### 2.1 <u>የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ዓላማዎች</u>

የሚከተሉት ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ዓላማዎች በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ ናቸው፤

1. በሀገሪቱ የገጠርና የከተማ አስተዳደር እርከኖች በሕግ የተቋቋመ የምዝገባ መዋቅር ዘርግቶ ተከታታይ፣ ቋሚና አስገዳጅ የሆነ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና የፍቺ ኩነቶችን እንደተከሰቱ ህጉ በሚፈቅደው የጊዜ ገደብ ውስጥ በመመዝገብ ለህግ፣ ለአስተዳደርና ለስታቲስቲክስ መረጃ ጥንቅር የሚውሉ ህጋዊና ግለሰባዊ መረጃዎችን ማስገኘት፣

2. በምዝገባ ሕጉና ለአመዘጋገቡ በወጣው የምዝገባ አፈጻጸም መመሪያ መሠረት ለተመዘገቡ ኩነቶች ለባለጉዳዮች ህጋዊ የኩነቶች የምስክር ወረቀት መስጠት፣

3. ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የተገኙትን ግለሰባዊ የኩነቶች መረጃዎችን ከመዝገቦች ላይና አስመዝጋቢዎችን በመጠየቅ በተዘጋጁ በወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጾች በመሙላት የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ መረጃዎችን ለሚያጠናቅረው፣ ለሚተነትነውና ለሚያሰራጨው አካል መላክ ናቸው፡፡ በዚህ መመሪያ መሠረት የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ቅጾች በኩነቶች መዝገብ ቅጾች ተካተው የቀረቡ ስለሆነ የመዝገብ ቅጾች ቅጂ ለወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ መረጃ ጥንቅር ይውላሉ።

### 2.2 <u>በሕዝብ የክብር መዝገብ የሚመዘገቡ ኩነቶች ዓይነት</u>

በሕዝብ የክብር መዝገብ ውስጥ የሚመዘገቡ ኩነቶች ልደት፣ ሞት፣ ጋብቻና ፍቺ ናቸው፡፡ እነዚህም ኩነቶች የተመረጡት የኩነቶቹ በአንድ ግለሰብ ላይ መከሰት ከማናቸውም ሌሎች ኩነቶች የበለጠ ግለሰቡን ከመንግስት ጋር በማገናኘት ቀዳሚ የህጋዊ ሰነድ ምንጭ በመሆን፤ የግለሰቡን ማንነት ከቤተሰቡ ጀምሮ ከሚኖርበት ማህበረሰብ ጋር ያለውን ግንኙነት የሚወስኑ፣ መንግስት ለሚያደርጋቸው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አገልግሎቶች የአፈጻጸም የመረጃ ፍላጎት የግብዓት ምንጭ በመሆናቸው ነው፡፡ ከዚህም ሌላ አንድ ግለሰብ በልደት ወደዚህ ዓለም ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ በሞት እስከሚለይበት ጊዜ ድረስ የሚደርሱበትን ክስተቶችና በዚህ መካከል የሚያሳልፋቸውን የማህበራዊና ህጋዊ የሕይወት ለውጦችን (Civil Status Change) በህጋዊ አሠራርና መንገድ መከታተል ስለሚያስችሉ ነው፡፡ በእርግጥ ወሳኝ ኩነቶች በመባል በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቴክኒካዊ መመሪያዎች ተለይተው የሚታወቁት የኩነት ዓይነቶች በርካቶች ናቸው።

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሚታወቁትን ሁሉንም ወሳኝ ኩነቶች ለመመዝገብ የሚያስችል የምዝገባ ተቋምና መሰል አስተዳደራዊ መዋቅሮችን በአንድ ጊዜ መዘርጋት በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ባለ ታዳጊ አገር አስቸጋሪና አዳጋች ነው፡፡ በመሆኑም በበርካታ ታዳጊ ሀገሮች እንደታየው አሠራር በቅድሚያ ዋነኛ ወሳኝ ኩነቶች (Principal Vital Events) በሚባሉት በመጀመር ቀስ በቀስ ሌሎችንም እያካተቱ መሄድ የተለመደና አግባባዊ አሠራር ነው፡፡ በመሆኑም በኢትዮጵያም ምዝገባውን ከላይ በተገለፀው መሠረት ቀዳሚ ወሳኝ ኩነት በተባሉት በልደት፣ በሞት፣ በጋብቻና ፍቺ ምዝገባ በመጀመር አቅም በፈቀደ መጠን ሌሎች ኩነቶችን ለማካተት የሚያስችል የአሠራር ስልት የሚከተል ይሆናል፡፡

## 2.3 <u>ወሳኝ ኩነቶች የሚያስገኙት ጥቅም</u>

ወሳኝ ኩነቶች (Vital Records) በነጠላም ሆነ በጥቅል ለግለሰቦች፣ ለማህበረሰብና ለመንግስት ከፍተኛ ጥቅም ያስገኛሉ፡፡ ከእነዚህም ጥቅሞች ዋና ዋናዎቹ በሚቀጥሉት ገጾች ቀርበዋል፡፡

### 2.3.1 <u>ለግለሰቦች የሚያስገኙት ጥቅም</u>

ከምዝገባ ሥርዓቱ የሚገኙት ህጋዊ የኩነት መረጃዎች ማለትም የወሳኝ ኩነት የምስክር ወረቀቶች እና በመዝገቦች የሠፈሩ መረጃዎች ግለሰቦች ከመወለድ ጀምሮ በማህበረሰብ አባልነታቸው ሊደረግላቸው የሚገቡ ዕውቅና የተሰጣቸውን መብቶች ለመጠየቅና በማናቸውም ወቅት (ቦታና ሁኔታ ሳይወስናቸው) የመብቶቹ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችሉዋቸው ህጋዊ ሰነዶች ናቸው፡፡ በመሆኑም መረጃዎቹ በተለይ በፍርድ ቤቶች፣ በማናቸውም የአስተዳደር፣ የማህበራዊና የኢኮኖሚ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንዲሁም የመምረጥና የመመረጥ መብትን በማስከበር ግለሰቦች ማንነታቸውን ለመግለጽና የኩነቶቹን መከሰት ለሚፈልጉት የመብትና የአገልግሎት ጥያቄ ያለተጨማሪ የሰው ወይም የአስተዳደር መረጃ (ያለሶስተኛ ወገን አስረጅነት) በመረጃነት በማቅረብ ይጠቀሙባቸዋል፡፡ ከነዚህም ጥቅሞች ዋና ዋናዎቹ በኩነቶች ዓይነት ከታች ተመልክተዋል፡፡

#### 2.3.1.1 <u>በህይወት መወለድ ሰነድ (Live birth record)</u>

ሀ. <u>የማንነት ህጋዊ መሠረትን በመጣል፥</u>

ወላጆችን ለማወቅ፤ ቤተሰባዊ ዝምድናን፣ አሳዳጊን፣ ማንነትን ለመለየት፤ ... ወዘተ

ለ በሌሎች ወሳኝ ኩነቶችና የማንነት ለውጥ ምዝገባዎች፥

በጋብቻ፣ በፍቺ ወይም በጉዲፈቻ ምዝገባ፤ ዜግነትን በመቀየር፤ ማንነትን ህጋዊ በማድረግ፣ ስምን በመቀየር፣ በማናቸውም ዕድሜ በህጋዊ የኩነት መዝገቦች ተጨማሪ ወይም የለውጥ መረጃዎችን ለማድረግ፣ ...ወዘተ

ሐ. መብትን ለመጠየቅ፥

ውርስ በተመለከተ፤ የንብረት ባለቤትነት፤ በልጅነት ጊዜ የመጠበቅ፤ ለቤተሰብ ዕርዳታ ለመጠየቅ (ለምሳሌ ለህፃናት እስከተወሰነ ዕድሜ ክልል በአገሩ ህግ መሠረት የኑሮ ድጎማ ለመጠየቅ)፣ የወሊድ ፈቃድ መብትን ለመጠየቅ፣ በአነስተኛ ኑሮ ላይ ለሚገኙ የወተትና የምግብ ራሽን ድጎማ ለመጠየቅ፤ ለአካለ ስንኩላን ህፃናት የኑሮ ድጎማ ለመጠየቅ፣ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ለማግኘት፤ የበሽታ መከላከያ መድሃኒቶችን/ ክትባቶችን ለማግኘት፣ ከወሊድ በኋላ ህፃናትና እናቶች የጤና እንክብካቤ ለማግኘት፣...ወዘተ

መ. ዕድሜን ወይም የትውልድ ቀንን መሠረት በማድረግ የተወሰነ ዕድሜ ሲደረስ የሚሰጡ የአገልግሎት መብቶችን ለመጠየቅ፥

ት/ቤት ለመግባት፣ በሥራ ለመሠማራት ፈቃድ ለማግኘት፣ በሰራዊት አባልነት ለማገልገል ወይም ለመገለል፣ የነዋሪነት ወይም የማንነት መታወቂያ ለመጠየቅ፣ መሣሪያ የመያዝ ፈቃድ ለመጠየቅ፣ የውርስ መብት ህጋዊነትን ለማሳወቅ፣ የመምረጥና መመረጥ መብትን ለመጠቀም፣ ለጋብቻ ብቁነት ፈቃድን ለመጠየቅ፣ የትምህርት ድጎማ ለመጠየቅ፣ የጡረታ ዋስትና ለማግኘት ወይም (ቀድሞ) ጡረታ ለመውጣት (ለመጠየቅ)፣ ... ወዘተ

ሠ. የትውልድ ቦታንና የምዝገባ ቦታን እንዲሁም በነዚህ መረጃዎች ላይ በመመሥረት የሚገኙ መብቶችን በህጋዊ መረጃ ለማቅረብ፥

ዘርን/ብሄረሰብን ለማወቅ፣ ዜግነትን በህጋዊነት ለመመሥረት፣ ወደ ሌላ አገር ክልል ለመግባት እና ዜግነትን ለመጠየቅ፣ ወደ ውጪ አገር ለመውጣት ወይም አገር ውስጥ የመግባት ፈቃድ ለመጠየቅ፣ ለውጭ አገር ጉዞ ፓስፖርት ለመጠየቅ፣ በሚኖሩበት አገር ከታክስ ወይም የወታደርነት አገልግሎት ጥያቄ ነፃ ለመሆን፣ እንደገና ወደ ራስ አገር የመመለስ (repatriation) ጥያቄን ለማቅረብ፣ ... ወዘተ ያገለግላል።

#### 2.3.1.2 የሞት መከሰት ሰነድ (Death record)

ሀ. ለሟች ቀሪ ዘመዶች ሟቹ ለመሞቱ ህጋዊ መረጃ በመሆን፥

ሟችን የመቅበር ፈቃድ ለማግኘት፣ ውርስ የሚገባቸው የመውረስ ጥያቄ ለማቅረብ፣ የኢንሹራንስ ጥያቄ ለማቅረብ፣ የቤተሰብ ድጎማ ጥያቄ ለማቅረብ፣ በህይወት ለሚኖረው የትዳር ጓደኛ የማግባት ፈቃድ ለመጠየቅ፣ አጠራጣሪ

ወይም የሞቱ ምክንያት ወንጀል ለሆኑ ለሚመለከተው አካል ለመጠቆም ወይም ለማመልከት፣ ... ወዘተ

ለ. ሞቱ የተፈፀመበትን ቀን እና ቦታ በማሳወቅ ህጋዊ መረጃ በመሆን፣

#### 2.3.1.3 የጋብቻ መፈፀም ሰነድ (Marriage record)

ሀ. ጋብቻ ለመከሰቱ ህጋዊ መረጃ በመሆን÷

ጋብቻው ህጋዊ መሆኑን ለማረጋገጥ፣ የተጋቢዎቹን ዝምድናና ግንኙነት ህጋዊነት ለማረጋገጥ፣ በቤተሰብ የመጠበቅ ህጋዊ መብትን ለማረጋገጥ፣ ህጋዊ ወራሽነትን ለማረጋገጥ፣ ለቤተሰብ ድጎማ ለመንግስት ጥያቄ ለማቅረብ፣ ከተጋቢዎች አንዳቸው ሲሞቱ ቋሚው የኢንሹራንስ ጥያቄን ለማቅረብ፣ ጋብቻ በሚፈርስበት ጊዜ የልጆች አስተዳደግን ለመወሰን፣ ወደ ውጭ አገር ለመጓጓዝ ፓስፖርት የማግኘት ፈቃድን ለማቅረብ፣ የልጆችን ህጋዊነት ለማረጋገጥ፣ የራስን ልጆች ህጋዊነት ለመመሥረት እንዲሁም ከሌላ የተወለዱትን ለማስመዝገብ፣ የዜግነት ቅያሬን ለመጠየቅ፣ ... ወዘተ

ለ. ጋብቻው የተፈፀመበትን ቀን እና ቦታ በማሳወቅ ህጋዊ መረጃ በመሆን፣

#### 2.3.1.4 የፍቺ መፈፀም ሰነድ (Divorce record)

ሀ. ፍቺ ለመፈፀሙ ህጋዊ ማረጋገጫ በመሆን÷

እንደገና የማግባት ጥያቄን ለማቅረብ፣ ከፍቺ በኋላ የንብረት ክፍፍል ለማድረግ፣ ከፍቺ በኋላ ስለተወለዱ ልጆች ህጋዊ መረጃ ለመሆን፣ ከፍቺ በኋላ በአንደኛቸው የትዳር ጓደኛ ምክንያት ከሚመጡ የገንዘብ ወይም የንብረት ጥያቄዎች (ዕዳ) ነፃ ለመሆን፣ ... ወዘተ

ለ. ፍቺው ለተፈፀመበት ቀንና ፍቺው ለተደረገበት ቦታ ህጋዊ መረጃ በመሆን፤

### 2.3.2 ወሳኝ ኩነቶችን ማስመዝገብ ለማህበረሰብ (Societal) ማህበራዊ አገልግሎቶችን በመስጠት የሚያስገኙት ጥቅም

ወሳኝ ኩነቶች በማህበራዊ አገልግሎት ዘርፍ በተለይ መንግስት የሚያወጣቸውን ጥቅል ዕቅዶችና ፕሮግራሞችን መሠረት በማድረግ እስከ ትንሹ የህብረተሰብ ክፍል አልፎም በቤተሰቦችና በግለሰቦች ደረጃ ልዩ ልዩ ማህበራዊ አገልግሎቶቸን ወቅታዊ፣ ቀጣይና ቋሚ ክትትልን በማድረግ አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስችል አሠራርንና ሥርዓትን

ለመዘርጋት ጥቅም ላይ የሚውሉ መረጃዎችን በማፍለቅ ጥቅም የሚሰጡበት ነው። ከነዚህም ጥቅሞች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ከታች ተመልክተዋል።

ሀ. <u>በህዝብ ጤና አጠባበቅ ፕሮግራሞች ከወሊድ በኋላ የእናቶችንና የህፃናትን ጤና በመጠበቅ የሚሰጠው ጥቅም፥</u>

በአንድ የማህበረሰብ ክፍል የተከሰቱ ልደቶችን ከያዘው መዝገብ ዝርዝር በመነሳት ለእያንዳንዷ እናትና ለተወለደው ህፃን ልደቱ ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ ተገቢውን የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ/ለማስደረግ የልደት መዝገቡ መነሻ ይሆናል። የልደት ዝርዝሩ ስለ እናትየዋና የተወለደው ህፃን ተጨማሪ ግላዊ መረጃዎችን ስለሚይዝ በዚያ መረጃ መሠረት ለአካባቢው የተመደበው ጤና ተጠሪ መረጃዎችን ተከትሎ እናትየዋ ለተወለደው ልጅ ተገቢውን እንክብካቤ ለማድረግ የሚያስችላትን ምክርና ድጋፍ በወቅቱ በቦታው በመገኘት ጭምር እንዲያደርግ መረጃው ምሪት በመስጠት ያገለግላል። ከወሊድ በኋላ የልጁንና የእናትየውን አመጋገብና ጤና አጠባበቅ ምክርና ክትትል ለማድረግ፣ ህፃናትን ከታወቁ የልጅነት በሽታዎች ለመከላከል ክትባት ለመስጠት የአካባቢውን የልደት ዝርዝር የሚያሳየው መዝገብ ትልቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በተለይም በመጀመሪያ የተወለዱ ልጆች፣ ሲወለዱ ዝቅተኛ ክብደት ያላቸውን፣ በተለያየ የጤና ችግር የተነሳ የአካል ጉድለት ወይም ችግር ያለባቸውን እና በወሊድ ወቅት ውስብስብ ችግር የነበረባቸውን ለይቶ በቅርበት ለመከታተልና ወቅታዊ ዕርዳታ በመስጠት የአፈፃፀም ምሪት የመረጃ ምንጭ ከልደት መዝገብ የሚዘጋጀው የልደት ዝርዝር ነው።

ለ. <u>ችግር ውስጥ ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለይቶ በተለዩ የህዝብ ጤና አጠባበቅ ፕሮግራሞች ለመከታተል፥</u>

ሲወለዱ የተለያየ የአካል ጉዳት/ጉድለት ያለባቸውን ህፃናት በመለየት ተገቢው የህክምና ዕርዳታ ተሰጥቶአቸው የሚድኑበት ወይም ችግሩ የሚስተካከልበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፣ አካለ ጐደሎ ሆነው የተወለዱ ህፃናት ተገቢውን የህክምናና የትምህርት ክትትል እንዲያገኙ ለማስቻል፣ ብዙ የወለዱ እናቶች ለቤተሰብ ምጣኔ የሚመረጡበትን እንዲሁም የመጀመሪያ ልጅ የወለዱትን ደግሞ ለከፍተኛ የሞት አደጋ ሊጋለጡ የሚችሉ ስለሆነ እነርሱን የተመለከተ ጥናት የማካሄድ፣...ወዘተ

ሐ. <u>በህዝብ ጤና አጠባበቅ ፕሮግራም የተላላፊ በሽታዎች ቁጥጥርን በማድረግ፥</u>

በሞት መዝገቡ የሞት ምክንያታቸው በተላላፊ በሽታ መያዝ ከሆነ ግለሰቦች መረጃ በመነሳት አፋጣኝ ክትትል በማድረግ በሽታው እንዳይዛመት ከሟቹ ጋር ግንኙነት ያላቸው ቤተሰቦች ተገቢውን ህክምና በወቅቱ እንዲያገኙ

ለማድረግ ያስችላል። በዚህ ረገድ እንደ ሳንባ ነቀርሳ፣ ቢጫ ወባ፣ ወባ፣ ወረርሽኝ፣ ... ወዘተ በመሳሰሉት ተላላፊ በሽታዎች ተጠቅተው ከሞቱ ሰዎች መረጃ (ከሞት መዝገቡ) በመነሳት ተገቢውን ወቅታዊና ተከታታይ እርምጃዎችን እያንዳንዱን ቤተሰብ መሠረት ባደረገ መልኩ ለማድረግ፣ እንዲህ ዓይነት ተላላፊ በሽታዎችን ለመቆጣጠር ከሚች ጋር ግንኙነት ያላቸውን በመለየት አልፎም ለአካባቢው ህብረተሰብ የበሽታውን መከላከያ ክትባት ለመስጠት ዋነኛው የመረጃ ምንጭ የሞት መዝገቡ ነው። በዚህ ዘርፍ በአሁኑ ወቅት ለኤድስ ወረርሽኝ መከላከያ የህክምና መድሀኒት ለማግኘት በሚደረገው ጥረት ከሞት መዝገብ የሚገኘው መረጃ ትልቅ ጠቀሜታ አለው።

መ. <u>የህዝብ ደህንነት ጥበቃ፣ አደጋ መከላከልና ወንጀልን ለማጥፋት በሚዘረጉ ፕሮግራሞች እንዲሁም የተለያዩ የአስተዳደር መዝገቦችን በማደስ ጥቅም በመስጠት፥</u>

የሞት ምዝገባ ጽሁፍን (መዝገቡን) መሠረት በማድረግ የማህበራዊ ደህንነት ፋይሎችን፣ የበሽታ መከሰት መመዝገቢያ መዝገቦችን፣ የመራጮች መዝገቦችን/ ዝርዝሮችን፣ የውትድርና አገልግሎትና የግብር ከፋይ መዝገቦችን ለማደስ ያገለግላል፤ ...

ሠ. <u>ለሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶችና ፕሮግራሞች አፈፃፀም ጥቅም በመስጠት፥</u>

በህፃናት/ልጆች ጥበቃና እንክብካቤ ተግባር ላይ የተሰማሩ የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በፊደል ቅደም ተከተል ከተዘጋጀው የልደት መዝገብ በመነሳት የቤተሰብ ድጎማ እና መሰል ማህበራዊ ግልጋሎት ፕሮግራሞችን የአስተዳደር አፈፃፀምና የክትትል ተግባርን ለማከናወን፣ የጋብቻ ወይም የፍቺ መጠኖችን መሠረት በማድረግ አካባቢያዊ ግልጋሎት ሰጪ ተቋማትን በማቋቋም እና በተለይ የጋብቻ ወይም የፍቺ መጠን ከፍተኛ በሆነበት አካባቢ ልዩ ጥናትና ክትትል ለማድረግ፣ ... ወዘተ

ረ. <u>ለጥናትና ምርምር ተግባር ጥቅም በመስጠት፥</u>

ለበርካታ ወቅታዊ፣ ያለፈና የወደፊቱን የተመለከቱ ጥናቶች ለማካሄድ የኩነቶች መዝገቦች ከፍተኛ ጥቅም ይሰጣሉ፤ በዚህ ዘርፍ የሚከተሉት ለአብነት ይጠቀሳሉ፣

- በጤና ምርምር (Health research) ዘርፍ
- በኢፒዲሞሊጂ ምርምር (Epidemological research) ዘርፍ
- በቦታ፣ በወቅትና በባህርይ የሞት ልዩነቶችን (Mortality differentials) በማጥናት

- በታሪክ ጠቀስ ስነ-ህዝብ (Historical Demography) ጥናትና ምርምር ዘርፍ

### 2.3.3 በወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ዘርፍ የሚሰጡት ጥቅም

በግለሰባዊ የኩነት ሰነዶች (Individual vital records) ተመዝግበው በመዝገብ የተያዙ የወሳኝ ኩነቶች መረጃዎች በአንድነት ተጠናቅረው በጥቅል መረጃነት የሚዘጋጁበት የሙያ መስክ "ወሳኝ ኩነቶች (ቫይታል) ስታትስቲክስ" በመባል ይታወቃል። የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ጥቅምን በሁለት ሰፊ ዘርፎች መክፈል ይቻላል። አንደኛው በአስተዳደር ግልጋሎት ዘርፍ ማለትም በህዝብና በግል የማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚሰጠው አገልግሎት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ለምርምር ተግባር ነው።

#### 2.3.3.1 የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ በአስተዳደር አገልግሎት ዘርፍ

ስነ-ህዝብ ስታቲስቲክስ በአጠቃላይና የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ በተናጠል ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ስነ-ህዝባዊ የሕዝብ አስተዳደር (public administration) ተግባሮችን በማቀድ፣ የአፈፃፀም ስትራተጂዎችን በመንደፍና አፈፃፀማቸውን በመከታተል በኢኮኖሚ በበለፀጉትም ሆነ በታዳጊ ሀገሮች የመረጃ መሠረት መሆናቸው ግንዛቤ ካገኘ በርካታ ዓመታትን አስቆጥሯል። የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ በሕዝብ አስተዳደር ዘርፍ ከሚሰጠው ግልጋሎት አንፃር ትልቁን ድርሻ የሚወስደው የህዝብ ጤና አጠባበቅ (Public Health) ዘርፍ ነው። በዚህ ዘርፍ የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ በህዝብ ጤና አጠባበቅ ፕሮግራም ቀረጻና አፈፃፀም ከሚሰጠው አገልግሎት ዋና ዋናዎቹን በአጭሩ ከታች እንመለከታለን።

ሀ. በእናቶችና ልጆች ጤና አጠባበቅ እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን ደረጃ የመረጃ አቅርቦት አገልግሎት በመስጠት፥

በእናቶችና ልጆች ጤና አጠባበቅ ፕሮግራም የተካተቱ የጤና ግልጋሎቶችን በትክክልና በወቅቱ ለተገልጋዮቹ ሊደርሱ በሚችሉበት አኳኋን የተሳካ (effective) አተገባበር ሊፈጠር የሚችለው ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት በሚገኘው የወሳኝ ኩነቶች ስታትስክቲስ ማለትም የልደት እና በእናቶችና ህፃናት ሞት መረጃ አማካይነት ነው። ይህ የመረጃ ምንጭ በተለያዩ የእናቶችና የህፃናት ባህርያት እንዲሁም ከኩነቱ መከሰት ጋር የተያያዙ ክንዋኔዎች ጋር በሠንጠረዥ ሲቀርብ ከወሊድ ጋር በተያያዘ በእናቶችና በህፃናት ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን ብዛት ለመከታተልና ለመከላከል ዋነኛው የመረጃ መሠረት ነው። በተለይ የተወለዱ ህፃናት ከህፃናት ሞት ምክንያት ጋር በማያያዝ መረጃውን በሰንጠረዥ ሲቀርብ የእርግዝና ውጤቶችን አስመልክቶ ስለእናቶች ሁኔታ በመግለጽ ትልቁ የመረጃ ግብዓት ይሆናል።

ለ. <u>በቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት በመስጠት፥</u>

የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ዕቅድን፣ አፈፃፀምንና ክትትልን በብቃት ለመዘርጋት በዋናነት የወሊድ ሁኔታ መረጃ በእናቶች ዕድሜ እና በወለዱዋቸው ልጆች ብዛት በቀጣይነትና በቋሚነት በትንሹ የአስተዳደር ዕርከን አልፎም በቤተሰብ ደረጃ ወቅታዊ የመረጃ ግብዓት ይፈልጋል። ከዚህም በላይ ትክክለኛ የጋብቻ ምጥነትና (Marriage Rate) የመጀመሪያ የጋብቻ ዕድሜ በአንድ አካባቢ የወሊድ ሁኔታን የሚያቀያይሩ መንስኤዎችን በማወቅ በኩል ይፈለጋሉ። እነዚህ መረጃዎች የወሊድ መጠንን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የፖሊሲ ጉዳዮችን (Policy issues) ለመለየት አልፎም የቤተሰብ መጠንን ለመመጠን የሚያስችሉ የአሰራር ስልቶችን እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ተቋም ለመዘርጋትና ወቅታዊና ቀጣይ አተገባበር/አፈፃፀም አሠራሮችን ለመፍጠር ያስችላሉ።

ሐ. <u>የጤና ደረጃ ጠቋሚ መለኪያዎችን (Health Status Indicators) ለማዘጋጀት፤</u>

የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ የሞት መጠን መለኪያዎችን ለማስላት የሚያስችሉ መሠረታዊ የመረጃ ግብዓቶችን ያስገኛል። ከዚህም በላይ የህዝብ ጤና አጠባበቅ ፕሮግራሞችንና ምርምሮችን ለማድረግ ምሪትን በመስጠት ይጠቅማል። የዓለም የጤና ድርጅት የአንድን አገር ህዝብ የጤና ደረጃ (health status) ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ የአገሮችን የጤና ደረጃ ንጽጽር ለማድረግ የጨቅላ ህፃናት (ዕድሜአቸው ከአንድ ዓመት በታች) ሞት ምጥነትን (Infant mortility rate)፣ የህይወት ዘመን ግምትን (Life expectancy at birth)፣ ግርድፍ የሞት ምጥነትን (Crude death rate) እና ከ 50 ዓመት ዕድሜ በኋላ የሚቾች ምጥነትን (Proportionate mortality rate at 50 years and over) እንደ ዋና የጤና ሁኔታ (Health Condition) መለኪያ አድርጎ ይጠቀምባቸዋል። እነዚህ መለኪያዎች ትክክለኛውን ምጥነት በማመልከትና በዚያውም መጠን የማስተካከያ እርምጃዎችን ለመውሰድ ግብዓት በመሆን ለማገልገል በሚችሉበት ሁኔታ ለመገኘት ቀጣይ፣ ቋሚና ወቅታዊ መረጃን በሚያስገኝ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ መሰብሰብ አለባቸው። ይኸው የመረጃ ምንጭ ከሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓት የሚገኘው የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ነው። ከጨቅላ የህፃናት ሞት ምጣኔ (Infant mortality rate) በተጨማሪ ድህረ-አዲስ ውልድ (ዕድሜአቸው ከ 4-52 ሳምንት) ሞት ምጥነት (Post-neontal mortality rate) የአካባቢያዊ ተጽእኖ በህዝብ ጤንነት ላይ የሚኖረውን መጠን ጠቋሚ (Index) መረጃ ተደርጎ ይወሰዳል። እነዚህ ድህረ-አዲስ ውልድ ሙተት ምጥነት (Post-neonetal mortality rate) እና አዲስ ውልድ ሙተት ምጥነት (ከአራት ሳምንት በታች) (Neonetal mortality rate) ወሳኝ የህዝብ የጤና ደረጃ ጠቋሚ መረጃዎች በትክክል፣ በቀጣይነት፣ በቋሚነትና በወቅታዊነት እስከ ትንሹ የአስተዳደር ዕርከን ደረጃ ሊገኙ የሚችሉት ከምዝገባ ሥርዓቱ ብቻ ነው። በሌላም በኩል በእያንዳንዱ የጤና ችግር ላይ

ባተኮረ መልኩ በቂ ግንዛቤ ለማግኘትና የበሽታዎች መከላከያ ስልት ለመንደፍ የሚያስችል መረጃ የሚገኘው በሞት ኩነት ሰነድ አማካይነት ከሚሰበሰበው የሞት ምክንያት (Cause of Death) የምዝገባ መረጃ ነው።

መ. <u>ሌሎች የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃ ጥቅሞች፣</u>

በቀጣይነትና በቋሚነት እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን የሚቀርበው የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ መረጃ የህዝብ የጤና አገልግሎት ፕሮግራሞችን በመቅረጽ፣ የተማሪን ብዛትና የመምህራን አቅርቦትን፣ የኤፒደሞሎጂ ጥናቶችን (Epidemiological Studies) ለማድረግ፣ የመኖሪያ ቤቶች ፍላጎትንና የግንባታ ዕቅድን በማዘጋጀት፣ ልዩ ልዩ የፍጆታ ዕቃዎችን ለማምረትና ለገበያ ለማቅረብ (ለምሳሌ መድሃኒት፣ የፋብሪካ ውጤት የሆኑ ሸቀጣ ሸቀጦች፣ በተለይም ለህጻናት ፍጆታ የሚውሉ ቁሳቁሶችን፣ ...) የሚያስችሉ ዕቅዶችን ለማዘጋጀት፣ ...ወዘተ የመረጃ ግብዓት በመሆን ያገለግላል።

### 2.3.3.2 <u>ወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ በጥናትና በምርምር ተግባር</u>

በዚህ ዘርፍ ወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ በሁለት ዋና ዋና መስኮች የጥናትና የምርምር ተግባር ጥቅም ላይ ይውላል።

ሀ. <u>በስነ-ሕዝብ ስታቲስቲክስ ጥናትና ምርምር</u> (Demographic Study and Research)፣

በስነ-ሕዝብ የምርምር ተግባር ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዙት የሕዝብ ብዛት ግምት (Population Estimation)፣ የሕዝብ ብዛት ትንበያ (Population Projection) እና የስነ-ሕዝብ ትንተና ጥናቶች (Analytical Studies) ናቸው። እነዚህ የመረጃ አቅርቦትና የትንተና ሥራዎች በዝቅተኛ የአስተዳደር ዕርከን ደረጃ በቀጣይነትና በቋሚነት ሊቀርቡ የሚችሉት ቀጣይና ቋሚ የወሳኝ ኩነት ስታቲስቲክስ መረጃዎች በሕዝብ የክብር መዝገብ የመረጃ ምንጭ አማካይነት ነው። በተጨማሪም በስነ-ሕዝብ ትንተና ጥናቶች ውስጥ የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ጥልቅ ሂሳባዊ ዲሞግራፊ (Mathematical Demography) እና የህዝብ-ነክ ጥናቶችን (Population Studies) በማድረግ ረገድ ዋነኛ ግብዓት በመሆን ጥቅም ይሰጣል።

ለ. <u>በህክምና ምርምር ዘርፍ</u> (Mdical Research)

ይህ የምርምር ዘርፍ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ በስነ-ሕዝብ የምርምር መስክ ከሚያስገኘው አገልግሎት ጋር በተያያዘ በህክምናው ዘርፍ የህክምና ባለሙያዎች ምርምር የሚያካሂዱበት የሥራ መስክ ነው። በዚህ የምርምር መስክ የወሳኝ ኩነት ስታቲስቲክስ መረጃዎችን በግብዓትነት በመጠቀም በጣም በርካታ የህክምና ውጤቶች ተገኝተዋል።

## 2.4 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሕግ

በአንድ አገር ወይም የአስተዳደር ክልል የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓትን ለማቋቋም ሲታሰብ በቅድሚያ መዘጋጀት ያለበት የአገሪቱን የኢኮኖሚና ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ዕድገት ደረጃ የሚመጥን፤ የሕዝቡን ባህል፣ ሃይማኖትና አኗኗር እንዲሁም ዓለም አቀፍ መርሆዎችን ያገናዘበ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሕግ (Civil Registration Law) ማዘጋጀት ነው። የሕጉ መኖርና መተግበር ግለሰቦች፣ ማህበረሰቡ፣ መንግሥትና ሌሎችም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት መብቶቻቸውን፣ ኃላፊነታቸውንና ግዴታዎቻቸውን አውቀው ህጋዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴ የሚያደርጉበትን ዘመናዊና አግባባዊ የሕዝብ አስተዳደር ሥርዓት ለመፍጠር የሚያስችሉ ወሳኝ መረጃዎችን ለማግኘት ያስችላል። ይህም የምዝገባ ህግ ከአገሪቱ ሕገ-መንግሥት፣ ከተለያዩ ሕጎችና ደንቦች እንዲሁም ከተለያዩ ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎችና ስምምነቶች ጋር የማይጋጭና የማይቃረን መሆን ይኖርበታል።

የምዝገባ ሕጉ የምዝገባውን ዓለም አቀፋዊ የቴክኒክ ምሪት እና አስተዳደራዊ አወቃቀር መሠረቶችን በመንተራስ እንዲሁም የአገሩን የመንግሥት የህግና የአስተዳደር አወቃቀርና የአስፈፃሚ ተቋማትን አደረጃጀት በማገናዘብ በሚዘጋጀው ቴክኒካዊ ጥናት ላይ ተመሠርቶ ይቀረፃል። ለምዝገባው አፈፃፀም የሕጉ አስገዳጅነት፣ የአስፈጻሚ ተቋማቱ ቋሚነትና የአሠራሩ ዘላቂነት ዋና መሠረቶች ናቸው። የምዝገባ ሕጉ መኖር ግለሰቦች፣ ሕብረተሰቡ፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ኃላፊነታቸውንና ግዴታቸውን አውቀው የኩነቶች ምዝገባን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ያስችላል። ሕጉ የምዝገባ አሠራር መመሪያና ማስፈፀሚያ ደንብ በመሆን የምዝገባው ሥርዓት እያደገ፣ እየተሻሻለና በዘመናዊ አሠራር እየተጠናከረ እንዲሄድ ያደርጋል።

በተጨማሪም የምዝገባውን ሥርዓት ለማቋቋም የሚቀረፀው ሕግ የምዝገባውን የተለያዩ የአመዘጋገብ አሠራሮችን፣ የአስፈጻሚ ድርጅቶች አስተዳደራዊ መዋቅርን፣ የምዝገባውን የአፈጻጸም መመሪያ አተገባበር፣ ... ወዘተ ግልጽ በሆነ መንገድ ማብራራትና መተርጎም ይኖርበታል። ሕጉ በአገሪቱ ያለውን የስታቲስቲክስ ሕግ፣ ደንብ፣ አወቃቀርና አስተዳደር ከምዝገባው ጋር የሚኖረውን ቁርኝት ግልጽ አድርጎ ማስቀመጥ ይኖርበታል። እንደዚሁም በምዝገባው አፈጻጸምና በመረጃ አጠቃቀም የተጠቃሚ ግለሰቦችንና ተቋማትን የተሳትፎና የአጠቃቀም ሥርዓት መግለጽ ይኖርበታል።

ከላይ በዋናነት የተገለጹትን የምዝገባ የህግ አቀራረጽ መርሆዎችን መሠረት በማድረግ የሚቀረጸው የኩነቶች ምዝገባ ህግ የሚከተሉትን ዓበይት ጉዳዮች ያካተተ እንዲሆን ይጠበቃል።

1. የሕጉ መደንገግ ያስፈለገበት ምክንያትና ዓላማ መግለጫ፣
2. የሚመዘገቡ ወሳኝ ኩነቶች ዓይነትና ትርጉም፣
3. የወሳኝ ኩነቶችን መከሰት ማስታወቅ፣ ማስመዝገብና መመዝገብ ግዴታ ስለመሆኑ፣

4. የወሳኝ ኩነቶች የምዝገባ የጊዜ ገደብ፣
5. በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቀርቦ አለመመዝገብ/ አለማስመዝገብ የሚያስከትለውን ጉዳትና ቅጣት፣
6. የጠቋሚ፣ የአስመዝጋቢና የመዝጋቢ ኃላፊነትና ተግባር፣
7. የምዝገባው ሥራ አፈጻጸምና አደረጃጀት፣
8. የምዝገባ ዶክመንቶች፣ መዝገቦችና ምስክር ወረቀቶች ቅርጽና ይዘት፣
9. የምዝገባ ዶክመንቶች አጠቃቀም ሥርዓት፣
10. የምዝገባ ዶክሜንቶች አያያዝ፣ አቀማመጥና አስተላለፍ፣
11. የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ አመዘጋገብ፣ አያያዝና አስተላለፍ፣
12. የምዝገባው ሥራ አስተዳደራዊና ድርጅታዊ መዋቅር፣
13. በምዝገባው ሥራ የተሠማሩ ተባባሪ አካላት ኃላፊነትና ተግባር፣
14. የምዝገባው ሥራ በጀት ምንጭና አወጣጥ፣
15. ስለ ምዝገባው ተከታታይነት፣ ቋሚነትና አገር አቀፍ ይዘት እንዲሁም አስገዳጅ ስለመሆኑ፣

## 2.5 <u>የወሳኝ ኩነት ምዝገባና ስታትስቲክስ የአፈጻጸም አደረጃጀት</u>

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባን ለማቋቋም ሲታቀድ በቅድሚያ ሊታሰቡና ቅድመ ዝግጅት ሊደረግባቸው ከሚገቡ ጉዳዮች አንዱና ዋነኛው በአገሪቱ ካለው ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ አወቃቀር ጋር የሚጣጣም የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ድርጅታዊና አስተዳደራዊ መዋቅርን መዘርጋት ነው።

በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ የምትተዳደረው በፌደራላዊ ሥርዓተ-መንግስት ነው። የምዝገባ ሥርዓቱ አስተዳደራዊና ድርጅታዊ አወቃቀር በምዝገባ ህጉ መደንገግ የሚገባው በመሆኑ በፌደራል የመንግሥት አደረጃጀት የወሳኝ ኩነቶች የምዝገባ ህግ አቀራረጽን በመጠኑ መመልከት ተገቢ ይሆናል። በፌደራላዊ የመንግስት አስተዳደር የክልል አስተዳደሮች/መንግስታት በሕገ-መንግስቱ የተቀመጡ ስልጣንና ተግባሮችን መሠረት በማድረግ ህግ ማውጣት ይችላሉ። ይህንኑ መርህ መሠረት በማደረግ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ህገ-መንግስት የክልል መስተዳድሮች የፍትሀ-ብሔር ሕጎችን የማውጣት ስልጣን እንዳሏቸው ተመልክቷል። ምንም እንኳ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ህግ በባህርይው የፍትሀ-ብሔር ህግ አካል እንደሚሆን ቢታሰብም ካለው ብሔራዊ ባህርይና ይዘት አንፃር የፌደራሉ መንግስት የህግ አወጣጡን የሚያስተባብርበት መንገድ ሊኖር እንደሚገባ መገንዘብ ይቻላል። በመሆኑም የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብን ለመፍጠር አልፎም ከብሄራዊና ዓለም አቀፍዊ ይዘቱ አንጻር የህገ-መንግስቱን አንቀጽ 55(6) መርህን በመከተል በፌደራሉ የህግ አውጪ አካል የህግ አቀራረጹ በጥልቀት ሊታይ ይገባዋል። በሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት በተደረገው የግምገማ ጥናት መሠረት በኢትዮጵያ የወሳኝ

ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት አደረጃጀት ያልተማከለ ሊሆን እንደሚገባ ተመልክቷል። በዚህም አደረጃጀት እያንዳንዱ የክልል አስተዳደር የክልሉ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ማዕከል ወይም አስፈጻሚ ይሆናል። በመሆኑም በክልሉ በከተማና ገጠር ቀበሌዎች የሚከናወኑትን የወሳኝ ኩነት ምዝገባዎች የክልሉ መስተዳድር ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ይመራል።

በክልል መስተዳድር የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የሚከናወንበት ትንሹ የአስተዳደር ዕርከን የቀበሌ መስተዳድር ነው። ሆኖም በአገሪቱ ካሉት አብዛኛዎቹ ክልሎች ስፋትና በአብዛኛዎቹ የአገሪቱ ገጠር አካባቢዎች ካለው የትራንስፖርትና የመገናኛ አቅርቦት ችግር አንፃር እየተጠና ከቀበሌ አስተዳደር በላይና በታች ንዑስ የምዝገባ አደረጃጀቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ። በየቀበሌው የሚካሄደውን የምዝገባ ሥራ የሚመሩና የሚያስተባብሩ የምዝገባ የሥራ ክፍሎች በቀበሌ ደረጃ በቀበሌ መስተዳድር ጽ/ቤቶች ሥር እንዲቋቋሙ ይደረጋል። በእያንዳንዱ ቀበሌ የምዝገባውን የዕለት ተዕለት ሥራ የሚያከናውን ቢያንስ አንድ የምዝገባ ሠራተኛ እንዲመደብ ይደረጋል።

በእያንዳንዱ የቀበሌ መስተዳድር ሥር የሚቋቋሙ የኩነቶች ምዝገባ የሥራ ክፍሎች በሌሎች የቀበሌው የአስተዳደር ዘርፎች እየታገዙ የምዝገባውን የዕለት ተዕለት ሥራ የሚያካሂዱ፣ የምስክር ወረቀቶችንና የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ መረጃዎችን ወደ ሚመለከታቸው አካላት ቅጂዎችንና ቅጾችን የሚያስተላልፉ ቢያንስ አንድ መዝጋቢ ይመደባል።

## 2.6 <u>የወሳኝ ኩነቶች አመዘጋገብ ስልቶች</u>

የተለያዩ አገሮች ልምድ እንደሚያሳየው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ በሁለት መንገዶች (ደረጃዎች ማለት ተገቢ ሊሆን ይችላል) ይከናወናል። አንደኛው መንገድ መዝጋቢው ከምዝገባው ጽ/ቤት ሳይንቀሳቀስ ወሳኝ ኩነቱ ከተከሰተበት ቤተሰብ አባላት መካከል ወይም ሌላ በሕግ ኩነቱን የማስመዝገብ ኃላፊነት የተጣለበት ግለሰብ ወይም አካል ኩነቱ እንደተከሰተ በአቅራቢያው ወደሚገኘው የምዝገባ ጽ/ቤት በመሄድ ኩነቱንና ተዛማጅ የሆኑ የሥነ-ሕዝብ፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መረጃዎችን የሚያስመዘግብበት (Passive Registration) መንገድ ነው። በዚህኛው ዘዴ መዝጋቢው ጽ/ቤቱን ከማደራጀት፣ መዛግብቱን አዘጋጅቶ ከመጠበቅና ለሕዝቡ ስለምዝገባው ትምህርታዊ ቅስቀሳ ከመስጠት ያለፈ ተግባር አይጠበቅበትም። ይህ የአመዘጋገብ ዘዴ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ በተሟላ ሽፋን በሚገኝባቸው በኢኮኖሚ የበለፀጉ ሀገሮች በአጠቃላይ የሚሠራበትና የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አግባባዊውና ዘላቂው የአመዘጋገብ ስልት ነው።

ሌላኛው የአመዘጋገብ መንገድ መዝጋቢው በተመደበበት ቀበሌ ክልል በሚኖሩ ቤተሰቦች መካከል ወሳኝ ኩነቶች መከሰታቸውን በተለያዩ ዘዴዎች በመከታተልና ኩነቱ ወደተከሰተበት ቤተሰብ በመሄድ ኩነቱንና ተዛማጅ የሥነ-ሕዝብ፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መረጃዎችን የሚመዘግብበት (Active Registration) መንገድ ነው። ይህ የአመዘጋገብ ስልት የምዝገባ

ባህሉና ልምዱ ባልዳበረባቸው የሶስተኛው ዓለም አገሮች ወይም የምዝገባውን ሥርዓት ለመዘርጋት በጅምር ላይ በሚገኙ ታዳጊ ሀገሮች የምዝገባው ባህልና ልምድ እስከሚዳብር የሚሠራበት የአመዘጋገብ ስልት ነው።

በመጀመሪያው ዘዴ ማለትም በምዝገባ ጽ/ቤት ሆኖ ኩነቶችን በመመዝገብ የአመዘጋገብ ዘዴ ሙሉ የምዝገባ የሽፋን ደረጃ (በቀበሌው አስተዳደር ክልል ውስጥ የተከሰቱ ኩነቶችን በህጉ በተሰጠው የጊዜ ገደብ እንደተከሰቱ ሁሉንም መመዝገብ ደረጃ) ላይ ለመድረስ የሚከተሉት ዋና ዋና ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት ይኖርባቸዋል። እነርሱም፡-

1ኛ/ ግለሰቦች አልፎም ቤተሰቦች ምዝገባው ለግለሰቦች፣ ለማህበረሰቡና ለአገር እንዲያም ሲል በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚያስገኛቸውን ሕጋዊ፣ አስተዳደራዊና ስታቲስቲካዊ ጥቅሞች ተረድተው ወሳኝ ኩነት በቤተሰቡ አባላት መካከል እንደተከሰተ በሕግ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ወደምዝገባ ጽ/ቤት በራስ ተነሳሽነት ሄዶ ለማስመዝገብ የሚችሉበት የዕውቀት ደረጃ ላይ መድረሳቸው የተረጋገጠ እንደሆነ፣

2ኛ/ በሕግ የማስመዝገብ ግዴታ የተጣለባቸው ግለሰቦች/አካላት ወሳኝ ኩነቱ እንደተከሰተ በሕግ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ የማስመዘገብ ግዴታ እንዳለባቸውና ይህንን ግዴታ ያለመወጣት አንድ ግለሰብ በዜግነቱ ሊያገኝ የሚገባውን ግልጋሎት ለማግኘት ችግር እንደሚገጥመው መረዳት ወይም በህግ የሚያስቀጣ ድርጊት መሆኑን በቂ ግንዛቤ ያላቸው እንደሆነ እና፤

3ኛ/ በምዝገባ ከሚገኙ የኩነቶች ማስረጃዎች ውጪ ሌሎች ማስረጃዎች በሕግ ተቀባይነት እንደማይኖራቸው ወይም በህግ ፊት የመረጃነት ደረጃቸው ዝቅ ያለ መሆኑን የሚደነግግ ሕግና አሠራር መኖሩንና ተፈጻሚነቱን ማረጋገጥ የሚያስችል አደረጃጀትና አሠራር መኖሩ የተረጋገጠ ሲሆን ነው።

በዚህ ረገድ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ በገጠር ቀርቶ በከተሞችም አንድ ግለሰብ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ የምስክር ወረቀት ቢኖረው ስለሚያገኘው ጥቅም፣ ባለመያዙ ደግሞ የሚያጣው ጥቅም ስለመኖሩ ያለው የግንዛቤ ደረጃ አናሳ በመሆኑ የተነሳ በምዝገባ ጽ/ቤት ተቀምጦ ተመዝጋቢዎችን ጠብቆ የመመዝገቡ አሠራር ተግባራዊ ሊሆን እንደማይችል ግልጽ ነው። ምክንያቱም ለሕግና ለአስተዳደር አካላትም የሚቀርቡ ግለሰባዊ ማስረጃዎችን በመጠቀሙ በኩል ሌሎች አማራጭ የመረጃ አቅርቦቶች ስላሉ ግለሰቦች ለምዝገባው የሚኖራቸው ተነሳሽነት በጣም ዝቅተኛ ስለሚሆን ነው። በመሆኑም በዚህ ሁኔታ ውስጥ ባለ ህብረተሰብ ግለሰቦች ወደ ምዝገባ ጽ/ቤት በራሳቸው ተነሳሽነት እየቀረቡ ኩነቶችን እንዲያስመዘግቡ በማድረግ የምዝገባ ሽፋኑን በሚፈለገው ደረጃ ከፍ ማድረግ አይቻልም።

በሌላም በኩል ሙሉ ለሙሉ ሁለተኛውን የአመዘጋገብ መንገድ ማለትም ተዘዋዋሪ መዝጋቢዎች በማሰማራት በቀበሌው ውስጥ የተከሰቱ ወሳኝ ኩነቶችን የመመዝገቡን አሠራር መከተል ምዝገባው ከሚጠይቀው የሰው ኃይልና ፋይናንስ ግዙፍነት አንፃር ምዝገባውን ቀጣይና ዘላቂ በማድረግ አዋጭ ባለመሆኑ እንዲሁም አግባባዊው የምዝገባ አፈፃፀም ይህን አሠራር የሚከተል ባለመሆኑ ይህ የአመዘጋገብ መንገድ ወደ አግባባዊው አሠራር ለመሸጋገር ካልሆነ በስተቀር በዘለቄታው ሊከተሉት የሚገባ አሰራር አይደለም።

ስለሆነም በኢትዮጵያ ያለው አማራጭ በበርካታ ታዳጊ ሀገሮች እንደሚደረገው ሁለቱንም ዘዴዎች በማቀናጀት የምዝገባውን ሥራ በመጀመር በሂደት በአስመዝጋቢዎች የራስ ተነሳሽነት የምዝገባ አፈጻጸምን ሙሉ ለሙሉ መተግበር ነው። ይህንንም አሠራር በመከተል የምዝገባውን ሽፋን ከፍ ለማድረግ የሚከተሉትን የምዝገባ አፈጻጸም አሠራሮችን መተግበር ያስፈልጋል።

1ኛ/ በወጣው የምዝገባ ህግ መሠረት በቀበሌ አስተደዳደር ውስጥ በሚቋቋመው የምዝገባ የሥራ ክፍል ኩነቶች እንደተከሰቱ ለመመዝገብ አስፈላጊውን የሰው ኃይልና የማቴሪያል ፍላጎት በማሟላት የምዝገባ ጽ/ቤቱን ማደራጀት፣

2ኛ/ ለምዝገባው ሥራ በሚያመች መልክ ቀበሌውን በምዝገባ ጣቢያዎች በመከፋፈል በእያንዳንዱ ዞን ጠቋሚዎችን (ለምሳሌ የቀበሌው ነዋሪ የሆኑ የሠለጠኑ/ያልሰለጠኑ የልምድ አዋላጆችን፣ የቀበሌ የሐይጂን/ የልማት ኮሚቴ አባላትን፣ የጤና/የልማት ተጠሪዎችን፣ የዕድር ተጠሪዎችን፣ የአገር ሽማግሌዎችን፣ የሃይማኖት መሪዎችን፣ የህግ/የህክምና ባለሙያዎችን፣ መምህራንን፣ ተማሪዎችን፣ ... ወዘተ) በመመደብ በመኖሪያ አቅራቢያቸው ኩነቶች እንደተከሰቱ ኩነቱን ለማስመዝገብ በህግ ኃላፊነት የተሰጠው ግለሰብ ቀርቦ እንዲያስመዘግብ ቀጣይና ቋሚ ትምህርት የሚሰጡ ወይም ለቀበሌው የምዝገባ ጽ/ቤት በቃል ወይም በጽሑፍ ኩነት መከሰቱን እንዲያሳውቁ ለማድረግ የሚያስችል አሠራር መዘርጋት፣

3ኛ/ መዝጋቢው በየሳምንቱ ወይም በየአስራ አምስት ቀኑ በምዝገባ ክልሉ ከቤት ቤት እየተዘዋወረ ቤተሰቦችን በመጎብኘት አስመዝጋቢዎች ያላስመዘገቧቸውን ወይም ጠቋሚዎች ያልደረሱባቸውና ያልተመዘገቡ ኩነቶችን መመዝገብ፣

4ኛ/ ወሳኝ ኩነቶች ከሚከሰቱባቸውና በሥራቸው አጋጣሚ የኩነቶች ምዝገባን ከሚያካሂዱ ሌሎች አካላት ወይም ተቋማት፣ ማለትም የጤና ተቋማት፣ ማረሚያ ቤቶች፣ የአረጋውያን መጦሪያዎች፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ የፍቺ አስፈፃሚ ተቋማት (ፍርድ ቤቶችና የሃይማኖት ተቋማት)፣ ... ወዘተ የምዝገባ ቅጂዎችን እንዲልኩ በማድረግ ወይም እየዞሩ በመሰብሰብ መመዝገብ ናቸው።

## 2.7 የወሳኝ ኩነት መዝገቦች ዓይነትና አቀማመጥ

እያንዳንዱ የቀበሌ የኩነቶች ምዝገባ የሥራ ክፍል አራት ዓይነት መዛግብት ማለትም የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና የፍቺ መዝገቦች ይኖሩታል። እያንዳንዱ መዝገብ በተለያየ ክፍል፣ በተራ ቁጥር ወይም ፊደል ቅደም ተከተል መሠረት ለየብቻው ይዘጋጃል። እነዚህ መዝገቦች በመንግሥት መዝገብ ቤት በጥንቃቄ የሚቀመጡና ኩነቶች በትክክል መከሰታቸውን የሚያረጋግጡ ህጋዊ ወይም ይፋዊ ዋና ሰነዶች ናቸው።

በመዝገቦቹ ውስጥ የጽሑፎች አመዘጋገብ በመዝገቦቹ አደረጃጀት መሠረት በቅጅዎች ጭምር በመመዝገብ መከናወን ይኖርበታል። በሁሉም መዝገቦች እያንዳንዱ ኩነት በአራት ቅጂ እንደሚዘጋጁ ይጠበቃል። በመሆኑም የመጀመሪያው ቅጂ መዝገቡ በተዘጋጀበት የቀበሌ ምዝገባ የሥራ ክፍል ከመዝገቡ ጋር ይቀመጣል። ሁለተኛው ቅጂ ለወረዳው አስተዳደር (ተመጣጣኝ የአስተዳደር እርከን) የህዝብ የክብር መዝገብ መዝገብ ቤት ይላካል። ሶስተኛው ቅጂ ለክልል አስተዳደር የሕዝብ የክብር መዝገብ መዝገብ ቤት ሲላክ፣ አራተኛው ቅጂ ደግሞ ወደ ማዕከላዊ መዝገብ ቤት ይላካል። ሁሉም ቅጅዎች እኩል ዋጋ አላቸው። በቅጅዎች መካከል ልዩነት የኖረ እንደሆነ በማዕከል የሕዝብ የክብር መዝገብ መዝገብ ቤት (Central Archive) ያለው ቅጂ እንደ ኦርጅናል ይወሰዳል። የመጨረሻ የፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲሁም የለውጥ ማስታወሻ (Complementary Notation) ለአስመዝጋቢ፣ ለመዝጋቢና ለሌላ ሦስተኛ ወገን ሕጋዊ የሚሆነው በሕዝብ የክብር መዝገብ ዋና (ኦሪጂናል) ቅጂ ውስጥ ከሰፈረ ብቻ ነው።

## 2.8 በወሳኝ ኩነት መዝገቦች የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነትና አመዘጋገብ

የወሳኝ ኩነት መዝገቦች የተቋቋሙበት ዋነኛ ዓላማ ለግለሰቦችና ለመንግስት ሕጋዊ የሆኑ ግለሰባዊ ማስረጃዎችን ወይም ሰነዶችን ለማስገኘት ነው። ከዚሁ በተጓዳኝ ለአስተዳደርና ለስታቲስቲካዊ ተግባራት የሚውሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ያገለግላሉ። ይህንንም ተግባር ለመፈፀም የሚያስችሉ መሠረታዊና ጠቀሜታ ያላቸው ተብለው የሚታወቁ ሁለት ዓይነት መረጃዎች ይሰበሰባሉ።

መሠረታዊ መረጃዎች የሚባሉት በየትኛውም የአስተዳደር ዕርከን በሚገኙ የወሳኝ ኩነት መዝገቦች ላይ መታየት ያለባቸው የመረጃ ዓይነቶች ናቸው። እነዚህ መረጃዎች የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት ዕድገት በየትኛውም ደረጃ ላይ ቢሆን መዝገቦቹ ውስጥ በግዴታ መካተት ያለባቸው ናቸው። መሠረታዊ መረጃዎች የምዝገባ ሥርዓቱ በትንሹ (Minimum) ሊይዛቸው የሚገቡ ለህግ፣ ለአስተዳደርና ለስታቲስቲክስ ግልጋሎት የሚውሉ የመረጃ ዓይነቶችን በዓለም አቀፍ ደረጃ በዘርፉ ከተሰጡ አስተያየቶች (Recommendations) ጋር ተገናዝበው በየመዝገቦቹ የሚደራጁ የመረጃ ዓይነቶች ናቸው። በሌላ በኩል ጠቀሜታ ያላቸው መረጃዎች በአገሪቱ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገት ደረጃ ላይ በመንተራስ ለምዝገባው ተግባር የሚመደበው

የመንግሥት በጀት፣ የሰው ኃይል አቅምና የመረጃ ፍላጎት እየታየ የሚጨመሩና ለሕግ፣ ለአስተዳደርና ለስታቲስቲክስ አገልግሎት እንዲውሉ የሚሰበሰቡ መረጃዎች ናቸው። አሁን በአገራችን ካለው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ እንዲሁም አጠቃላይ የአስተዳደርና የመሠረተ ልማት አውታሮች የዕድገት ደረጃ አንፃር በልደት፣ በሞት፣ በጋብቻና በፍቺ የክብር መዝገቦች ላይ የሚካተቱ መረጃዎች በአመዛኙ መሠረታዊ መረጃዎች ላይ ያተኮሩ ይሆናሉ።

ይህንኑ መሠረት በማድረግ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻ እና የፍቺ መዝገቦች ይዘት የሚከተሉትን ዋና ዋና ርዕሶች የያዙ ይሆናሉ።

ሀ. <u>የልደት መዝገብ ይዘት</u>

ሀ.1 የምዝገባ አካባቢ መለያ
ሀ.2 ሕፃኑን/ኗን የሚመለከት
ሀ.3 የሕፃኑን/ኗን እናት የሚመለከት
ሀ.4 የሕፃኑን/ኗን አባት የሚመለከት
ሀ.5 አስመዝጋቢን የሚመለከት
ሀ.6 የልደት ኩነት መከሰት ማረጋገጫ
ሀ.7 አስተያየት
ሀ.8 የመዝጋቢ፣ የአስመዝጋቢ፣ የዓይን ምስክሮችና የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም ስም፣ ፊርማ፣ ቀንና የምዝገባ ጽ/ቤቱ ማህተም፣

ለ. <u>የሞት መዝገብ ይዘት</u>

ለ.1 የምዝገባ አካባቢ መለያ
ለ.2 ሟችን የሚመለከት
ለ.3 አስመዝጋቢን የሚመለከት
ለ.4 ለሞት ኩነቱ መከሰት የቀረበ ማረጋገጫ መረጃ
ለ.5 አስተያየት
ለ.6 የመዝጋቢ፣ የአስመዝጋቢ፣ የዓይን ምስክሮችና የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም ስም፣ ፊርማ፣ ቀንና የምዝገባ ጽ/ቤቱ ማህተም፣

ሐ. <u>የጋብቻ መዝገብ ይዘት</u>

ሐ.1 የምዝገባ አካባቢ መለያ
ሐ.2 ጋብቻውን የሚመለከት
ሐ.3 ሙሽራውን የሚመለከት
ሐ.4 ሙሽራዋን የሚመለከት
ሐ.5 ለጋብቻው ኩነት መከሰት የቀረበ ማረጋገጫ መረጃ
ሐ.6 አስተያየት

ሐ.7 የሙሽራው፣ የሙሽሪት፣ የዓይን ምስክሮች ስም፣ ፊርማና ቀን

ሐ.8 የመዝጋቢ፣ የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም ስም፣ ፊርማ፣ ቀንና የምዝገባ ጽ/ቤቱ ማህተም

መ. <u>የፍቺ መዝገብ ይዘት</u>

መ.1 የምዝገባ አካባቢ መለያ

መ.2 ፍቺውን የሚመለከት

መ.3 ባልየውን የሚመለከት

መ.4 ሚስትየዋን የሚመለከት

መ.5 ለፍቺው ኩነት መከሰት ማረጋገጫ የቀረበ መረጃ

መ.6 አስተያየት

መ.7 የባል፣ የሚስትና የዓይን ምስክሮች ስም፣ ፊርማና ቀን

መ.8 የመዝጋቢና የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም ስም፣ ፊርማ፣ ቀንና የምዝገባ ጽ/ቤቱ ማህተም

የመዝገቦቹ ይዘት በምዝገባ ሕጉ የሚዘረዘሩትን ወሳኝ ኩነቶች ብቻ በማካተት የሚዘጋጁ ይሆናሉ። በመዛግብቱ ውስጥ መመዝገብ ያለባቸው መረጃዎችም በምዝገባ ህጉ በአስመዝጋቢነት ስልጣን በተሰጠው ግለሰብ ወይም ተቋም መረጃ ላይ የተመሠረቱ መሆን ይገባቸዋል።

በኩነቶች ምዝገባ ወቅት የሚከተሉት ጥንቃቄዎች መወሰድ አለባቸው።

1. እያንዳንዱ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ የሚካሄደው በማዕከል (በክልሉ) በተዘጋጀው መዝገብና የአመዘጋገብ መመሪያ መሠረት ሊሆን ይገባል፤
2. ኩነቶች ሁሉ መመዝገብ ያለባቸው ለቀበሌ የኩነቶች ምዝገባ የሥራ ክፍል ከማዕከል (ከክልሉ) በተሰጡ መዝገቦች ውስጥ ሊሆን ይገባል፤
3. መረጃዎች በመዝገቡ ነጠላ ቅጾች ላይ በተወሰነላቸው ቦታ በመካከል ክፍት ቦታ ባለመተው ይመዘገባሉ፤
4. ሁሉም የወሳኝ ኩነቶች መዛግብት የሚዘጋጁት በቅጂ ነው። በቅጂዎቹ መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት የሌለ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፤
5. በመዛግብቱ ውስጥ ያልተጻፈበት ቅጠል ወይም ቅጽ መኖር የለበትም። በቅጾቹም ውስጥ በጽሑፎች መካከል ባዶ ቦታ መኖር የለበትም። ይህም ሁኔታ ሲያጋጥም በጽሑፍና በፊርማ ለምን እንደሆነ መገለጽ አለበት፤
6. መዛግብቱ ላይ የተሠራ ስሕተት ካለ ስሕተቱ ታርሞ በስሕተቱ አንፃር ስለተስተካከለው ነገር ትክክለኛነት በፊርማ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፤
7. በተራ ቁጥር 6 መሠረት ማስተካከል ያልተቻለ እንደሆነ ገጹን ሙሉ ለሙሉ መቀየር ያስፈልጋል፤

8. በመዝገቡ ውስጥ የሰፈረውን የኩነት ጽሑፍ ሙሉ ለሙሉ መሠረዝ በሚያስፈልግበት ጊዜ ወረቀቱን በሙሉ ከቀኝ ወደ ግራና ከግራ ወደቀኝ በሚሠመሩ መስመሮችና የተሳሳተ (Void) የሚል ጽሑፍ በማስቀመጥ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፤

9. ጽሑፉ በከፊል የተበላሸ ከሆነ ግን የተበላሹትን ቃላት በአንድ መስመር በመሠረዝ ከበላዩ ትክክለኛውን ቃል ማስፈር ብቻ ይበቃል፤

10. ስሕተቶች በምንም ሁኔታ ቢታረሙ የስሕተቱን መነሻ፣ ዓይነትና ማስተካከል ያስፈለገበትን ምክንያት የሚገልጽ ተጨማሪ ማስታወሻ መጻፍ ያስፈልጋል፤

11. መዝጋቢው ምዝገባውን ካጠናቀቀ በኋላ ለአስመዝጋቢው ያስመዘገበውን እንዲያውቀው ካነበበለት በኋላ እንዲፈርም ያደርጋል፤

12. መዝገቦቹ ላይ ስለሰፈሩት ጽሑፎች ትክክለኛነት መዝጋቢው ስሙን፣ ፊርማውን፣ ቀኑንና የሥራ ኃላፊነቱን በመጨረሻ ላይ ማስቀመጥ አለበት።

## 2.9 የወሳኝ ኩነት ምዝገባ አፈጻጸም

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ በሚከተሉት የጊዜ ገደብ ውስጥ መከናወን አለባቸው።

1. የልደት ኩነት ምዝገባ - ልደቱ በተፈፀመ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ፤
2. የሞት ኩነት ምዝገባ - ሞቱ በተፈፀመ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ፣
3. የጋብቻ ኩነት ምዝገባ - ጋብቻው በተፈፀመ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ፣
4. የፍቺ ኩነት ምዝገባ - ፍቺው በተፈፀመ በአንድ ወር ጊዜ ውሰጥ፣

በዚህም መሠረት የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ በሚከተለው አኳኋን ይፈፀማል፣

1. የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባን እንዲያከናወን በህግ ሥልጣንና ኃላፊነት የተሰጠው መዝጋቢ በምዝገባው ጽ/ቤት ምዝገባ ለማከናወን በተወሰነው የሥራ ሰዓትና የአመዘጋገብ መመሪያ መሠረት ወደ ምዝገባ ክፍሉ የሚመጡ አስመዝጋቢዎች አስፈላጊውን የምዝገባ ፎርማሊቲ እንዲያሟሉ በማድረግ ምዝገባውን ይፈጽማል። በጠቋሚዎች አማካይነት ወይም በቀበሌው በመዘዋወር ያወቃቸውንም ኩነቶች በአመዘጋገብ መመሪያው መሠረት ይመዘግባል፤

2. እንዲያስመዘግብ በሕግ ግዴታ የተጣለበት አስመዝጋቢ ኩነቱ እንደተከሰተ በህጉ በተመለከተው የማስመዝገቢያ የጊዜ ገደብ ውስጥ ወደ ቀበሌ ምዝገባ የሥራ ክፍል በመሄድ የኩነቱን መከሰትና ተዛማጅ መረጃዎችን ያስመዘግባል፤

3. መዝጋቢው የአስመዝጋቢውን ማንነት ለመለየት እንዲያስችለው በቅድሚያ የነዋሪነት መታወቂያ እንዲያሳየው ይጠይቃል። ኩነቱ ከተከሰተበት ግለሰብ ጋር ያለውን ዝምድና ወይም ግንኙነት ያጣራል። ከዚህም በላይ አስመዝገጋቢው በምዝገባ ህጉ ኩነቱን ለማስመዝገብ ስልጣን የተሰጠው መሆኑን ያረጋግጣል፤

4. የሚመዘገበው ኩነት በትክክል ለመከሰቱ የሚያረጋግጥ መረጃ (ለምሳሌ የሐኪም ሰርቲፊኬት ወይም የዓይን ምስክር) አስመዝጋቢው እንዲያቀርብ መዝጋቢው ይጠይቃል። አጠራጣሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ መዝጋቢው እራሱ በቦታው ተገኝቶ ኩነቱ ስለመከሰቱ ያጣራል፤

5. ከቀረበው የማረጋገጫ መረጃና አስመዝጋቢው በሚሰጠው ተጨማሪ መረጃ መሠረት ኩነቱን የሚመለከቱ መረጃዎች ተገቢ በሆነው መዝገብ ውስጥ ይመዘገባሉ።

6. መዝጋቢው ስለኩነቱ የመዘገበውን መረጃ ለአስመዝጋቢ ካነበበና ትክክለኛነቱን በጋራ ካረጋገጡ በኋላ አስመዝጋቢው በመዝገቡ ላይ እንዲፈርም ያደርጋል።

7. መዝጋቢው ኩነቱን በመዝገቡ ላይ መዝግቦ ካጠናቀቀ በኋላ የኩነቱን የምስክር ወረቀት በሁለት ቅጂ በማዘጋጀት፣ የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም በምስክር ወረቀቱ ዋና (ኦርጅናል) እና ቅጂዎች ላይ እንዲፈርም ያደርጋል።

8. በተዘጋጁት የኩነት የምስክር ወረቀቶች ላይ የጽ/ቤቱ ማህተም ከተደረገበት በኋላ ኦሪጅናል የምስክር ወረቀት ለአስመዝጋቢው ወይም ለባለጉዳዩ ሲሰጥ ቅጂው በጽ/ቤቱ እንዲቀመጥ ይደረጋል።

## 2.10 <u>የወሳኝ ኩነቶች መዝጋቢ ተግባርና ሃላፊነት</u>

የወሳኝ ኩነት ክስተቶችን በሕዝብ የክብር መዝገቦች ውስጥ እንዲመዘግብ ሥልጣን የተሰጠው መዝጋቢ ዋነኛ ተግባር ኩነቱን እንዲያስመዘግብ በሕግ ኃላፊነት የተሰጠው አስመዝጋቢ በሚሰጠው መረጃ ላይ በመመሥረት የራሱን ተጨማሪ ማጣሪያ ካደረገ በኋላ ኩነቱንና ከኩነቱ ጋር ተዛማጅ የሆኑ የሥነ-ሕዝብ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መረጃዎችን ለዚህ ተግባር በተዘጋጁ የሕዝብ የክብር መዝገቦችና የወሳኝ ኩነት ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጾች ውስጥ መመዝገብ ነው።

የእነዚህ መረጃዎች በትክክልና በህጉ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ በጥራት መመዝገብ ከኩነቶቹ ሕጋዊ፣ አስተዳደራዊና ስታቲስቲካዊ ጠቀሜታ አንጻር ግንዛቤ አግኝቶ የመረጃዎች አመዘጋገብ ጥንቃቄ የተሞላበት መሆን ይኖርበታል።

በዚህም መሠረት የወሳኝ ኩነቶች መዝጋቢ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች በህግ ተጥለውበታል።

1. የገጠር ወይም የከተማ ቀበሌ መዝጋቢ በቀበሌው ክልል ውስጥ የሚከሰቱ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና የፍቺ ኩነቶችን በምዝገባ ህጉ የማስመዝገብ ኃላፊነት ባለባቸው አስመዝጋቢዎች ጠያቂነት ወይም ለዚህ ተግባር የተመደቡ ጠቋሚዎች በሚያቀርቡለት ሪፖርት ወይም በራሱ ተነሳሽነት የኩነቱን መከሰትና የቀረቡትን መረጃዎች ትክክለኛነት ካጣራ በኋላ ለእያንዳንዱ ኩነት በተዘጋጀው የክብር መዝገብ ውስጥ መረጃዎችን ያሰፍራል። የምዝገባ ዶክመንቶችንም ሚስጥራዊነት ይጠብቃል፤

2. ወሳኝ ኩነቶች ከሚከሰቱባቸውና ከሚሰጡት አገልግሎት ጋር በተያያዘ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት ከሚሰጡ ተቋማት፣ ለምሳሌ የጤና ተቋማት፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ ማረሚያ ቤቶች፣ የጦር ሠፈሮች፣ የአረጋዊያን መጦሪያዎች፣ … ወዘተ ጋር የቅርብ ግንኙነት በማድረግ ኩነቱ በሌላ የምዝገባ ጽ/ቤት ያልተመዘገበ መሆኑን ካጣራ በኋላ ከተቋማቱ በሚያገኛቸው መረጃዎች በመጠቀም ኩነቶቹን ይመዘግባል፤

3. በምዝገባ ሕጉ መሠረት የሲቪል ጋብቻ ሥርዓትን ያስፈጽማል፤

4. በሕግ የኩነቶች መረጃ የማግኘት መብት ላላቸው ባለጉዳዮች የኩነት የምስክር ወረቀት ቅጂ በማዘጋጀት ለሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም ለፊርማ ያቀርባል። የምስክር ወረቀቱ ከተፈረመና የምዝገባ ጽ/ቤት ማህተም ከተደረገበት በኋላ ለባለጉዳዮች መረጃውን ይሰጣል፤

5. የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና የፍቺ ወሳኝ ኩነት መዝገቦችን፣ ቅጾችንና ጥራዞችን በፊደል ተራና በዘመን ቅደም ተከተል አደራጅቶ ለጥበቃ በሚያመች ሁኔታ ጠርዞ በጥንቃቄ ይይዛል። ለመልካም አጠባበቃቸውም ኃላፊነት ይወስዳል፤

6. በማዕከል (ክክልል) ተዘጋጅተው በመጡለት የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና የፍቺ ኩነት የስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጾች ላይ ከመዝገቦች፣ ከአስመዝጋቢዎችና

ከጠቋሚዎች ባገኘው መረጃ መሰረት የወሳኝ ኩነት ስታቲስቲክስ መረጃዎችን በወሳኝ ኩነት ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጾች ላይ ይመዘግባል፤

7. ስለወሳኝ ኩነት ምዝገባ አስፈላጊነት፣ የአስመዝጋቢዎች ግዴታ፣ የወሳኝ ኩነቶች መረጃዎች ጥቅም ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎቸ በተዘጋጀው የትምህርትና ቅስቀሳ መመሪያ መሠረት በቋሚነትና በየተወሰነ ጊዜ ትምህርት ይሰጣል፤

8. ለምዝገባ አስፈላጊ የሆኑ ባዶ መዝገቦችንና መሰል የመረጃ መመዝገቢያ ፎርሞችን ከማዕከል (ከክልል) የምዝገባ ጽ/ቤቶች ወቅቱን ጠብቆ በመጠየቅ ያስመጣል፤ እንዲሁም በቀበሌው የተመዘገቡ ኩነቶች ብዛትን የተመለከተ ሪፖርት ለበላይ ምዝገባ ጽ/ቤት ያቀርባል፤

9. የሞትንና የሟችን ግላዊ የሥነ-ሕዝብ፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ባህርያት በሚመዘግብበት ጊዜ አጠራጣሪ ሁኔታ ካጋጠመው በፖሊስና በፍርድ ቤት ምርመራ እንዲደረግ በማድረግ በሚገኘው መረጃ ላይ ተመሥርቶ ምዝገባውን ያካሂዳል፤

10. በፍ/ቤት ወይም በህግ ስልጣን በተሰጠው ሌላ አካል ሲታዘዝ በልደት፣ በሞት፣ በጋብቻና በፍቺ መዝገቦች፣ ቅጾች፣ ጥራዞችና ምስክር ወረቀቶች ላይ የታዩ ስሕተቶችን ያርማል፤

11. ሟች በሞት የሕዝብ የክብር መዝገብ ከተመዘገበ በኋላ የቀብር የፈቃድ ወረቀት ለሟች ቤተሰብ/ዘመድ/ተቋም ይሰጣል፤

12. ቀደም ባለው ወር የመዘገባቸውን የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና የፍቺ መዝገብ ነጠላ ቅጂዎችን ቀጣዩ ወር በገባ እስከ 10ኛው ቀን ለወረዳ፣ ለክልል እና ለማዕከል የሕዝብ የክብር መዝገብ ቤቶች እና ለሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት ያስተላልፋል።

13. እያንዳንዱ ወሳኝ ኩነትና ከኩነቱ ጋር ተዛማጅ የሆኑ መረጃዎች በሚመዘገቡበት ጊዜ የአስመዝጋቢዎቹን ማንነትና ችሎታ ማረጋገጥ ይኖርበታል። በተጨማሪም የኩነቱን እውነተኛነት፣ ትክክለኛነት እና ሕጋዊነት ካረጋገጠ በኋላ ይመዘግባል። ካልመዘገበ ደግሞ ምክንያቱን ለአስመዝጋቢው በጽሑፍ ይገልጻል።

14. በአስመዝጋቢዎች ተነሳሽነት ወይም በተለያዩ ምክንያቶች ያልተመዘገቡ ኩነቶችን አጣርቶ ለመመዝገብ እንዲቻል በየሳምንቱ በቀበሌው ክልል ባሉ

ቤተሰቦች ቤት ከቤት ወደ ቤት በመዞር ያልተመዘገቡ ኩነቶችን ያጣራል፤ ቅስቀሳዎችንና ትምህርቶችን ይሰጣል፣ ሳይመዘገቡ የቀሩ ኩነቶችን ይመዘግባል።

## 2.11 የወሳኝ ኩነት መዝገቦች እርማት አደራረግ

በወሳኝ ኩነት መዛግብት በመዝጋቢው ተመዝግበውና ትክክለኛነታቸው ተረጋግጦ የምስክር ወረቀት ተዘጋጅቶላቸው፣ በሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም ከተፈረመባቸውና ማህተም ከተደረገባቸው በኋላ በኩነት መዝገብ ቅጽ ላይ እርማት ወይም ማስተካከያ ሊደረግባቸው የሚችለው በፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም ጉዳዩን ለመወሰን በምዝገባ ሕጉ ሥልጣን በተሰጠው አካል ውሳኔ ብቻ ነው። ይህም ያስፈለገበት ምክንያት የመዛግብቱን ህጋዊነት በአግባባቡ ለመጠበቅና ከጥንቃቄ ጉድለት ሊመጡ የሚችሉ ሕገ ወጥ አሠራሮችን ለመከላከል ነው።

በሕዝብ የክብር መዝገብ ቅጽ ላይ እርማት ወይም ማስተካከያ የማድረግ ጥያቄ በጉዳዩ ባለቤት፣ በአሳዳጊዎች ወይም ጠባቂዎች፣ በዘመዶችና በሌሎች በግለሰቡ ሕጋዊ የዘር ሐረግ ተቀረጾች ሊቀርብ ይችላል።

የወሳኝ ኩነት መዝጋቢው የፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም በህግ ስልጣን ከተሰጠው የበላይ አካል ትዕዛዝ ሳይጠብቅ ከዚህ የሚከተሉትን እርማቶች ሊያደርግ ይችላል።

1. ከመዝገብ ወደ ቅጽ ወይም ከመዝገብ ወደ ምስክር ወረቀት ጽሑፍ ሲገለበጥ የተፈጸመ ቀላል (Clerical) ስሕተት ከሆነ ለምሳሌ የመጠሪያ ስም ወይም የትውልድ ቦታ፣ ... ወዘተ የፊደል ግድፈት፣

2. በመዝገቡ ላይ የሠፈረው ጽሑፍ የኩነቱን መከሰት ለማረጋገጥ በማስረጃነት ከቀረቡ መረጃዎች (ጽሑፍ) ጋር ሲመሳከር ስሕተት ሆኖ ከተገኘ፣

3. የተፈጸመው ስሕተት ከግለሰቡ መታወቂያ ጋር ሲተያይ ግለሰቡ የያዘው መታወቂያ ትክክለኛ ሆኖ ሲገኝ፣

4. በአጋጣሚ ማጣራት ሳይደረግ ከተለያዩ ጠቋሚዎች ወይም አስመዝጋቢዎች በደረሱ መረጃዎች መሠረት ለአንድ ኩነት ድጋሚ ጽሑፍ በዚያው በምዝገባ ጽ/ቤት ተዘጋጅቶ ከሆነ አንደኛው ተሠርዞ ሌላኛው ብቻ እንዲቀር የማድረግ፣ በቀሪው ላይም ለወደፊት ለማመሳከር እንዲረዳ ማጣቀሻ ወይም ማመሳከሪያ ከጎኑ በመጻፍ የዕርምት ዕርምጃ የመውሰድ፣

መዝጋቢው በማንኛውም መንገድ ጽሑፉን ለማስተካከል ወይም ለማረም በተገደደ ጊዜ ማስተካከያውን ያደረገበትን ምክንያት በጽሑፍ ማስፈር ግዴታው ነው።

ከዚህ ያለፉ ማስተካከያዎች ወይም እርማቶች ሊደረጉ የሚችሉት በፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም በህጉ ላይ በሚገለፀው መሠረት በሕዝብ የክብር መዝገብ የበላይ ኃላፊዎች ትዕዛዝ ብቻ ነው። በተለይም እርማቱ ሕግ ነክ ጥያቄዎችን የሚያስነሳ የሆነ እንደሆነ ለምሳሌ የልደት ቀን፣ ወርና ዓመተ ምሕረት፣ የስም ለውጥ፣ የአድራሻ፣ ... እርማቱ ሊደረግ የሚችለው በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ብቻ ነው።

## 2. 12 የወሳኝ ኩነት መዝገቦች አያያዝና አቀማመጥ

የወሳኝ ኩነቶች መዝገቦች ኩነቶች በግለሰቦች ላይ መከሰታቸውን ወይም መድረሳቸውን በትክክል የሚያረጋግጡ ሕጋዊ የመንግሥት ቋሚ ሰነዶች ናቸው። ስለሆነም ለሥራ ቅልጥፍናና ለአያያዝ በሚያመች ሁኔታ መዘጋጀትና ማስረጃነታቸው ለረጅም ዘመናት በሚያገለግል አኳኋን በከፍተኛ ጥንቃቄ መያዝና መጠበቅ አለባቸው።

የሕዝብ የክብር መዝገቦች በብትን ወረቀቶች፣ በጥራዝ ወይም በባህር መዝገብ መልክ ሊዘጋጁ ይችላሉ። እያንዳንዳቸው የክብር መዝገብ አዘገጃጀቶች የየራሳቸው ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሏቸው። አሁን በአገራችን በተለይም በገጠሩ ክፍል ካለው ዝቅተኛ የመሠረተ ልማት አውታሮች አቅርቦት አንፃር ብትን ፎርሞችን ከምዝገባው ማዕከል ወደየምዝገባ ቀበሌዎች መላክና መሰብሰብ ከሚጠይቀው ከፍተኛ ጥንቃቄና ከመሳሰሉት ችግሮች አንጻር ብትን ፎርሞችን ከመጠቀም ይልቅ በጥራዝ መጠቀሙ ተመራጭ ነበር። ሆኖም ግን በጥራዝ የተዘጋጁ መረጃዎችን ፎቶ ኮፒ በማድረግ ቅጂዎችን ለማዘጋጀት ወይም በታይፕ ወይም በኮምፒውተር ለመጻፍ አስቸጋሪ ስለሚሆን መዝገቦችን በጥራዝ ማዘጋጀት ለአሰራር አመቺ አይሆንም። በመሆኑም በኢትዮጵያ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ መዝገቦች የሚዘጋጁት በብትን ወረቀት ሆኖ በአንድነት በሚታሰር ማህደር (ፎልደር) ይሆናል። ይህም ሲሆን ብትን የመዝገብ ቅጾቹ በተለያየ ምክንያት እንዳይጠፉ ወይም ከውስጥ ተለይተው እንዳይወጡ ለቅጾቹ አስቀድሞ ተከታታይ ቁጥር መስጠት እንዲሁም ሌሎች የተለዩ የጥንቃቄ የአያያዝ ስልቶችን መጠቀም ያስፈልጋል።

የክብር መዝገቦች አያያዝ ትክክለኛነትና ለሥራ ቅልጥፍና ያላቸው አመቺነት የሚለካው መዝገቦቹ ለሥራ በሚፈለጉበት ጊዜ በሚቀርቡበት ፍጥነት ልክና ደህንነታችውን ለመጠበቅና ለመከላከል ባላቸው አመቺነት ነው። ለዚህም ሲባል እያንዳንዱ ወሳኝ ኩነት የየራሱ መዝገብ እንዲኖረው ይደረጋል። ማለትም ለልደት፣ ለሞት፣ ለጋብቻና ለፍቺ የተለያዩ መዝገቦች ይኖራሉ። በተጨማሪም እያንዳንዱ ወሳኝ ኩነት በአራት ቅጂዎች ይዘጋጃል። ለማጣቀሻነት እንዲያገለግልም ከመዝገቡ ጋር የተያያዙት ቅጠሎች/ ቅጾች በቅደም ተከተል ቁጥር

ይሰጣቸዋል። በእያንዳንዱ ቅጠል/ ቅጾች ውስጥ የአንድ ወሳኝ ኩነት መረጃ ብቻ ይሰፍራል። በምዝገባው የተዘጋጀው አንደኛው ቅጂ በቀበሌው የኩነቶች ምዝገባ ክፍል መዝገብ ቤት ሲቀመጥ ሁለተኛው ቅጂ ወደ ወረዳ (ተመጣጣኝ ወይም አግባብ ወዳለው የአስተዳደር ዕርከን) የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነት መዝገብ ቤት ይላካል፤ ሶስተኛው ቅጂ ደግሞ ወደ ክልል የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነት መዝገብ ቤት ሲላክ አራተኛው ቅጂ ወደ ማዕከል የሕዝብ የክብር መዝገብ ቤት ይላካል። ተደጋግሞ እንደተገለጸው እነዚህ መዝገቦች ላይ የሰፈሩት መረጃዎች አስረጂነት ለዘመናት የሚፈለግ በመሆኑ ዕድሜያቸውን ለማራዘም አስፈላጊዎቹ ጥንቃቄዎች ሁሉ መደረግ አለባቸው። መዝገቦቹ ከወረቀቶቹ ጥራት ማነስና ከአያያዝ ጉድለት የተነሣ ከጥቅም ውጪ እየሆኑ ሊሄዱ ስለሚችሉ ጥራት ባለው ወረቀት መዘጋጀት አለባቸው። እንደዚሁም በእርጥበት፣ በውሃና እሳት ሊበላሹ ስለሚችሉ መዝገብ ቤቶቹ ከእነዚህና ከመሳሰሉት አደጋዎች መጠበቅ አለባቸው።

በተጨማሪም የመዝገብ ቤቶቹ የብርሃንና የአየር ሁኔታ የወሳኝ ኩነቶች መረጃዎችን የቀለም መልቀቅ፣ መደብዘዝ፣ የጽሑፎች መጥፋት፣ ቶሎ ማርጀትንና ብሎም ከጥቅም ውጭ እንዳይሆኑ አስፈላጊው ጥንቃቄ መደረግ አለበት። ከዚህም ሌላ መዝገቦቹ በቀበኛ እንስሳት፣ በበራሪ ነፍሳት፣ በአይጦችና በመሳሰሉት አጥፊ ፍጥረታት ጉዳት እንዳይደርስባቸው በጥንቃቄ በተሠሩ ክፍሎች ውስጥ መቀመጥ አለባቸው።

# ምዕራፍ ሶስት

# የወሳኝ ኩነቶች መረጃ አመዘጋገብ

## 3.1 የልደት ወሳኝ ኩነት መረጃ አመዘጋገብ

በልደት መዝገብ ውስጥ የሚሠፍሩት መረጃዎች ከዚህ በታች የተመለከተውን የአመዘጋገብ መመሪያ መሠረት በማድረግ ይመዘገባሉ። የወሳኝ ኩነቶች መዝጋቢ ከአስመዝጋቢዎች የመጡለትን ልደቶች፣ በጠቋሚዎችም ሆነ በራስ አነሳሽነት ያወቃቸውን ልደቶች ይመዘግባል።

የልደት ኩነት ቀዳሚ የማስመዝገብ ግዴታ የተጣለባቸው ከወላጅ እናት ወይም አባት አንዳቸው ናቸው። ሆኖም ወላጅ እናት ወይም ወላጅ አባት በሞት ወይም በከፍተኛ የጤና ችግር/ ህመም ምክንያት ወይም በአካባቢው ባለመኖር ምክንያት ወይም ባለመታወቅ የልደት ኩነቱን ማስመዝገብ ካልቻሉ ሌላ የቅርብ ዘመድ ወይም በቤት ውስጥ ነዋሪ የሆነ ማናቸውም ሰው ወይም ልደቱ ስለመከሰቱ ያወቀ ጐረቤት የማስታወቅና የማስመዝገብ ግዴታ አለበት። በመሆኑም በልደት መዝገቡ የሚመዘገቡ መረጃዎችን መዝጋቢው ከታች የተሰጡትን አጠቃላይ መመሪያዎች መሠረት በማድረግና ህጉን በመከተል በትክክል መመዝገብ ይጠበቅበታል።

በዚህ ረገድ በተለይም ፦

1ኛ/ በቤት ውስጥ የተከሰቱ ልደቶችን የህፃኑ/ኗ እናት/አባት፣ እናት/አባት ከሌሉ የህፃኑ የቅርብ ዘመድ ወይም አሳዳጊ የልደቱን መከሰት የህፃኑ/ኗ እናት በመደበኛነት በምትኖርበት ቀበሌ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ የሥራ ክፍል በመገኘት ልደቱን በህግ በተወሰነው የጊዜ ገደብ የማስመዝገብ ግዴታ አለባቸው። በተመሳሳይም በቤት ውስጥ የተፈፀመን ወሊድ ያዋለዱ የልምድ/የሰለጠኑ አዋላጅ ልደት ስለመከሰቱ ለቀበሌ የወሳኝ ኩነቶች መዝጋቢ ጥቆማ የማድረግ ግዴታ አለባቸው።

2ኛ/ በማናቸውም የጤና ተቋም ወሊድ ሲከሰት ወሊዱን ያከናወነው ሐኪም የወሊድ የሜዲካል የምስክር ወረቀት እንዲዘጋጅ በማድረግና የህክምና ተቋሙን ማህተም በማስፈር የህክምና ተቋሙ የበላይ ሃላፊ ተቋሙ ለሚገኝበት የቀበሌ የሕዝብ የክብር መዝገብ የሥራ ክፍል የሜዲካል የምስክር ወረቀት ቅጂ የመላክ ግዴታ አለበት። በተመሳሳይም በህክምና ተቋሙ የተሰጠውን የልደት የሜዲካል ምስክር ወረቀት በመያዝ የህፃኑ/ኗ እናት/አባት፣ እናት/አባት ከሌሉ የህፃኑ የቅርብ ዘመድ ወይም

አሳዳጊ፣ የህፃኑ/ኗ እናት በመደበኛነት በምትኖርበት ቀበሌ የሕዝብ የክብር መዝገብ የሥራ ክፍል በመገኘት ልደቱን የማስመዝገብ ግዴታ አለባቸው።

3ኛ/ ወድቆ የተገኘ ወይም ወላጁ ያልታወቀ ህፃን ተገቢው የህግ አካል ማለትም ፖሊስ እንዲያውቀው ከተደረገ በኋላ ጉዳዩን የሚከታተለው የፖሊስ ባልደረባ ህፃኑ/ኗን የፖሊስ ጣቢያው ለሚገኝበት የቀበሌ የሕዝብ የክብር መዝገብ ምዝገባ የሥራ ክፍል በመሄድ የማስመዝገብ ግዴታ አለበት።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች በማጤንና በምዝገባ ህጉ በዝርዝር የሚደነገጉትን የአመዘጋገብ ሥርዓቶች ተከትሎ መዝጋቢው በልደት የክብር መዝገቡ የተመለከቱትን መረጃዎች ይመዘግባል። መዝጋቢው እና አስመዝጋቢው በጋራ እና በተናጠል በመዝገቡ ላይ ላሰፈሩዋቸው በተለይም ስለ ልደቱ መከሰት ለሚመለከቱት መረጃዎች ትክክለኛነት በህግ ተጠያቂ ናቸው።

## ክፍል 1. <u>የምዝገባ አካባቢ መለያ</u>

በዚህ ክፍል ልደቱ የተመዘገበበት የቀበሌ መስተዳድር የሕዝብ የክብር መዝገብ የሥራ ክፍል የሚገኝበት ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ እና ቀበሌ ስም ወይም ቁጥር እና የምዝገባ የሥራ ክፍሉ የሚገኝበት ቤት የቤት ቁጥር ወይም በገጠር የመንደሩ ልዩ ስም ይመዘገባል።

### 1.1 <u>የክልል ስም</u>

"የክልል ስም" በሚለው ክፍት ቦታ የልደት ምዝገባው የሚካሄድበት ቀበሌ የሚገኝበት ክልል ስም ይመዘገባል።

### 1.2 <u>የዞን ስም</u>

"የዞን ስም " በሚለው ክፍት ቦታ የልደት ምዝገባው የሚካሄድበት ቀበሌ የሚገኝበት ዞን ስም ይመዘገባል።

### 1.3 <u>የወረዳ ስም</u>

"የወረዳ ስም" በሚለው ክፍት ቦታ የልደት ምዝገባው የሚካሄድበት ቀበሌ የሚገኝበት ወረዳ ስም ይመዘገባል።

### 1.4 <u>የከተማ ስም</u>

ምዝገባው የሚካሄድበት ቀበሌ የሚገኘው በከተማ ሥር ከሆነ በተሰጠው ክፍት ቦታ "የከተማው ስም" ይመዘገባል።

1.5 <u>የከተማ ቀበሌ ስም ወይም ቁጥር</u>

ምዝገባው የሚካሄድበት የከተማ ቀበሌ መስተዳድር ጽ/ቤት ስም ወይም ቁጥር ይመዘገባል።

1.6 <u>የገጠር ቀበሌ (ገ/ማህበር) ስም ወይም ቁጥር</u>

ምዝገባው የሚካሄድበት ቀበሌ የሚገኘው በገጠር ከሆነ የገጠር ቀበሌው ስም ወይም ቁጥር በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል።

1.7 <u>የምዝገባ ጽ/ቤት የቤት ቁጥር (በከተማ)</u>

የቀበሌው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የሥራ ክፍል የሚገኝበት ቤት የቤት ቁጥር ይመዘገባል። በከተማ ቤቱ የሚለየው ለቤቱ የቀበሌው መስተዳድር በሰጠው የቤት ቁጥር አማካይነት ነው። በዚሁም መሠረት ቀበሌው ለቤቶች ሥርዓትን ተከትሎ የቤት ቁጥር እንዲሰጥ "በሚያዘው መመሪያ" መሠረት የምዝገባ የሥራ ክፍሉ ለሚገኝበት ጽ/ቤት የተሰጠው የቤት ቁጥር ይመዘገባል። ቤቱ ንዑስ ቁጥር ወይም ፊደል ካለው ከቤቱ ቁጥር ጋር አብሮ ይመዘገባል።

1.8 <u>የምዝገባ ጽ/ቤት የሚገኝበት የመንደር ልዩ ስም እና የቤት ቁጥር (በገጠር)</u>

በገጠር መኖሪያ ቤቶችም ሆኑ የድርጅት ቤቶች የመለያ የቤት ቁጥር ላይሰጣቸው ይችላል። ሆኖም የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባን በማከናወን ቤተሰቦችን ለመለየትና አድራሻቸውን ለማወቅ አልፎም የምዝገባ ጽ/ቤቶችን ለመለየት ለቤቶች ሥርዓትን የተከተለ የቤት ቁጥር መስጠት አስፈላጊ ነው። ስለሆነም ቤቶችን በሥርዓት የቤት ቁጥር የመስጠት አሰራርን በገጠር ቀበሌዎች ማስፈንን የምዝገባው አንድ አካል አድርጎ መውሰድ ያስፈልጋል። በዚሁም መሠረት ቀበሌው ለቤቶች ሥርዓትን ተከትሎ የቤት ቁጥር እንዲሰጥ "በሚያዘው መመሪያ" መሠረት የምዝገባ የሥራ ክፍሉ ለሚገኝበት ጽ/ቤት የተሰጠው የቤት ቁጥር እና የመንደሩ ልዩ ስም ይመዘገባል።

ክፍል 2 <u>ሕጻኑን/ኗን የሚመለከት</u>

በዚህ ክፍል በህይወት የተወለደውን/ችውን ሕጻን የሚመለከቱ መረጃዎች አስመዝጋቢውን በመጠየቅና ከተለያዩ ተቋማት የተሰጡ መረጃዎችን በመመርመር ይመዘገባሉ።

2.1 <u>የህፃኑ/ኗ ሙሉ ስም ከነአያት</u>

ለሕጻኑ/ኗ የተሰጠው ሙሉ ስም በተዘጋጀው ክፍት ቦታ ይመዘገባል። በዚሁም መሠረት የሕጻኑ/ኗ ስም ከመመዝገቡ በፊት የሚከተሉት መሟላት አለባቸው።

1ኛ/ በአገሪቱ የፍትሀ-ብሔር ሕግና በአካባቢው ባህል መሠረት የተሰጠ ስም ስለመሆኑ፣
2ኛ/ የሕጻኑ/ኗ ወላጆች በጋራ ወይም ከሁለቱ በአንዳቸው ወይም በአሳዳጊ የተሰጠ ስለመሆኑ፣
3ኛ/ የተሰጠው ስም የሕዝብን ሥነ-ምግባር የማይነካና ክብረ-ነክ ያልሆነ ስለመሆኑ፣

4ኛ/ በተለያዩ ምክንያቶች ለሕጻኑ/ኗ ስም መሰየም ያልተቻለ እንደሆነ ለወንዱ "ማሞ"፣ ለሴቷ ደግሞ "ማሚቱ" የሚል ጊዜያዊ ስም በመዝገቡ ውስጥ ለጊዜው ሊሰፍር ይችላል። ሆኖም ለዘለቄታው ለህፃኑ/ኗ የወጣለት/ላት ስም ምዝገባው በተፈፀመ ጥቂት ቀናት ውስጥ አስመዝጋቢው በምዝገባ ክፍሉ በመቅረብ ማስመዝገብ አለበት።

ከላይ የተሰጡትን ማስታወሻዎች መሠረት በማድረግ የህፃኑ/ኗ ስም አፃፃፍ የግል ስም፣ የአባትና የአያት ስምን ጨምሮ መመዝገብ ይኖርበታል። ይህንኑም መሠረት በማድረግ ለምሳሌ ለአንድ ህፃን የተሰጠው የግል ስም "ደጀኔ" ከሆነና፣ የህፃኑ አባት ስም ደግሞ "መንገሻ"፣ እንዲሁም የህፃኑ አያት ስም "ሰይፉ" ከሆነ የህፃኑ ሙሉ ስም "ደጀኔ መንገሻ ሰይፉ" በማለት መመዝገብ ይኖርበታል።

2.2 <u>የህፃኑ/ኗ ፆታ</u>

የህፃኑ/ኗ ፆታ ተለይቶ ወንድ ለሆኑት "ወንድ" በማለት ሴት ለሆኑት ደግሞ "ሴት" በማለት በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል።

2.3 <u>ህፃኑ/ኗ የተወለደበት/ችበት ቀን</u>

ሕፃኑ/ኗ የተወለደበት/ችበት ቀን፣ ወር እና ዓመተ ምህረት በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል። በዚሁም መሠረት ለምሳሌ አንድ ህፃን የተወለደው በመስከረም ወር በ5ኛው ቀን 1997 ዓ.ም ከሆነ ቀን በሚለው ክፍት ቦታ "05"፣ ወር በሚለው ክፍት ቦታ "መስከረም" እንዲሁም ዓመተ ምህረት በሚለው ክፍት ቦታ "1997" ይመዘገባል።

2.4 <u>ህፃኑ/ኗ የተወለደበት/ችበት ስፍራ (ተቋም)</u>

ሕፃኑ/ኗ የተወለደበት/ችበት ስፍራ በጤና ተቋም ወይም በቤት ውስጥ መሆኑን አስመዝጋቢው ተጠይቆ ወይም ከልዩ ልዩ ተቋማት የተሰጡ መረጃዎችን በመመርመር ስፍራው ወይም የተቋሙ ስም ይመዘገባል። ህፃኑ/ኗ የተወለደው/ችው በጤና ተቋም ውስጥ የሆነ እንደሆነ የተቋሙን ደረጃና ይዞታ በሚገልፅ አኳኋን መልሱ ይመዘገባል። ለምሳሌ የመንግስት ሆስፒታል፣ የመንግስት ጤና ጣቢያ፣ የግል ጤና ኬላ፣ የግል ክሊኒክ፣ ... ወዘተ በማለት በመግለጽ መመዝገብ አለበት። ህፃኑ/ኗ የተወለደው/ችው ከጤና ተቋም ውጪ እቤት ውስጥ ከሆነ "በቤት ውስጥ" ተብሎ ይመዘገባል። የልደቱን ስፍራ ለመመዝገብ ይረዳ ዘንድ ከታች የቦታዎችና ተቋማት አፃፃፍ ዝርዝር ቀርቧል።

- የመንግስት ሆስፒታል
- የመንግስት ጤና ጣቢያ
- የመንግስት ክሊኒክ
- የመንግስት ጤና ኬላ
- የግል ሆስፒታል

- የግል ጤና ጣቢያ
- የግል ክሊኒክ
- መንግስታዊ ያልሆነ የዕርዳታ ሰጪ ድርጅት የጤና ተቋም
- በቤት ውስጥ
- በመንገድ ላይ (ጫካ ውስጥ፣ ጉድጓድ፣...ወዘተ ያጠቃልላል)
- በማረሚያ ቤት /ሕፃናት ማሳደጊያ/ የጦር ካምፕ/ ማገገሚያ ... ወዘተ

2.5 <u>ልደቱ የተከሰተበት ቦታ</u>

ህፃኑ/ኗ የተወለደበት/ችበት ቦታ የሚገኝበት ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ከተማ፣ እና ቀበሌ ስም ወይም ቁጥር በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ይመዘገባሉ። ይኸውም ሕፃኑ/ኗ የተወለደው/ችው በሆስፒታል ወይም በጤና ጣቢያ ከሆነ ሆስፒታሉ ወይንም ጤና ጣቢያው የሚገኝበት ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ እና ቀበሌ ስም ይመዘገባል። ሕፃኑ/ኗ የተወለደው/ችው በቤት ውስጥ ከሆነ የተወለደበት/ችበት ቤት የሚገኝበት ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ከተማ እና ቀበሌ ስም እንዲሁም የቤት ቁጥር፣ በገጠር ከሆነ ደግሞ የመንደሩ ልዩ ስምና የቤት ቁጥር ይመዘገባል።

2.6 <u>በልደት ጊዜ የተደረገ እርዳታ</u>

እናትየው ልጁን የወለደችው እቤት ውስጥ ከሆነ እገዛ ያገኘችው ከሠለጠነ/ች የልምድ አዋላጅ ወይም ካልሠለጠነ/ች የልምድ አዋላጅ ወይም ምንም ዕውቀት ከሌለው/ላት ሴት ወይም ሌላ መሆኑ ይጠየቃል። በሌላ በኩል እናትየው የወለደችው በጤና ተቋም የሆነ እንደሆነ የጤና ተቋሙ በሰጠው የሜዲካል ሰርቲፊኬት ላይ በመመሥረት ዕርዳታ የሰጠው ባለሙያ የሙያ ደረጃ ይመዘገባል። ማንኛውም የጤና ተቋም በተቋሙ ለተከሰተ የወሊድ ኩነት የሜዲካል የምስክር ወረቀት ወዲያው ለእናትየው/ለአባትየው፤ እነዚህ ከሌሉም ለተወለደው ህፃን አሳዳጊ የመስጠት ግዴታ እንዳለበት እንደሚደነገግ ይጠበቃል። ከዚህም በተጨማሪ የህክምና ተቋሙ ለሚገኝበት የቀበሌ የሕዝብ የክብር መዝገብ የሥራ ክፍል የሜዲካል የምስክር ወረቀት ቅጂ መላክ እንዳለበት ተገልፆ ይገኛል።

2.7 <u>የልደት ምዝገባ መለያ ቁጥር</u>

የሕጻኑ/ኗ ልደት በተመዘገበበት ቅደም ተከተል መሠረት የተሰጠው የልደት ምዝገባ መለያ ቁጥር ይመዘገባል። መዝ.ጋቢ.ው በዓመቱ መጀመሪያ ምዝገባ በሚጀመርበት ጊዜ በልደት የክብር መዝገቡ በመጀመሪያ ለመዘገበው የልደት ኩነት "0001" በሚል ተራ ቁጥር ጀምሮ ሌሎችንም ልደቶች በቅደም ተከተል "002"፣ "0003"፣ ... ወዘተ ተራ ቁጥር እየሰጠ ይመዘግባል። ከዚህ ቁጥር በኋላ ልደቱ የተከሰተበትን ዓመት ሊያመለክት በሚችል መልኩ ልደቱ የተከሰተበት ዓመተ ምህረት ተከትሎ ይመዘገባል። በመሆኑም ለምሳሌ በ1997 ዓ.ም በቀበሌው በመጀመሪያ ለተመዘገበው ልደት "0001 - 97"፣ ለሁለተኛው ልደት "0002-97"፣ ለሶስተኛ ልደት "0003-97"፣ ...ወዘተ በማለት የልደት የምዝገባ መለያ ቁጥር በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል።

## 2.8 ልደቱ የተመዘገበበት ቀን

የሕጻኑ/ኗ ልደት በልደት የክብር መዝገብ የተመዘገበበት ቀን፣ ወርና ዓ.ም በቅደም ተከተል በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። በዚሁም መሠረት ለምሳሌ አንድ ህፃን ተወልዶ የተመዘገበው በጥቅምት ወር በ10ኛው ቀን 1997 ዓ.ም ከሆነ ቀን በሚለው ሥር "10"፣ ወር በሚለው ሥር "ጥቅምት"፣ እንዲሁም ዓመተ ምህረት በሚለው ሥር "1997" በማለት ይመዘገባል።

## 2.9 የልደቱ ዓይነት

ሕፃኑ/ኗ በህይወት የተወለደው/ችው ለብቻው/ዋ ከሆነ የልደቱ ዓይነት በተሰጠው ክፍት ቦታ "ነጠላ" ተብሎ ይመዘገባል። ሕፃኑ/ኗ የተወለደው/ችው ከሌላ ህፃን ጋር ከሆነ በተሰጠው ክፍት ቦታ "መንታ" ተብሎ ይመዘገባል። እንዲሁም ህፃኑ/ኗ የተወለደው/ችው ከአንድ በላይ ከሆኑ ህፃናት ጋር ከሆነ በተሰጠው ክፍት ቦታ የህፃናቱ ብዛት ተጠቅሶ ይመዘገባል። ለአመዘጋገብ እንዲረዳ ከታች የልደት አይነት ዝርዝሮች ቀርቧል።

- ነጠላ
- መንታ
- ሶስት
- . . .

ከአንድ በላይ በህይወት ለተወለዱ ህፃናት ለእያንዳንዳቸው የተናጠል የልደት መዝገብ ቅጽ ሊዘጋጅላቸው ይገባል።

## 2.10 በልደት ጊዜ የሕጻኑ/ኗ ክብደት /በግራም/

ሕፃኑ/ኗ በጤና ተቋም የተወለደ/ች ከሆነ ሕጻኑ/ኗ ከእናቱ/ቷ ማህፀን እንደወጣ/ች ተመዝኖ የተገኘው ክብደት ከጤና ተቋሙ በተገኘው መረጃ መሠረት ወደ መዝገቡ ቅጽ ይገለበጣል። አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ በተለይም በገጠሩ ክፍል ባለው ተጨባጭ ሁኔታ አብዛኛው ልደት የሚከሰተው/የሚፈፀመው በመኖሪያ ቤት ውስጥ ነው። በዚህም ምክንያት በሕይወት የተወለዱ ሕፃናትን ክብደት እንደተወለዱ መለካት ያስቸግራል። መረጃው ለጤናው ዘርፍ ካለው ከፍተኛ ጠቀሜታ አንፃር የቀበሌው ጤና ተጠሪ ልደቱ በተከሰተ እስከ ሶስት ቀናት ባለ ጊዜ ውስጥ ወደ እናትየው መኖሪያ ቤት በመሄድ የሕፃኑን/ኗን ክብደት እንዲመዝን ማድረግ ያስፈልጋል። ቀበሌው የጤና ተጠሪ የሌለው ከሆነ የአጎራባች/ አቅራቢያ ጤና ተቋም፣ የጤና ባለሙያ ወይም ለዚህ ሲባል በምዝገባ የሥራ ክፍሉ በተዘጋጀው አሠራር መሠረት የተገኘውን የህፃኑን/ኗን ክብደት በተሰጠው ክፍት ቦታ በግራም ይመዘገባል።

## 2.11 ልደቱ የተከሰተው በጋብቻ ውስጥ ወይስ ከጋብቻ ውጪ

መዝጋቢው ልደቱን የሚያስመዘግበውን ሰው ሕፃኑ/ኗ በተፀነሰበት/ችበት ጊዜ ወይም በተወለደበት/ችበት ጊዜ ወላጆቹ/ቿ በጋብቻ ተሳስረው የነበሩ መሆን አለመሆናቸውን ጠይቆ፣

በጋብቻ የነበሩ ከሆነ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ "በጋብቻ ውስጥ" ተብሎ ሲመዘገብ በአንፃሩ ከጋብቻ ውጪ ከሆነ ደግሞ "ከጋብቻ ውጪ" በማለት ይመዘገባል። በመረጃው አመዘጋገብ አጠራጣሪ ሁኔታዎች ከተከሰቱ የጋብቻ ወይም የፍቺ ማስረጃዎችን በማየት ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

## ክፍል 3 የሕጻኑን/ኗን እናት የሚመለከት

በዚህ ክፍል የሕጻኑን/ኗን ወላጅ እናት የሚመለከቱ ጥያቄዎች አስመዝጋቢው በሚሰጠው መልስና መዝጋቢው በተከታታይ በሚያደርገው ማጣራት መሠረት ይመዘገባል። በመሠረቱ እናትየውን የሚመለከቱ ግለሰባዊ የማንነት መረጃዎች መገኘት የነበረባቸው ለእናትየው ከተዘጋጀ የልደት፣ የጋብቻ ወይም የፍቺ የምስክር ወረቀት መሆን ነበረበት። ሆኖም በአገራችን የሕዝብ የክብር መዝገብ አመዘጋገብ ሥርዓት ቀደም ብሎ የተጀመረ ባለመሆኑ ህጋዊ የኩነቶች የምስክር ወረቀቶች ማቅረብ ያስቸግራል። በመሆኑም የመረጃዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ደጋፊ ማስረጃዎችን መጠየቅና በአስመዝጋቢው የተሰጡ መልሶች ትክክለኛነታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

### 3.1 የእናት ሙሉ ስም

የሕጻኑ/ኗ ወላጅ እናት የግል ስም፣ የአባት ስምና የአያት ስም በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባሉ። የወላጅ እናት የግል የመለያ ስም ሊወሰድ ይገባ የነበረው እናትየው ሲወለዱ ከተመዘገበ የልደት የምስክር ወረቀት ላይ ነበር። ሆኖም ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው እስከ ተወሰኑ ዓመታት በአግባባዊው አሠራር የተዘጋጁ የኩነቶች የምስክር ወረቀቶች የሚኖሩ ባለመሆኑ ያለው አማራጭ በወቅቱ እናትየዋ በቀበሌ መስተዳድር ጽ/ቤት በሚሰጠው የመኖሪያ መታወቂያ ወረቀት ላይ የተጠቀሰውን ስም ወስዶ መመዝገብ ነው። ይህም ሲሆን በቀበሌ የነዋሪነት መታወቂያ የተገለፀው መለያ ስም ትክክል ለመሆኑ ወይም አጠራጣሪ ያለመሆኑን መዝጋቢው ማረጋገጥ አለበት።

### 3.2 የእናት ዕድሜ (በዚህ ልደት ወቅት)

የሕጻኑ/ኗ እናት ሕጻኑን/ኗን በወለደችበት ጊዜ ዕድሜዋ ተጠይቆ ትክክለኛው ዕድሜ በሙሉ ዓመት (በጨረሰችው ዓመት) በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። የማንኛውም ሰው ትክክለኛ ዕድሜ የማወቂያ ብቸኛው መንገድ ግለሰቡ በተወለደበት ጊዜ በኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ከተያዘ የትውልድ ቀን መረጃ ማግኘት ከተቻለ ነው። ይህ ከሆነ ዕድሜው ከተፈለገበት ቀን ላይ የተወለደበትን ቀን በማቀናነስ ትክክለኛ የዕድሜ መረጃ ማግኘት ይቻላል። በኩነቶች ምዝገባ አማካይነት የልደት የምስክር ወረቀት ለሌላቸው ግለሰቦች የተወለዱበትን ትክክለኛ ጊዜ ጠይቆና እንዲያስታውሱ በማድረግ ዕድሜአቸውን ማግኘት ያስፈልጋል። በዚህ መንገድ የሚገኘው የዕድሜ መረጃ ትክክለኛነት በግለሰቡ የልደት ቀንና በጽሁፍ የማስቀመጥ ልምድና ማስታወስ ችሎታ ላይ ይመሠረታል። ዕድሜ በሙሉ ዓመት ማለት ከሙሉ ዓመት በተጨማሪ

ያሉትን ወሮችንና ቀኖችን በመተው ዓመቱን ብቻ በመውሰድ ዕድሜውን መመዝገብ ነው። ለምሳሌ እናትየው ህፃኑን/ኗን በወለደችበት ቀን ዕድሜዋ 20 ዓመት ከ6 ወራትና ከ29 ቀናት ከሆነ መመዝገብ ያለበት 20 ዓመት ብቻ ነው።

ዕድሜዋን በትክክል ለማታውቅ እናት በተወለደችበት ጊዜ/አካባቢ በብሔራዊ ደረጃ ወይም በምትኖርበት አካባቢ የተፈጸሙ ታሪካዊ ድርጊቶች እንዳሉና እናትየዋ ድርጊቱ በተፈጸመበት ጊዜ ዕድሜዋ ስንት እንደነበረ ወይም ከድርጊቱ በኋላ/በፊት ምን ያህል ጊዜ ቆይታ እንደተወለደች አስመዝጋቢውን በመጠየቅና ዕድሜዋን በማስላት ገምቶ መመዝገብ ያስፈልጋል።

ከዚህም ሌላ አስመዝጋቢው የአንዳንድ የቤተሰቡን አባላት ወይም የአካባቢ ነዋሪዎች ዕድሜ በትክክል ሊያውቅ ከቻለ ከነዚህ ግለሰቦች ዕድሜ ጋር በማነጻጸር የእናትየዋን ዕድሜ መገመት ይቻላል። በተጨማሪም እናትየው ባገባችበት ጊዜ የነበራትን ዕድሜና ልጇን እስከወለደችበት ጊዜ ያለውን ዘመን በመደመር ልጇን/ልጅቷን በወለደችበት ጊዜ የነበራትን ዕድሜ መገመት ይቻላል።

### 3.3 <u>የእናት ብሔረሰብ</u>

የእናትየው ብሔረሰብ ስም ተጠይቆ ይመዘገባል። አስመዝጋቢው የብሔረሰብን ትርጉም በትክክል እንዲረዳ ትውልድ፣ ነገድ፣ ዘር፣ ጎሳ፣ ...ወዘተ በማለት ማብራራት ሊያስፈልግ ይችላል። የዋና ዋና እና የቅርንጫፍ ብሔረሰቦች ስም ዝርዝር በዕዝል 1 ቀርቧል።

### 3.4 <u>የእናት መደበኛ መኖሪያ ቦታ</u>

ህፃኑን/ኗን በወለደችበት ጊዜ የእናትየው መደበኛ መኖሪያ ቦታ የት እንደነበር ተጠይቆ ክልሉ፣ ዞኑ፣ ወረዳው፣ ከተማው፣ ቀበሌው፣ የቤት ቁጥሩ እንዲሁም የቤት ቁጥር በሌለበት የገጠር ቀበሌ እናትየው የምትኖርበት መንደር ልዩ ስም በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባሉ። የአንድን ሰው መደበኛ መኖሪያ ቦታ ለመለየት በዚህ መመሪያ ለጽንሰ-ሃሳቦች ትርጉምና ማብራሪያ የተሰጠውን መመልከት ይገባል።

### 3.5 <u>የእናት ሃይማኖት</u>

እናትየው የምትከተለው እምነት ወይም የመንፈሳዊ ድርጅት አባልነት በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል። በኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ የሃይማኖት ዓይነቶች ይታወቃሉ። አመዳደባቸውም ከታች ተመልክቷል።

- ኦርቶዶክስ (ተዋህዶ፣ ቅባት፣ ፀጋ)
- ፕሮቴስታንት (ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት፣ ሙሉወንጌል፣ ሉትራን፣ መካነኢየሱስ፣ ባፕቲስት፣ ሜኖናይት፣ አንግሊካን፣ ፕሪስፒተሪያን፣ ...ወዘተ)
- ካቶሊክ

- ሙስሊም (እስላም)
- ባህላዊ እምልኮ
- ሌላ (ሂንዱ፣ ይሁዲ፣ በሃይ፣ ጀሆባ፣ ቡድሂስት፣ ኢቴስት፣...ወዘተ)

እናትየው የምትከተለው ዕምነት ተጠይቆና ተጣርቶ የተገለፀውን የሃይማኖት ስም መመዝገብ ያስፈልጋል። በአመዘጋገብ ወቅት በተለይ ዕምነታቸው ፕሮቴስታንት ለሆኑ በርከት ያሉ የዕምነቱ የአጠራር ዓይነቶች ስለሚኖሩ የቅርንጫፍ ስሙን በመግለጽ መፃፍ ያስፈልጋል። ለምሳሌ የእናትየው ሃይማኖት ሙሉ ወንጌል ከሆነ መመዝገብ ያለበት ፕሮቴስታንት ሳይሆን "ሙሉ ወንጌል" ይሆናል።

## 3.6 የእናት ዜግነት

የእናትየው ዜግነት ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። የአንድ ሰው የኢትዮጵያዊ ዜግነት ጉዳይ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የዜግነት ህግን መሠረት በማድረግ በመለየት ይመዘገባል።

## 3.7 የእናት ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ

እናትየው ህፃኑን/ኗን በወለደችበት ጊዜ በማናቸውም ቋንቋ ማንበብና መፃፍ ትችል እንደነበር፣ ከቻለችም ያጠናቀቀችው ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ስንት እንደሆነ አስመዝጋቢው ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ መልሱ ይመዘገባል። በቅድሚያ መዝጋቢው እናትየው ማንበብና መጻፍ መቻል አለመቻሏን ጠይቆ ማንበብና መፃፍ አትችልም ከተባለ "ማንበብና መፃፍ የማትችል" ተብሎ ይመዘገባል። አንድ ግለሰብ የማንበብና የመፃፍ ችሎታ አለው የሚባለው ቢያንስ በአንድ ቋንቋ አንብቦ መረዳትና መፃፍ ሲችል ነው። የራሳቸውን ስም ወይም ቁጥሮችን ብቻ ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ግለሰቦች የማንበብና የመፃፍ ችሎታ እንዳላቸው አይቆጠሩም። እንዲሁም ሃይማኖት ነክ የሆኑና ቀደም ብለው በቃል የተጠኑ ዐረፍተ ነገሮችን ብቻ መድገም የሚችሉ የማንበብና የመፃፍ ችሎታ እንዳላቸው አይቆጠሩም። ሆኖም ግን መደበኛ በሆነ ት/ቤት ሳይገቡ በመሰረተ ትምህርት ፕሮግራም፣ በቄስ፣ በቁርዓንና በመሳሰሉት በመከታተል እንዲሁም በራሳቸው ጥረት የግለሰቦችን እርዳታ እየጠየቁ ማንበብና መፃፍ የቻሉ ሰዎች ማንበብና መፃፍ እንደሚችሉ በመውሰድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ "መደበኛ ያልሆነ ትምህርት የተከታተለች" ተብሎ ይመዘገባል። እናትየዋ ማንበብና መጻፍ የምትችል ከሆነ የጨረሰችው ከፍተኛ የክፍል ደረጃ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል። የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል አመዘጋገብ እንደ እናትየዋ የትምህርት ደረጃ ወይም በወቅቱ በትምህርት ላይ መሆን ያለመሆን ሊለያይ ይችላል። ይህም ሲባል ግለሰቦች ባለው የትምህርት ስርዓት በመደበኛ ትምህርት እየተማሩ ያሉ ሊሆኑ ይችላሉ፣ የጨረሱ ወይም ያቋረጡ ሊሆኑም ይችላሉ። ስለሆነም እናትየው ያጠናቀቀችው ከፍተኛ የትምህርት ክፍል አመዘጋገብ እንደ ትምህርት ደረጃዋ፣ በወቅቱ ትምህርት እየተከታተለች መሆን ወይም ያለመሆን ይለያያል። ለምሳሌ እናትየው 11ኛ ክፍል እየተማረች ከሆነ ያጠናቀቀችው ከፍተኛ ክፍል "10ኛ ያጠናቀቀች" ተብሎ መመዝገብ አለበት።

በተመሳሳይ እናትየው የዲግሪ ትምህርት ተከታትላ ዲግሪ ያላት ከሆነ የሚመዘገበው "ዲግሪ ያላት" በማለት ነው። ለአመዘጋገብ ያመች ዘንድ የከፍተኛ የትምህርት ደረጃ አመዘጋገብን እንዲረዱ ከታች የትምህርት ደረጃ ዝርዝር ተመልክተዋል።

| | |
|---|---|
| - ማንበብና መፃፍ አትችልም | - 12ኛ ክፍል ያጠናቀቀች |
| - መደበኛ ያልሆነ ትምህርት | - 10+2 |
| የተከታተለች | - 10+3 |
| - አንደኛ ክፍል ያጠናቀቀች | - ሰርተፊኬት ያላት |
| - ሁለተኛ ክፍል ያጠናቀቀች | - ዲፕሎም ያልጨረሰች |
| - ሶስተኛ ክፍል ያጠናቀቀች | - ዲግሪ ያልጨረሰች |
| - አራተኛ ክፍል ያጠናቀቀች | - ዲፕሎም ያላት |
| - አምስተኛ ክፍል ያጠናቀቀች | - ዲግሪ ያላት |
| - ስድስተኛ ክፍል ያጠናቀቀች | - የማስተርስ ዲግሪ ያላጠናቀቀች |
| - ሰባተኛ ክፍል ያጠናቀቀች | - የዶክትሬት ዲግሪ ያላጠናቀቀች |
| - ስምንተኛ ክፍል ያጠናቀቀች | - የማስተርስ ዲግሪ ያላት |
| - ዘጠነኛ ክፍል ያጠናቀቀች | - የዶክትሬት ዲግሪ ያላት |
| - አስረኛ ክፍል ያጠናቀቀች | - ፕሮፌሰር |
| - አስራ አንደኛ ክፍል ያጠናቀቀች | |

### 3.8 የእናት የጋብቻ ሁኔታ

እናትየው ልጁን/ጅቷን በወለደችበት ጊዜ የነበራት የጋብቻ ሁኔታ ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። በወሊድ ጊዜ የጋብቻ ሁኔታ መረጃ መገኘት የሚገባው ከሕዝብ የክብር መዝገብ ከተሰጡ የጋብቻ ወይም የፍቺ ምስክር ወረቀት ነበር። ሆኖም በኢትዮጵያ የሕዝብ የክብር መዝገብ ምዝገባ ሥርዓት ያልተዘረጋ በመሆኑ ህጋዊ የጋብቻ ምስክር ወረቀት ግለሰቦች ማቅረብ አይችሉም። ስለሆነም የእናትየው የወቅቱ የጋብቻ ሁኔታ ከተለያዩ ተቋማት ከተሰጡ ማስረጃዎች ወይም አስመዝጋቢውን በመጠየቅ መመዝገብ አለበት። ለአመዘጋገብ ያመች ዘንድ ከታች የጋብቻ ዓይነቶችና ምንነታቸው ተገልፆአል።

ያላገባች፦ ሕጻኑን/ኗን በወለደችበት ጊዜ አግብታ የማታውቅ ከሆነ "ያላገባች" ተብሎ ይመዘገባል።

ባለትዳር፦ ሕጻኑን/ኗን በወለደችበት ወቅት በጋብቻ ላይ የሆነች ከሆነ "ባለትዳር" ተብሎ ይመዘገባል።

ፈት፦ ሕጻኑን/ኗን በወለደችበት ወቅት ከባልዋ ጋር ተፋታ ከሆነ "ፈት" ተብሎ ይመዘገባል።

ባል የሞተባት፦ ሕጻኑን/ኗን በወለደችበት ወቅት ባሏ የሞተባት ከሆነ "ባል የሞተባት" ተብሎ ይመዘገባል።

የወላጅ እናት ፊርማ

ወላጅ እናት በልደት መዝገቡ ያስመዘገበችው መረጃ ትክክል ለመሆኑ ሙሉ ስም፣ ፊርማና ቀን በመግለጽ ማረጋገጥ ይገባል። ወላጅ እናት በህይወት ከሌለች ወይም የማትታወቅ ከሆነ ይኸው በማስታወሻው ላይ ይገለፃል።

## ክፍል 4 የሕጻኑን/ኗን ወላጅ አባት በሚመለከት

በዚህ ክፍል የሕጻኑን/ኗን ወላጅ አባት አጠቃላይ ሁኔታ የሚመለከቱ ጥያቄዎች አስመዝጋቢው በሚሰጠው መልስና መዝጋቢው በተከታታይ በሚያደርገው ማጣራት መሠረት የተገኙት መረጃዎች ይመዘገባሉ።

### 4.1 የአባት ሙሉ ስም

የሕጻኑን/ኗን ወላጅ አባት የግል ስም፣ የአባትና የአያት ስሞች በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባሉ። የወላጅ አባት የግል ስም ሊወሰድ ይገባ የነበረው አባትየው ሲወለድ ከተመዘገበ የልደት የምስክር ወረቀት ላይ ነበር። ሆኖም ከላይ በሌሎች ቦታዎች እንደተገለጸው በአግባባዊው አሠራር የተዘጋጀ የልደት የምስክር ወረቀቶች እስከተወሰኑ ዓመታት የማይኖሩ በመሆኑ ያለው አማራጭ በወቅቱ አባትየው በቀበሌ መስተዳድር ጽ/ቤት በተሰጠው የመታወቂያ ወረቀት ላይ የተጠቀሰውን ስም ወስዶ መመዝገብ ነው። ይህም ሲሆን በቀበሌ የመታወቂያ ወረቀት ላይ የተገለጸው መለያ ስም ትክክል ለመሆኑ መዝጋቢው ማጣራት አለበት።

### 4.2 የአባት ዕድሜ

አባት ሕጻኑ/ኗ በተወለደበት/ችበት ጊዜ የነበረው ትክክለኛ ዕድሜ በሙሉ ዓመት (በጨረሰው ዓመት) በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። የማንኛውም ሰው ትክክለኛ ዕድሜ የማወቂያ ብቸኛ መንገድ ግለሰቡ በተወለደ ጊዜ በኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት አማካይነት በተመዘገበ የልደት ምስክር ወረቀት መረጃ አማካይነት ነበር። ይህ ከሆነ ዕድሜው ከተፈለገበት ቀን ላይ የተወለደበትን ቀን በማቀናነስ ትክክለኛ ዕድሜውን ማግኘት ይቻላል። በኩነቶች ምዝገባ አማካይነት የልደት የምስክር ወረቀት ለሌላቸው ግለሰቦች ትክክለኛ ዕድሜአቸው ተጠይቆና እንዲያስታውሱ በማድረግ ዕድሜአቸውን ማግኘት ያስፈልጋል። በዚህ መንገድ የሚገኘው የዕድሜ መረጃ ትክክለኛነት በግለሰቡ የልደት ቀን በጽሑፍ ማስታወሻ የመያዝ ልምድና የማስታወስ ችሎታ ላይ ይመሠረታል። ዕድሜ በሙሉ ዓመት ማለት ከሙሉ ዓመት በተጨማሪ ያሉትን ወሮችንና ቀኖችን በመተው ዓመቱን ብቻ በመውሰድ ዕድሜውን መመዝገብ ነው። ለምሳሌ ህፃኑ/ኗ በተወለደችበት ቀን የአባትየው ዕድሜ 36 ዓመት ከ5 ወራት ከ29 ቀናት ቢሆን መመዝገብ ያለበት 36 ዓመት ብቻ ነው።

ዕድሜውን በትክክል ለማያውቅ አባት በተወለደበት ጊዜ/አካባቢ በብሔራዊ ደረጃ ወይም በሚኖርበት አካባቢ የተፈጸመ ታሪካዊ ድርጊት እንዳለና አባትዬው ድርጊቱ በተፈጸመበት ጊዜ

ዕድሜው ስንት እንደነበረ ወይም ከድርጊቱ በኋላ/በፊት ምን ያህል ጊዜ ቆይቶ እንደተወለደ አስመዝጋቢውን በመጠየቅና ዕድሜውን በማስላት ገምቶ መመዝገብ ያስፈልጋል። ከዚህም ሌላ አስመዝጋቢው የአንዳንድ የቤተሰቡን አባላት ወይም የአካባቢ ነዋሪዎች ዕድሜ በትክክል ሊያውቅ ከቻለ ከነዚህ ግለሰቦች ዕድሜ ጋር በማነጻጸር የአባትዬውን ዕድሜ መገመት ይቻላል።

### 4.3 የአባት ብሔረሰብ

የአባትየው ብሔረሰብ ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። አስመዝጋቢው የብሔረሰብን ትርጉም በትክክል እንዲረዳ ትውልድህ፣ ነገድህ፣ ዘርህ፣ ጎሳህ፣ ...ወዘተ በማለት ማብራራት ሊያስፈልግ ይችላል። የዋና ዋና እና የቅርንጫፍ ብሔረሰቦች ስም በዕዝል 1 ተያይዞ ቀርቧል።

### 4.4 የአባት መደበኛ መኖሪያ ቦታ

ህፃኑ/ኗ በተወለደበት/ችበት ጊዜ የአባትየው መደበኛ መኖሪያ ቦታ የት እንደነበር ተጠይቆ ክልሉ፣ ዞኑ፣ ወረዳው፣ ከተማው፣ ቀበሌው እና የቤት ቁጥሩ እንዲሁም የቤት ቁጥር በሌለበት (የገጠር አካባቢ) የመንደሩ ልዩ ስም በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባሉ። የአንድን ሰው መደበኛ መኖሪያ ቦታ ለመለየት በዚህ መመሪያ ለጽንሰ-ሃሳቦች ትርጉምና ማብራሪያ የተሰጠውን መመልከት ይገባል።

### 4.5 የአባት ሃይማኖት

አባትየው የሚከተለው እምነት ወይም የመንፈሳዊ ድርጅት አባልነት ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል። በኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ የሃይማኖት ዓይነቶች ይታወቃሉ። አመዳደባቸውም ከታች ተመልክቷል።

- ኦርቶዶክስ (ተዋህዶ፣ ቅባት፣ ፀጋ)
- ፕሮቴስታንት (ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት፣ ሙሉወንጌል፣ ሉትራን፣ መካነኢየሱስ፣ ባፕቲስት፣ ሜኖናይት፣ አንግሊካን፣ ፕሪስፒተሪያን፣ ...ወዘተ)
- ካቶሊክ
- ሙስሊም (እስላም)
- ባህላዊ አምልኮ
- ሌላ (ሂንዱ፣ ይሁዲ፣ በሃይ፣ ጂሆባ፣ ቡድሂስት፣ ኢቴስት፣...ወዘተ)

አባትየው የየትኛው እምነት ተከታይ እንደሆነ ተጠይቆና ተጣርቶ ትክክለኛውን የሃይማኖት ስም መመዝገብ ያስፈልጋል። በአመዘጋገብ ወቅት በተለይ ዕምነታቸው ፕሮቴስታንት ለሆኑ በርከት ያሉ የዕምነቱ የአጠራር ዓይነቶች ስለሚኖሩ የቅርንጫፍ ስሙን በመግለጽ መፃፍ ያስፈልጋል። ለምሳሌ የአባትየው ኃይማኖት ሙሉ ወንጌል ከሆነ መመዝገብ ያለበት ፕሮቴስታንት ሳይሆን "ሙሉ ወንጌል" ይሆናል።

## 4.6 የአባት ዜግነት

የአባትየው ዜግነት ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። የአንድ ሰው ኢትዮጵያዊ ዜግነት ጉዳይ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የዜግነት ህግን መሠረት በማድረግ በመለየት ይመዘገባል።

## 4.7 የአባት ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ

አባትየው ህፃኑ/ኗ በተወለደበት/ችበት ጊዜ በማናቸውም ቋንቋ ማንበብና መፃፍ ይችል እንደነበር፣ ከቻለም ያጠናቀቀው ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ስንት እንደሆነ አስመዝጋቢው ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ መልሱ ይመዘገባል። በቅድሚያ መዝጋቢው አባትየው ማንበብና መጻፍ መቻል አለመቻሉን ጠይቆ ማንበብና መጻፍ አይችልም ከተባለ "ማንበብና መፃፍ የማይችል" ተብሎ ይመዘገባል። አንድ ግለሰብ የማንበብና የመፃፍ ችሎታ አለው የሚባለው ቢያንስ በአንድ ቋንቋ አንብቦ መረዳትና መፃፍ ሲችል ነው። የራሳቸውን ስም ወይም ቁጥሮችን ብቻ ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ግለሰቦች የማንበብና የመፃፍ ችሎታ እንዳላቸው አይቆጠሩም። እንዲሁም ሃይማኖት ነክ የሆኑና ቀደም ብለው በቃል የተጠኑ ዐረፍተ ነገሮችን ብቻ መድገም የሚችሉ የማንበብና የመፃፍ ችሎታ እንዳላቸው አይቆጠሩም። ሆኖም ግን መደበኛ በሆነ ት/ቤት ሳይገቡ በመሰረተ ትምህርት ፕሮግራም፣ በቄስ፣ በቁርዓንና በመሳሰሉት በመከታተል እንዲሁም በራሳቸው ጥረት የግለሰቦችን እርዳታ እየጠየቁ ማንበብና መፃፍ የቻሉ ሰዎች ማንበብና መፃፍ እንደሚችሉ በመውሰድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ "መደበኛ ያልሆነ ትምህርት የተከታተለ" ተብሎ ይመዘገባል። አባትየው ማንበብና መጻፍ የሚችል ከሆነ የጨረሰው ከፍተኛ የክፍል ደረጃ ይመዘገባል። የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል አመዘጋገብ እንደ አባትየው የትምህርት ደረጃ ወይም በወቅቱ በትምህርት ላይ መሆን ያለመሆን ሊለያይ ይችላል። ይኸም ሲባል ግለሰቦች ባለው የትምህርት ስርዓት በመደበኛ ትምህርት እየተማሩ ያሉ ሊሆኑ ይችላሉ፣ የጨረሱ ወይንም ያቋረጡ ሊሆኑም ይችላሉ። ስለሆነም አባትየው ያጠናቀቀው ከፍተኛ የትምህርት ክፍል አመዘጋገብ እንደ ትምህርት ደረጃው፣ በወቅቱ ትምህርት እየተከታተለ መሆን ወይም አለመሆኑ ይለያያል። ለምሳሌ 10ኛ ክፍል አጠናቆ ያቋረጠ ከሆነ ያጠናቀቀው ከፍተኛ ክፍል 10 ተብሎ ይመዘገባል። በተመሳሳይ አባትየው የዲፕሎም ትምህርት ተከታትሎ ዲፕሎም ያለው ከሆነ የሚመዘገበው "ዲፕሎም ያለው" በማለት ነው። ለአመዘጋገብ ያመች ዘንድ የከፍተኛ ትምህርት ደረጃ ዝርዝር ከታች ተመልክቷል።

- ማንበብና መፃፍ የማይችል
- መደበኛ ያልሆነ ትምህርት የተከታተለ
- አንደኛ ክፍል ያጠናቀቀ
- ሁለተኛ ክፍል ያጠናቀቀ
- ሶስተኛ ክፍል ያጠናቀቀ
- አራተኛ ክፍል ያጠናቀቀ
- አምስተኛ ክፍል ያጠናቀቀ
- ስድስተኛ ክፍል ያጠናቀቀ
- ሰባተኛ ክፍል ያጠናቀቀ
- ስምንተኛ ክፍል ያጠናቀቀ
- ዘጠነኛ ክፍል ያጠናቀቀ
- አስረኛ ክፍል ያጠናቀቀ
- 12ኛ ክፍል ያጠናቀቀ

- 10+2
- 10+3
- ሰርተፊኬት ያለው
- ዲፕሎም ያልጨረሰ
- የመጀመሪያ ዲግሪ ያልጨረሰ
- ዲፕሎም ያለው
- አስራ አንደኛ ክፍል ያጠናቀቀ
- ዲግሪ ያለው
- የማስተርስ ዲግሪ ያልጨረሰ
- የዶክትሬት ዲግሪ ያልጨረሰ
- የማስተርስ ዲግሪ ያለው
- የዶክትሬት ዲግሪ ያለው
- ፕሮፌሰር

### 4.8 የአባት የጋብቻ ሁኔታ

አባትየው ልጁ/ጅቷ በተወለደበት/ችበት ጊዜ የነበረው የጋብቻ ሁኔታ ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። በወሊድ ጊዜ የጋብቻ ሁኔታ መረጃ መገኘት የሚገባው ከሕዝብ የክብር መዝገብ የጋብቻ ወይም ፍቺ ምስክር ወረቀት ነበር። ሆኖም በኢትዮጵያ የሕዝብ የክብር መዝገብ ምዝገባ ሥርዓት ያልተዘረጋ በመሆኑ ህጋዊ የጋብቻ ወይም ፍቺ የምስክር ወረቀት ግለሰቦች ማቅረብ አይችሉም። ስለሆነም የአባትየው የወቅቱ የጋብቻ ሁኔታ ከተለያዩ ተቋማት ከተሰጡ ማስረጃዎች ወይም አስመዝጋቢውን በመጠየቅ መመዝገብ አለበት። ለአመዘጋገብ ያመች ዘንድ ከታች የጋብቻ ዓይነቶችና ምንነታቸው ተገልፆአል።

ያላገባ፡- ሕጻኑ/ኗ በተወለደበት/ችበት ጊዜ አግብቶ የማያውቅ ከሆነ "ያላገባ" ተብሎ ይመዘገባል።

ባለትዳር፡- ሕጻኑ/ኗ በተወለደበት/ችበት ወቅት ከህፃኑ/ኗ እናት ጋር ወይም ከሌላ ሴት ጋር በጋብቻ ላይ ከሆነ "ባለትዳር" ተብሎ ይመዘገባል።

ፈት፡- ሕጻኑ/ኗ በተወለደበት/ችበት ወቅት ከህፃኑ/ኗ አባት (ከሚስቱ) ጋር የተፋታ ከሆነ "ፈት" ተብሎ ይመዘገባል።

ሚስት የሞተበት፡- ሕጻኑ/ኗ በተወለደበት/ችበት ወቅት የህፃኑ/ኗ እናት (ሚስቱ) የሞተችበት ከሆነና ከዚያ በኋላ ያላገባ ከሆነ "ሚስት የሞተችበት" ተብሎ ይመዘገባል።

#### የወላጅ አባት ፊርማ

ወላጅ አባት በልደት መዝገቡ ያስመዘገበው መረጃ ትክክል ለመሆኑ ሙሉ ስም፣ ፊርማ እና ቀን በመግለጽ ማረጋገጥ ይገባል። ወላጅ አባት በህይወት ከሌለ ወይም የማይታወቅ ከሆነ ይኸው በማስታወሻው ላይ ይገለፃል።

## ክፍል 5 አስመዝጋቢን የሚመለከት

በዚህ ክፍል የልደቱን አስመዝጋቢ የሚመለከቱ መረጃዎች ይመዘገባሉ። የልደት ኩነት የማስመዝገብ ቀዳሚ ኃላፊነት የተጣለባቸው እናትና አባት ናቸው። ይኸም ሲሆን ልደቱን በህጉ

በተደነገገው የምዝገባ ጊዜ ለማስመዝገብ ከአባት ወይም ከእናት አንዳቸው በምዝገባ ጽ/ቤት በመገኘት ማስመዝገብ ይኖርባቸዋል። ሆኖም ምንም እንኳን የልደቱን መከሰት ለማሳወቅ አንዳቸው ማስመዝገብ ቢችሉም ሁለቱም በአንድነት በምዝገባ ጽ/ቤቱ ቀርበው ዝርዝር መረጃዎችን መስጠትና ወላጅነታቸውን በፊርማቸው ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል። ነገር ግን የህፃኑ/ኗ አባት ወይም እናት በሞት ወይም በከፍተኛ የጤና ችግር/ ህመም ምክንያት ወይም በአካባቢው ባለመኖር ወይም በሌላ የተረጋገጠ ምክንያት ልደቱን ማስመዝገብ ካልቻሉ የህፃኑ/ኗ የቅርብ ዘመድ ወይም ህፃኑን/ኗን በአደራ የተረከበ ተቋም ወይም ማናቸውም ልደቱን ያወቀ ግለሰብ ወይም ተቋም ልደቱን የማስመዝገብ ግዴታ አለበት።

ልደቱን የማስመዝገብ ቅድሚያ ኃላፊነት የተጣለባቸው ወላጆች ሁለቱም ቀርበው ካስመዘገቡ የአስመዝጋቢዎች ቦታ ላይ የእናት ወይም የአባት መረጃ ይመዘገባል። ሆኖም በአስተያየት መስጫው ላይ ይኸው ይገለጻል። በሌላ በኩል ከሁለቱ ወላጆች አንዳቸው ቀርበው ካስመዘገቡ ወይም ከሁለቱ ወላጆች የተለየ አስመዝጋቢ ልደቱን ካስመዘገበ አስመዝጋቢው አንድ ብቻ ይሆናል።

5.1 <u>የአስመዝጋቢ ሙሉ ስም</u>

የአስመዝጋቢ የግል፣ የአባትና የአያት ስሞች በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባሉ።

5.2 <u>አስመዝጋቢ ለህፃኑ/ኗ ያለው የዝምድና ዓይነት</u>

አስመዝጋቢ ከሕጻኑ/ኗ ጋር ያለው/ላት የዝምድና ዓይነት በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። ሕጻኑ/ኗ ተጥሎ/ላ የተገኘ/ች ወይም ደግሞ የተመዘገበው/ችው በተቋማት ኃላፊዎች ከሆነ ይኸው ተገልጾ በአስተያየት ይጻፋል።

5.3 <u>የአስመዝጋቢ መደበኛ መኖሪያ ቦታ</u>

የአስመዝጋቢ መደበኛ መኖሪያ ቦታ የሚገኝበት ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ከተማ፣ ቀበሌ እና የቤት ቁጥር እንዲሁም የቤት ቁጥር በሌለበት የገጠር አካባቢ የመንደሩ ልዩ ስም በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባሉ።

5.4 <u>የአስመዝጋቢ ፊርማና ቀን</u>

በልደት መዝገቡ የተመዘገቡት መረጃዎች ለአስመዝጋቢ ከመዝገቡ እየተነበቡ ከተገለፁ እና በአስመዝጋቢው/ዋ ከታመነባቸው በኋላ አስመዝጋቢ የሰጠው መረጃ ትክክል ስለመሆኑ በፊርማ በማረጋገጥና ቀኑን፣ ወሩን እና ዓመተ ምህረቱን በመፃፍ ይገልፃል/ ትገልጻለች።

*<u>ማስታወሻ፡-</u>*

*በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ በተለይም በገጠሩ ክፍል ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ብዙ ሰዎች ማንበብና መፃፍ አይችሉም። ስለሆነም ማንበብና መፃፍ የማይችሉ አስመዝጋቢዎች ለመዝጋቢ የሰጡዋቸው መረጃዎች*

ከተነበቡላቸው በኋላ በኩነቱ መረጃ ሥር ለመፈረም ይቸገሩ ይሆናል። የዚህ ዓይነት ሁኔታ በሚያጋጥም ጊዜ ያስመዝጋቢውን አውራ ወይም አመልካች ጣት ቀለም በመቀባት በጣት ማስፈረም ያስፈልጋል።

## ክፍል 6 ለልደት መከሰት ማረጋገጫ የቀረበ ማስረጃ

በዚህ ክፍል የልደት ኩነቱ በእርግጥ የተከሰተ መሆኑን የሚገልጸው ማስረጃ ዓይነት የሚገለጽበት ነው።

### 6.1 የሐኪም የልደት የምስክር ወረቀት

እናትየዋ የተገላገለችው በጤና ተቋም ውስጥ ከሆነና በምዝገባው ወቅት ይህንኑ የሚገልጽ የጽሑፍ ማስረጃ ወይም የሜዲካል የልደት የምስክር ወረቀት በአስመዝጋቢው አማካይነት ከቀረበ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ በልደት የምስክር ወረቀት ላይ የተፃፈው የመዝገብ ቁጥር እና ህፃኑ/ኗ የተወለደበት/ችበት የጤና ተቋም ስም ይመዘገባል። እንዲሁም የሜዲካል የልደት የምስክር ወረቀቱ ቅጂ ከመዝገቡ ጋር ይያያዛል።

### 6.2 የዓይን ምስክሮችን የሚመለከት

ልጅ በትክክል መወለዱን የሚያረጋግጡ ሶስት የአይን ምስክሮች ሙሉ ስም (የግል፣ የአባት፣ የአያት ስሞች) በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። የአይን ምስክሮች ሆነው በመዝጋቢው ፊት ሊቀርቡ የሚችሉ ሰዎች እድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆኑና ልጁ/ጅቷ ሲወለድ/ስትወለድ ያዋለዱ ወይም በእናትየው የእርግዝና ወቅትም ሆነ በምትወለድበት ጊዜ የቅርብ ግንኙነት ያላቸው ዘመዶች ወይም ጎረቤቶች ወይም ሠራተኛ ሊሆኑ ይችላሉ። በተጨማሪም የምስክሮቹ መደበኛ መኖሪያ ቦታ ማለትም ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ከተማ፣ ቀበሌ፣ የቤት ቁጥር እንዲሁም የቤት ቁጥር በሌለበት የገጠር ቀበሌ የመንደሩ ልዩ ስም በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። እንዲሁም የዓይን ምስክሮች ልደቱ ስለመከሰቱ የሰጡት ቃል ትክክል ስለመሆኑ በፊርማቸው በማረጋገጥ ቀኑን፣ ወሩንና ዓመተ ምህረቱን በበዚህ ክፍል በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ በመፃፍ ይገልፃሉ።

## ክፍል 7. አስተያየት

ማናቸውም ከሕጻኑ ልደትና ምዝገባ ጋር ተዛማጅ የሆኑና ጠቃሚነት ኣላቸው ተብለው የሚገመቱ ማስታወሻዎች ሁሉ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይፃፋሉ።

## ክፍል 8. የመዝጋቢ ሙሉ ስም፣ ፊርማና ቀን

በዚህ ክፍል መዝጋቢው በልደት መዝገቡ የመዘገበው መረጃ ትክክል መሆኑን ሙሉ ስሙን፣ ፊርማውንና ዕለቱን በመግለፅ ያረጋግጣል።

8.1 የመዝጋቢው ሙሉ ስም

የመዝጋቢው የግል ስም፣ የአባት ስምና የአያት ስም በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባሉ።

8.2 የመዝጋቢ ፊርማና ቀን

መዝጋቢው አስፈላጊዎቹ መረጃዎች ተሟልተው ምዝገባው በትክክል ለመከናወኑ ፊርማውን በማስቀመጥ ያረጋግጣል። በተጨማሪም መዝጋቢው ምዝገባውን ያጠናቀቀበትን ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት በመጥቀስ ያሰፍራል።

## 3.2 የሞት ወሳኝ ኩነት መረጃ አመዘጋገብ

በሞት የክብር መዝገብ ውስጥ የሚሠፍሩት መረጃዎች ከዚህ በታች የተመለከተውን የአመዘጋገብ መመሪያ መሠረት በማድረግ ይመዘገባሉ። የወሳኝ ኩነቶች መዝ.ጋቢ ከአስመዝ.ጋቢ.ዎች የመጡለትን የሞት ኩነቶች፣ ከተለያዩ አካላት በመጡለት የሞት ማስረጃዎች በመታገዝ፣ በጠቋሚዎችና በራስ አነሳሽነት ያወቃቸውን የሞት ኩነቶች ጭምር ይመዘግባል።

የሞት ኩነትን በቀዳሚነት የማስመዝገብ ግዴታ የተጣለባቸው የሟች የትዳር ጓደኛ፣ ወላጆች፣ ልጆች ወይም ሌሎች የቅርብ ዘመዶች ናቸው። እነዚህ በሌሉበት ሁኔታ ሞቱ በተከሰተበት ቤት ባለቤት/ነዋሪ የሆነ ማንኛውም ሰው ወይም ጐረቤት የሞቱን ክስተት የማስታወቅና የማስመዝገብ ግዴታ አለበት። በመሆኑም በሞት መዝገቡ ውስጥ የሚመዘገቡ መረጃዎችን መዝ.ጋቢ.ው ከዚህ በታች የተሰጡትን አጠቃላይ መመሪያዎች መሠረት በማድረግ እንደ ሁኔታው በትክክል መመዝገብ ይጠበቅበታል።

በተጨማሪም የሞት ኩነት ምዝገባን በተመለከተ *በምዝገባ ሕጉ* የተመለከተውን መሠረት በማድረግ የሚከተሉት ጉዳዮች በአመዘጋገብ አፈፃፀሙ ትኩረት ሊያገኙ ይገባል።

1ኛ/ በቤት ውስጥ ሞት ሲከሰት የሟች የቅርብ ዘመዶች ወይም የትዳር ጓደኛ ወይም የቤቱ ባለቤት ወይም በወቅቱ ያስታመሙ ሰዎች ሞት ስለመከሰቱ ለቀበሌ የወሳኝ ኩነቶች መዝ.ጋቢ. ጥቆማ የማድረግና የማስመዝገብ ግዴታ አለባቸው።

2ኛ/ በማናቸውም የጤና ተቋም ሞት ሲከሰት በሞቱ ጊዜ የነበረ ወይም በመጨረሻ የህመሙ ወቅት ያከመው ሐኪም የሞት የሜዲካል የምስክር ወረቀት እንዲዘጋጅ በማድረግና የተቋሙን ማህተም በማስፈር የሕክምና ተቋሙ የበላይ ሃላፊ ተቋሙ ለሚገኝበት ቀበሌ የሕዝብ የክብር መዝገብ የሥራ ክፍል የምስክር ወረቀቱን ቅጂ የመላክ ግዴታ አለበት። በተመሳሳይም የሟች የቅርብ ዘመዶች በጤና ተቋሙ የተሰጣቸውን የሞት የሜዲካል የምስክር ወረቀት በመያዝ ሟች በመደበኛነት ለሚኖርበት ቀበሌ የወሳኝ ኩነት መዝ.ጋቢ. ሞቱን የማስመዝገብ ግዴታ አለባቸው።

3ኛ/ ወድቆ የተገኘ ወይም ዘመዶቹ ያልታወቁ ሟች አስከሬኑ በመጀመሪያ ፖሊስ እንዲያውቀው ተደርጐ፣ አስከሬኑ ለምርመራ ወደ ጤና ተቋም ይላካል። በተገኘውም የምርመራ መረጃ መሠረት የሞቱ መንስዔ በሚዘጋጅለት የሞት ሜዲካል የምስክር ወረቀት ይመዘገባል። የጤና ተቋሙ የምስክር ወረቀቱን ቅጂ ተቋሙ ለሚገኝበት ቀበሌ የሕዝብ የክብር መዝገብ የሥራ ክፍል የመላክ ግዴታ አለበት። በተመሳሳይም የሟች የቅርብ ዘመዶች በጤና ተቋሙ የተሰጣቸውን የሞት የሜዲካል የምስክር ወረቀት በመያዝ

ሟች በመደበኛነት ለሚኖርበት ቀበሌ የወሳኝ ኩነቶች መዝጋቢ ሞቱን የማስመዝገብ ግዴታ አለባቸው።

4ኛ/ በማረሚያ ቤቶች፣ በጦር ካምፖች፣...ወዘተ ሞት የተከሰተ እንደሆነ የነዚህ ተቋሞች የበላይ ኃላፊዎች የሞቱን መከሰት ተቋሞቹ ለሚገኙበት ቀበሌ የሕዝብ የክብር መዝገብ የሥራ ክፍል የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው።

በመሆኑም መዝጋቢው ከላይ የተገለጹትንና በምዝገባ ሕጉ በዝርዝር የሚደነገጉትን የአመዘጋገብ ሥርዓቶች ተከትሎ በሞት የሕዝብ የክብር መዝገቡ ውስጥ ተፈላጊዎቹን መረጃዎች መመዝገብ ይጠበቅበታል።

ከሁሉም በላይ መዝጋቢው በሞት የሕዝብ የክብር መዝገቡ ውስጥ ላሰፈራቸው መረጃዎች ትክክለኛነትና እውነተኛነት በሕግ ተጠያቂነት ስላለበት በአስመዝጋቢ የሚነገሩትንና በመረጃ የቀረቡትን ማስረጃዎች በከፍተኛ ጥንቃቄ መርምሮ መረጃዎችን መመዝገብ ይጠበቅበታል።

## ክፍል 1 <u>የምዝገባ አካባቢ መለያ</u>

በዚህ ክፍል የሞት ኩነቱ የተመዘገበበት የቀበሌ መስተዳድር የሕዝብ የክብር መዝገብ የሥራ ክፍል የሚገኝበት ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ከተማ፣ የቀበሌ ስም ወይም ቁጥር እና የምዝገባ ጽ/ቤቱ የሚገኝበት ቤት የቤት ቁጥር ወይም በገጠር የመንደሩ ልዩ ስምና የቤት ቁጥር ይመዘገባል።

### 1.1 <u>የክልል ስም</u>

"የክልል ስም" በሚለው ክፍት ቦታ ምዝገባው የሚካሄድበት ቀበሌ የሚገኝበት ክልል ስም ይመዘገባል።

### 1.2 <u>የዞን ስም</u>

"የዞን ስም" በሚለው ሥር በተሰጠው ክፍት ቦታ ምዝገባው የሚካሄድበት ቀበሌ የሚገኝበት ዞን ስም ይመዘገባል።

### 1.3 <u>የወረዳ ስም</u>

"የወረዳ ስም" በሚለው ክፍት ቦታ ምዝገባው የሚካሄድበት ቀበሌ የሚገኝበት ወረዳ ስም ይመዘገባል።

## 1.4 የከተማ ስም

ምዝገባው የሚካሄድበት ቀበሌ የሚገኘው በከተማ ሥር ከሆነ በተሰጠው ክፍት ቦታ "የከተማው ስም" ይመዘገባል።

## 1.5 የከተማ ቀበሌ ስም ወይም ቁጥር

ምዝገባው የሚካሄድበት የከተማ ቀበሌ መስተዳድር ስም ወይም ቁጥር በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል።

## 1.6 የገጠር ቀበሌ (ገ/ማህበር) ስም ወይም ቁጥር

ምዝገባው የሚካሄድበት ቀበሌ የሚገኘው በገጠር ከሆነ የገጠር ቀበሌው ስም ወይም ቁጥር በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል።

## 1.7 የምዝገባ ጽ/ቤት የቤት ቁጥር (በከተማ)

የቀበሌው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የሥራ ክፍል የሚገኝበት ቤት የቤት ቁጥር ይመዘገባል። በከተማ ቤቱ የሚለየው ለቤቱ የቀበሌው መስተዳድር በሰጠው የቤት ቁጥር አማካይነት ነው። በዚሁም መሠረት ቀበሌው ለቤቶች ሥርዓትን ተከትሎ የቤት ቁጥር እንዲሰጥ "በሚያዘው መመሪያ" መሠረት የምዝገባ የሥራ ክፍሉ ለሚገኝበት ጽ/ቤት የተሰጠው የቤት ቁጥር ይመዘገባል። ቤቱ ንዑስ ቁጥር ወይም ፊደል ካለው ከቤቱ ቁጥር ጋር አብሮ ይመዘገባል።

## 1.8 የምዝገባ ጽ/ቤት የሚገኝበት የመንደር ልዩ ስም እና የቤት ቁጥር (በገጠር)

በገጠር መኖሪያ ቤቶችም ሆኑ የድርጅት ቤቶች የመለያ የቤት ቁጥር ላይሰጣቸው ይችላል። ሆኖም የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባን በማከናወን ቤተሰቦችን ለመለየትና አድራሻቸውን ለማወቅ አልፎም የምዝገባ ጽ/ቤቶችን ለመለየት ለቤቶች ሥርዓትን የተከተለ የቤት ቁጥር መስጠት አስፈላጊ ነው። ስለሆነም ቤቶችን በሥርዓት የቤት ቁጥር የመስጠት አሰራርን በገጠር ቀበሌዎች ማስፈጸን የምዝገባው አንድ አካል አድርጎ መውሰድ ያስፈልጋል። በዚሁም መሠረት ቀበሌው ለቤቶች ሥርዓትን ተከትሎ የቤት ቁጥር እንዲሰጥ "በሚያዘው መመሪያ" መሠረት የምዝገባ የሥራ ክፍሉ ለሚገኝበት ጽ/ቤት የተሰጠው የቤት ቁጥር እና የመንደሩ ልዩ ስም ይመዘገባል።

# ክፍል 2 ሟችን በሚመለከት

በዚህ ክፍል የሟቹን አጠቃላይ ሁኔታ የሚመለከቱ ጥያቄዎች አስመዝጋቢው በሚሰጠው መልስና መዝጋቢው በተከታታይ በሚያደርገው ማጣራት መሠረት ይመዘገባሉ። በሌሎች ቦታዎች ተደጋግሞ እንደተገለጸው በመሠረቱ ሟችን የሚመለከቱ ግላዊ የማንነት መረጃዎች የሚገኙት ለግለሰቡ ከተዘጋጁት የልደት፣ የጋብቻና ፍቺ የምስክር ወረቀቶች ላይ ነበር። ሆኖም በአገራችን የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ቀደም ብሎ ስላልተጀመረ ሕጋዊ የምስክር

ወረቀቶች ማቅረብ ያስቸግራል። በመሆኑም የመረጃዎቹን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ደጋፊ ማስረጃዎችን መጠየቅና በአስመዝጋቢው የተሰጡ መልሶችን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

2.1 የሟች ሙሉ ስም

የሟቹ የግል ስም፣ የአባት ስምና የአያት ስሞች በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባሉ። የሟች የግል የመለያ ስም ሊወሰድ ይገባ የነበረው ሟች ሲወለድ/ስትወለድ ከተመዘገበ የልደት የምስክር ወረቀት ላይ ነበር። ሆኖም ከላይ በተለያዩ ቦታዎች ለመግለጽ እንደተሞከረው እስከተወሰኑ ዓመታት በአግባባዊው አሠራር የተዘጋጁ የኩነቶች የምስክር ወረቀቶች የማይኖሩ በመሆኑ ያለው አማራጭ ሟች ቀደም ሲል በቀበሌ መስተዳድር ጽ/ቤት በተሰጠው የነዋሪነት መታወቂያ ላይ የተጠቀሰውን ስም ወስዶ መመዝገብ ነው። ይህም ሲሆን በቀበሌ የነዋሪነት መታወቂያ ላይ የተገለፀው የሟች ስም ትክክል ለመሆኑ መዝጋቢው ማጣራት አለበት።

2.2 የሟች ዕድሜ

ሟቹ በሞተበት ጊዜ የነበረው ትክክለኛ ዕድሜ በሙሉ ዓመት (በጨረሰው ዓመት) በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። በሌሎች ቦታዎች እንደተገለጸው የማንኛውንም ሰው ትክክለኛ ዕድሜ የማወቂያ አስተማማኝ መንገድ ግለሰቡ በተወለደበት ጊዜ በኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት አማካይነት ከተሰጠው የምስክር ወረቀት ላይ በመውሰድ ነው። ይህ ከሆነ ዕድሜው ከተፈለገበት ቀን ላይ የተወለደበትን ቀን በማቀናነስ ትክክለኛውን የዕድሜ መረጃ ማግኘት ይቻላል። በኩነቶች ምዝገባ አማካይነት የተሰጠ የልደት ምስክር ወረቀት ለሌላቸው ግለሰቦች የተወለዱበትን ትክክለኛ ዕድሜ ጠይቆ ዕድሜአቸውን ማግኘት ያስፈልጋል። በዚህ መንገድ የሚገኘው የዕድሜ መረጃ ትክክለኛነት በግለሰቡ የትውልድ ቀኑን በጽሑፍ ማስታወሻ በመያዝ ልምድ ላይ ይመሠረታል። ዕድሜ በሙሉ ዓመት ማለት ከሙሉ ዓመት በተጨማሪ ያሉትን ወሮችንና ቀኖችን በመተው ዓመቱን ብቻ በመውሰድ ዕድሜውን መመዝገብ ነው። ለምሳሌ የሟቹ ዕድሜ 39 ዓመት ከ11 ወራት ከ29 ቀናት ቢሆን መመዝገብ ያለበት 39 ዓመት ብቻ ነው።

የሟች ዕድሜ በትክክል የማይታወቅ የሆነ እንደሆነ ሟች በተወለደበት ጊዜ/አካባቢ በብሔራዊ ደረጃ ወይም ይኖር በነበረበት አካባቢ የተፈጸሙ ታሪካዊ ድርጊቶችን አስመዝጋቢውን እንዲያስታውስ በማድረግና ሟቹ ድርጊቱ በተፈጸመ ጊዜ ዕድሜው ስንት እንደነበረ ወይም ከድርጊቱ በኋላ/በፊት ምን ያህል ጊዜ ቆይቶ እንደተወለደ አስመዝጋቢውን በመጠየቅና በማስላት የሟችን ዕድሜ መመዝገብ ያስፈልጋል።

ከዚህም ሌላ አስመዝጋቢው የአንዳንድ የቤተሰቡን አባላት ወይም የአካባቢ ነዋሪዎች ዕድሜ በትክክል ሊያውቅ ከቻለ ከነዚህ ግለሰቦች ዕድሜ ጋር በማነጻጸር የሟቹን ዕድሜ መገመት ይቻላል።

## 2.3 የሟች ፆታ

የሟች ፆታ ተለይቶ ወንድ ከሆነ "ወንድ"፣ ሴት ከሆነች "ሴት" በማለት በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል።

## 2.4 የሟች ብሔረሰብ

የሟቹ ብሔረሰብ አስመዝጋቢውን በመጠየቅ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። አስመዝጋቢው የብሔረሰብን ትርጉም በትክክል እንዲረዳ ትውልድ፣ ነገድ፣ ዘር፣ ጎሳ፣...ወዘተ በማለት ማብራራት ሊያስፈልግ ይችላል። የዋና ዋና እና የቅርንጫፍ ብሔረሰቦች ስም ዝርዝር በዕዝል 1 ተያይዞ ቀርቧል።

## 2.5 የሟች ሃይማኖት

ሟች ይከተለው የነበረው እምነት ወይም የመንፈሳዊ ድርጅት አባልነት በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። በኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ የሃይማኖት ዓይነቶች ይታወቃሉ። አመዳደባቸውም ከታች ተመልክቷል።

- ኦርቶዶክስ (ተዋህዶ፣ ቅባት፣ ፀጋ)
- ፕሮቴስታንት (ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት፣ ሙሉወንጌል፣ ሉትራን፣ መካነኢየሱስ፣ ባፕቲስት፣ ሜኖናይት፣ አንግሊካን፣ ፕሪስፒተሪያን፣ ...ወዘተ)
- ካቶሊክ
- ሙስሊም (እስላም)
- ባህላዊ አምልኮ
- ሌላ (ሂንዱ፣ ይሁዲ፣ በሃይ፣ ጀሆባ፣ ቡድሂስት፣ ኢቴስት፣...ወዘተ)

ሟች ከላይ ከተጠቀሱት እምነቶች የየትኛው ዕምነት ተከታይ እንደነበረ ተጣርቶ ትክክለኛውን የሃይማኖት ስም መመዝገብ ያስፈልጋል። በአመዘጋገብ ወቅት በተለይ ዕምነታቸው ፕሮቴስታንት ለሆኑ በርከት ያሉ የዕምነቱ የአጠራር ዓይነቶች ስለሚኖሩ የቅርንጫፍ ስሙን በመግለጽ መፃፍ ያስፈልጋል። ለምሳሌ የሟች ሃይማኖት ሙሉ ወንጌል ከነበረ መመዝገብ ያለበት ፕሮቴስታንት ሳይሆን "ሙሉ ወንጌል" ይሆናል።

## 2.6 የሟች ዜግነት

የሟቹ/ቿ ዜግነት ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። የአንድ ግለሰብ የኢትዮጵያ ዜግነት ጉዳይ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የዜግነት ህግን መሠረት በማድረግ በመለየት ይመዘገባል።

## 2.7 የሟች መደበኛ መኖሪያ ቦታ

የሟች መደበኛ መኖሪያ ቦታ ሟች ከመሞቱ አስቀድሞ በመደበኛነት ይኖርበት የነበረውን ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ከተማ፣ ቀበሌ እና የቤት ቁጥር ይመለከታል። የሟችን መደበኛ መኖሪያ ከአስመዝጋቢው በመጠየቅ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። ሟች የቤት ቁጥር በሌለበት የገጠር ቀበሌ ይኖር የነበረ ከሆነ የመንደሩ ልዩ ስም ይመዘገባል።

## 2.8 የሟች ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ

ሟች በህይወት ዘመኑ በማናቸውም ቋንቋ ማንበብና መፃፍ ይችል እንደነበር፣ ይችል ከነበረም ያጠናቀቀው ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ አስመዝጋቢው ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ የትምህርት ደረጃው ይመዘገባል። በቅድሚያ አስመዝጋቢው ሟች ማንበብና መጻፍ መቻል አለመቻሉን ተጠይቆ ሟች ማንበብና መጻፍ አይችልም ነበር ከተባለ "ማንበብና መፃፍ አይችልም" ተብሎ ይመዘገባል። አንድ ግለሰብ የማንበብና የመፃፍ ችሎታ አለው የሚባለው ቢያንስ በአንድ ቋንቋ አንብቦ መረዳትና እንዲሁም መፃፍ ሲችል ነው። የራሳቸውን ስም ወይም ቁጥሮችን ብቻ ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ግለሰቦች የማንበብና የመፃፍ ችሎታ እንዳላቸው አይቆጠሩም። እንዲሁም ሃይማኖት ነክ የሆኑና ቀደም ብለው በቃል የተጠኑ ዐረፍተ ነገሮችን ብቻ መድገም የሚችሉ የማንበብና የማፃፍ ችሎታ እንዳላቸው አይቆጠሩም። ሆኖም ግን መደበኛ በሆነ ት/ቤት ሳይገቡ በመሰረተ ትምህርት ፕሮግራም፣ በቄስ፣ በቁርዓንና በመሳሰሉት በመከታተል እንዲሁም በራሳቸው ጥረት የግለሰቦችን እርዳታ እየጠየቁ ማንበብና መፃፍ የቻሉ ሰዎች ማንበብና መፃፍ እንደሚችሉ በመወሰድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ "መደበኛ ያልሆነ ትምህርት የተከታተለ" ተብሎ ይመዘገባል። ሟች ማንበብና መጻፍ የሚችል ከነበረ የጨረሰው ከፍተኛ የክፍል ደረጃ ይመዘገባል። የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል አመዘጋገብ እንደ ሟች የትምህርት ደረጃ ወይም ከመሞቱ በፊት በትምህርት ላይ መሆን አለመሆኑ ሊለያይ ይችላል። ይህም ሲባል ሟች ከመሞቱ በፊት ባለው የትምህርት ስርዓት በመደበኛ ትምህርት እየተማረ የነበረ ሊሆን ይችላል፣ ወይም የጨረሰ ወይም ያቋረጠ ሊሆንም ይችላል። ስለሆነም ሟች ያጠናቀቀውን ከፍተኛ የትምህርት ክፍል አመዘጋገብ እንደ ክፍል ደረጃውና ከመሞቱ በፊት ትምህርት እየተከታተለ መሆን ወይም ያለመሆኑ ይለያያል። ለምሳሌ ሟች ከመሞቱ በፊት 8ኛ ክፍል እየተማረ ከነበረ ያጠናቀቀው ከፍተኛ ክፍል 7ኛ ተብሎ ይመዘገባል። ለአመዘጋገብ ያመች ዘንድ የከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ዝርዝር ከታች ተመልክቷል።

- መደበኛ ትምህርት የተከታተለ/ች
- ማንበብና መፃፍ አይችልም/አትችልም
- አንደኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ቀች
- ሁለተኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ቀች
- ሶስተኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ቀች
- አራተኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ቀች
- አምስተኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ቀች
- ስድስተኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ቀች
- ሰባተኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ቀች
- ስምንተኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ቀች
- ዘጠነኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ቀች
- አስረኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ቀች

- አስራ አንደኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ቀች
- 10+2
- 10+3
- አስራ ሁለተኛ ክፍል ያጠናቀቀ
- ሰርተፊኬት ያለው/ላት
- ዲፕሎም ያልጨረሰ/ች
- ዲግሪ ያልጨረሰ/ች
- ዲፕሎም ያለው/ያላት
- የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው/ያላት
- የማስተርስ ዲግሪ ያላጠናቀቀ/ቀች
- የዶክትሬት ዲግሪ ያላጠናቀቀ/ች
- የማስተርስ ዲግሪ ያለው/ያላት
- የዶክትሬት ዲግሪ ያለው/ያላት
- ፕሮፌሰር

## 2.9 የሟች የጋብቻ ሁኔታ

ሟች በሞተበት ጊዜ የነበረው የጋብቻ ሁኔታ ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ የጋብቻው ሁኔታ ይመዘገባል። የሟች የጋብቻ ሁኔታ መረጃ መገኘት የነበረበት ሟች ጋብቻ በፈፀመበት ወቅት ወይም ጋብቻው ፈርሶ ከሆነም ይኸንኑ ከሚያረጋግጥ የጋብቻ ወይም የፍቺ የምስክር ወረቀት በማቅረብ ነበር። ሆኖም በአገራችን የሕዝብ የክብር መዝገብ ምዝገባ ሥርዓት ያልተዘረጋ በመሆኑ በርካታ ግለሰቦች ሕጋዊ የጋብቻ ወይም የፍቺ የምስክር ወረቀት ማቅረብ አይችሉም። ስለሆነም ሟች በሞተበት ወቅት የነበረው የጋብቻ ሁኔታ ከተለያዩ ተቋማት ከተሰጡ ማስረጃዎች ወይም አስመዝጋቢውን በመጠየቅ መመዝገብ አለበት። ለአመዘጋገብ ያመች ዘንድ ከታች የጋብቻ ዓይነቶችና ምንነታቸው ተገልፆአል።

ያላገባ/ች፡- ሟች በህይወት ዘመኑ/ኗ አግብቶ/ታ የማያውቅ/የማታውቅ ከሆነ "ያላገባ/ች" ተብሎ ይመዘገባል።

ባለትዳር፡- ሟች በሞተበት/ችበት ወቅት በጋብቻ ላይ የነበረ/ች ከነበረ "ባለትዳር" ተብሎ ይመዘገባል።

ፈት፡- ሟች በሞተበት/ችበት ወቅት ከሚስቱ ወይም ከባልዋ ተፋቶ/ታ ከነበረ "ፈት" ተብሎ ይመዘገባል።

የሞተበት/ባት፡-ሟች በሞተበት/ችበት ወቅት ባል ወይም ሚስት የሞተበት ወይም የሞተችበት ከሆነ "የሞተበት/ባት" ተብሎ ይመዘገባል።

## 2.10 የሟች መደበኛ የሥራ ዓይነት

ሟች በሕይወት በነበረበት ጊዜ ያከናውን የነበረው ዋነኛ መደበኛ ተግባር ምን እንደነበር አስመዝጋቢውን በመጠየቅ ይመዘገባል። ሟች ከአንድ በላይ የሥራ ዓይነት ያከናውን ከነበረ ዋነኛው ተግባር ተለይቶ መመዝገብ አለበት። የሟችን የሥራ ዓይነት ለመግለጽ እንዲረዳ ከታች በምሳሌነት የተለያዩ የሥራ ዓይነቶች ቀርበዋል። ስለሆነም መዝጋቢው በአስመዝጋቢው የተጠቀሰውን የሥራ ዓይነት በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘግባል።

- አራሽ ገበሬ
- አርብቶ አደር (በከብት ርቢ የሚተዳደር)
- ነጋዴ
- ሸማኔ
- አንጥረኛ
- ተማሪ
- የቤት እመቤት
- የፋብሪካ ወዛደር
- የቀን ሠራተኛ
- ግንበኛ
- ቀለም ቀቢ
- አናፂ
- ስራ አጥ
- የህክምና ዶክተር
- ነርስ
- አስተማሪ
- ጸሐፊ
- አስተዳዳሪ
- ኢንጅነር
- የመዝገብ ቤት ሰራተኛ

...ወዘተ

2.11 <u>የሞት ምክንያት</u>

ለሟቹ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት ዋና መንስዔ የሆነው የበሽታ ወይም የአደጋ ዓይነት ይመዘገባል። ሟቹ የሞተው በጤና ተቋም ውስጥ የሆነ እንደሆነ ሟቹን በመጨረሻው የህመሙ ወቅት ያከመ የጤና ባለሙያ ፈርሞ በሰጠው የሞት የምስክር ወረቀት ላይ የተመለከተው የሞት ምክንያት ተወስዶ ይመዘገባል። በቤት ውስጥ ህይወታቸው ያለፈ ወይም በድንገተኛ በሽታ የሞቱ ሰዎችን የሞት ምክንያት ለይቶ ማወቅ በተለይም የህክምና ባለሙያ ላልሆነ ግለሰብ አስቸጋሪ እንደሚሆን ይታወቃል። ስለሆነም በተለይ በቤት ውስጥ ህይወታቸው ያለፈ ወይም ቀደም ሲል ህመም ሳይኖራቸው ድንገት ህይወታቸው ያለፈ ሰዎች የሞት ምክንያት ሲመዘገብ አስመዝጋቢው ሟቹ ቀደም ሲል የነበረውን የህመም ወይም የበሽታ ዓይነት በማስታወስና ከአሟሟቱ ጋር በማገናዘብ የሞቱን ምክንያት እንዲያስመዘግብ ማድረግ ያስፈልጋል። በተለይም የህክምና ዕርዳታ ሳያገኙ በቤት ውስጥ ህይወታቸው ያለፈ ህፃናትን የሞት መንስኤ ማወቅ አስቸጋሪ እንደሚሆን ይገመታል። የጤና ሥርጭትና አቅርቦት እየሰፋ ሲሄድ ሰዎች በህመማቸው ወቅት ወደ ጤና ማዕከል የመሄዳቸው ዕድል እየሰፋ ይሄዳል። ከዚህም በላይ የጤና ግልጋሎት አቅርቦት በገጠርና በከተማ እየጨመረ ሲሄድ በጤና ተቋም ሳይታዩ በቤት ውስጥ ህይወታቸው የሚያልፍ ህፃናትም ሆኑ አዋቂዎች ቁጥር እንደሚቀንስ ስለሚገመት የሞት ምክንያት መረጃን በትክክል የማግኘቱ ጉዳይ ወደፊት እየተሻሻለ እንደሚሄድ ይጠበቃል። ዋና ዋና የሞት መንስዔዎች/ምክንያቶች ዝርዝር በዕዝል _______ ተያይዞ ቀርቧል።

2.12 <u>ሟች የሞተበት ቀን</u>

ሟች የሞተበት/ችበት ቀን፣ ወር እና ዓ.ም ይመዘገባል። በዚሁም መሠረት ለምሳሌ ሟች የሞተው ጥቅምት 10 ቀን 1997 ዓ.ም ከሆነ በተሰጠው ክፍት ቦታ ቀን በሚለው ሥር "10"፣ ወር በሚለው "ጥቅምት" እና ዓመተ ምህረት በሚለው ሥር "1997" በማለት ይመዘገባል።

## 2.13 ሟች የሞተበት/ ችበት ስፍራ (ተቋም)

ሟች ህይወቱ ያለፈው ከህክምና ተቋም ውጪ ወይም በጤና ተቋም ውስጥ መሆኑ ተጠይቆ አስመዝጋቢው የሚሰጠው መልስ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። ሟች ህይወቱ ያለፈው በጤና ተቋም ውስጥ የሆነ እንደሆነ የተቋሙ ዓይነትና ደረጃ ተገልጾ ይመዘገባል። ለምሳሌ የመንግሥት ሆስፒታል፣ የመንግሥት ጤና ጣቢያ፣ የግል ጤና ጣቢያ፣ … ወዘተ በማለት ተገልፆ መመዝገብ አለበት። ሟች ህይወቱ ያለፈው እቤት ውስጥ ከሆነ "ከጤና ተቋም ውጪ በቤት ውስጥ" ተብሎ ይመዘገባል። በሌላም በኩል ሟች በአደጋም ይሁን በበሽታ ምክንያት ህይወቱ ያለፈውና አስከሬኑ የተገኘው ከቤት ውጭ ማለትም በመንገድ ላይ፣ ጫካ፣ ጉድጓድ፣ …ወዘተ ከሆነ እንደሁኔታው "ከቤት ውጭ መንገድ ላይ" በሚል ተለይቶ ይመዘገባል። ለአመዘጋገብ የመች ዘንድ ሟች የሞት ሥፍራ ዝርዝር ከታች ተመልክቷል።

- የመንግስት ሆስፒታል
- የመንግስት ጤና ጣቢያ
- የመንግሥት ክሊኒክ
- የመንግስት ጤና ኬላ
- የግል ሆስፒታል
- የግል ጤና ጣቢያ
- የግል ክሊኒክ
- መንግስታዊ ያልሆነ የዕርዳታ ጤና ተቋም/ድርጅት
- በቤት ውስጥ
- በመንገድ ላይ (ጫካ ውስጥ፣ ጉድጓድ፣…)
- በማረሚያ ቤት፣ ሕፃናት ማሳደጊያ፣ የጦር ካምፕ/ማገገሚያ፣ . . . ወዘተ

## 2.14 ሞቱ የተመዘገበበት ቀን

የሟቹ የሞት ኩነት የተመዘገበበት ቀን፣ ወር እና ዓመተ ምሕረት በቅደም ተከተል በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባሉ። ሟች የሞተበት ቀን ሞቱ ከተመዘገበበት ቀን ጋር ተመሳሳይ ላይሆን ይችላል። ሟች የሞተበት ቀን እና ሞቱ የተመዘገበበት ቀን አንድ ሊሆን የሚችለው ሟች ህይወቱ ባለፈበት ዕለት አስመዝጋቢው ሞቱን ያስመዘገበ እንደሆነ ብቻ ነው።

## 2.15 የሞት ምዝገባ መለያ ቁጥር

የሞት ኩነቱ በተመዘገበበት ቅደም ተከተል መሠረት ለኩነቱ የተሰጠው የምዝገባ መለያ ቁጥር ይመዘገባል። መዝጋቢው በዓመቱ መጀመሪያ ምዝገባ በሚጀምርበት ጊዜ በሞት የክብር መዝገቡ ውስጥ መጀመሪያ ለመዘገበው የሞት ኩነት "0001" በሚል ተራ ቁጥር ጀምሮ ሌሎችንም ሞቶች በቅደም ተከተል "0002" ፣ "0003" ፣ ወዘተ ተራ ቁጥር ይሰጣቸዋል። ከዚህ ቁጥር በኋላ ሞቱ የተከሰተበትን በዓመት ሊያመለክት በሚችል መልክ ሞቱ የተከሰተበት ዓመተ ምህረት ተከትሎ ይመዘገባል። በመሆኑም ለምሳሌ በ1997 ዓ.ም በቀበሌው በሞት የክብር መዝገብ መጀመሪያ ለተመዘገበው ሞት "0001-97"፣ ለሁለተኛው ሞት "0002-97"፣ ለሶስተኛው

ሞት "0003-97"፣ ...ወዘተ በማለት የሞት የምዝገባ መለያ ቁጥር በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል።

2.16 በሞት ጊዜ የተደረገ እርዳታ

ሟች ህይወቱ ያለፈው በቤት ውስጥ የሆነ እንደሆነ ሟቹ በመጨረሻው የህመሙ ወቅት በዘመናዊ ሃኪም ወይም በባህላዊ መድሃኒት አዋቂ እርዳታ ተደርጎለት ከሆነ ይኸው ተጠይቆ ይመዘገባል። በሌላም በኩል ሟች በመጨረሻ የህመሙ ወቅትም ቢሆን ወደ ህክምና ተቋም በመሄድ በሃኪም ዕርዳታ አግኝቶ ከነበረ ይኸው ይገለፃል። የሞት አስመዝጋቢውን መልስ መሠረት በማድረግ በሟች የመጨረሻ የህመም ጊዜ የተደረገ ዕርዳታ ዓይነት ከታች በተመለከተው አኳኋን በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል።

- የሀኪም ዕርዳታ በህክምና ተቋም አግኝቷል
- የሀኪም ዕርዳታ በቤት ወስጥ አግኝቷል
- በባህል መድሃኒት አዋቂ በቤት ውስጥ ዕርዳታ አግኝቷል
- ምንም ዕርዳታ አላገኘም።

## ክፍል 3 አስመዝጋቢን የሚመለከት

3.1 የአስመዝጋቢው ሙሉ ስም

የአስመዝጋቢ የግል ስም፣ የአባት ስምና የአያት ስሞች ይመዘገባሉ። በዚህ ክፍል የሞቱን አስመዝጋቢ የሚመለከቱ መረጃዎች ይመዘገባሉ። የሞት ኩነት የማስመዝገብ ቅድሚያ ኃላፊነት የተጣለበት የሟች የቅርብ የጋብቻ ወይም የስጋ ዘመድ ነው። በሌላም በኩል የሟች አስከሬን በተቋማት (የጤና ተቋም፣ ፖሊስ፣ ...ወዘተ) እጅ ያለ ከሆነ ሞቱን ማስመዝገብ ያለበት የተቋሙ ኃላፊ ነው። ስለሆነም የአስመዝጋቢው ስም በሚለው ሥር ሞቱን ያስመዘገበው ግለሰብ ወይም ተቋም ሊሆን ስለሚችል እንደሁኔታው ስሙ ይመዘገባል።

3.2 አስመዝጋቢው ለሟች ያለው የዝምድና ዓይነት

አስመዝጋቢው ከሟቹ ጋር ያለው ዝምድና ተጠይቆ ይመዘገባል። የሟች አስከሬን ወድቆ የተገኘና የተመዘገበው በፖሊስ አማካይነት የሆነ እንደሆነ በተሰጠው ክፍት ቦታ "ፖሊስ" ተብሎ ይመዘገባል።

3.3 የአስመዝጋቢው መደበኛ መኖሪያ ቦታ

የአስመዝጋቢው መደበኛ መኖሪያ ቦታ የሚገኝበት ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ከተማ፣ ቀበሌ፣ የቤት ቁጥር እንዲሁም የቤት ቁጥር በሌለበት የገጠር ቀበሌ የሚኖር/የምትኖር ከሆነ የመንደሩ ልዩ ስም ይመዘገባል።

3.4 የአስመዝጋቢ ፊርማና ቀን

በሞት መዝገብ የተመዘገቡት መረጃዎች ለአስመዝጋቢው ከመዝገቡ እየተነበቡ ከተገለፀ እና በአስመዝጋቢው ከታመነባቸው በኋላ አስመዝጋቢው የሰጠው መረጃ ትክክል ስለመሆኑ በፊርማው ማረጋገጥ ዕለቱን (ቀኑን) በመፃፍ ይገልፃል።

## ክፍል 4 ለሞት ማረጋገጫ የቀረበ ማስረጃ

በዚህ ክፍል የሞት ኩነቱ በእርግጥ የተከሰተ መሆኑን የሚገልፀው ማስረጃ ዓይነት የሚገለፅበት ነው።

4.1 የሀኪም የሞት የሜዲካል የምስክር ወረቀት

ሟቹ የሞተው በጤና ተቋም ውስጥ ከሆነና በምዝገባ ወቅት ማስረጃ ከቀረበ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ በሞት የሜዲካል የምስክር ወረቀቱ ላይ የተፃፈውን የምዝገባ ቁጥር እና ሟች የሞተበት የጤና ተቋም ስም ይመዘገባል።

4.2 የዓይን ምስክሮችን የሚመለከት

ሟች መሞቱን የሚያረጋግጡ ሶስት የዓይን ምስክሮች ሙሉ ስም (የግል ስም፣ የአባት፣ የአያት ስሞች) ይመዘገባል። የምስክሮች መደበኛ መኖሪያ ቦታ ማለትም ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ከተማ፣ ቀበሌ እና የቤት ቁጥር እንዲሁም የቤት ቁጥር በሌለበት የገጠር መንደር የመንደሩ ልዩ ስም በተዘጋጀው ክፍት ቦታ ይመዘገባል። በተጨማሪም የዓይን ምስክሮች ሞቱ ስለመከሰቱ የሰጡት ቃል ትክክል ስለመሆኑ በፊርማቸው በማረጋገጥ ዕለቱን (ቀኑን) በመፃፍ ይገለፃል።

## ክፍል 5 አስተያየት

ማናቸውም ከሟች ጋር የተያያዙና በሌሎች ክፍሎች ያልተጠቀሱ ጠቃሚነት አላቸው ተብለው የሚገመቱ መረጃዎች በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይጻፋሉ።

## ክፍል 6. የመዝጋቢ ስም፣ ፊርማና ቀን

በዚህ ክፍል መዝጋቢው በሞት መዝገብ የሞላው መረጃ ትክክል መሆኑን ሙሉ ስሙን፣ ፊርማውንና ዕለቱን በመግለፅ ያረጋግጣል።

6.1 የመዝጋቢ ሙሉ ስም

የመዝጋቢው የግል ስም፣ የአባት ስምና የአያት ስም በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባሉ።

6.2 የመዝጋቢ ፊርማና ቀን

መዝጋቢው አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ተሟልተው የሞቱ ኩነት ምዝገባ በትክክል ለመከናወኑ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ፊርማውን በማስቀመጥ የሚያረጋግጥበት ነው። በተጨማሪም መዝጋቢው ምዝገባውን ያጠናቀቀበትን ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት በመጥቀስ ያሰፍራል።

## 3.3 የጋብቻ የወሳኝ ኩነት መረጃ አመዘጋገብ

በጋብቻ የሕዝብ የክብር መዝገብ ውስጥ የሚሠፍሩት መረጃዎች ከዚህ በታች የተመለከተውን የአመዘጋገብ መመሪያ መሠረት በማድረግ ይመዘገባሉ። የወሳኝ ኩነቶች መዝጋቢ ከአስመዝጋቢዎች፣ ከጠቋሚዎች፣ ከተለያዩ ተቋማት ባገኛቸው መረጃዎችና በራሱ ያወቃቸውን የጋብቻ ኩነቶች ይመዘግባል።

የጋብቻ ኩነትን በቀዳሚነት የማስመዝገብ ግዴታ የተጣለባቸው ሁለቱ ተጋቢዎች ናቸው። የጋብቻ ሥነ ሥርዓቱን ያስፈጸሙ ተቋማት ኃላፊዎችና ሽማግሌዎችም የጋብቻውን ክስተት ማስታወቅና የማስመዝገብ ግዴታ አለባቸው። በመሆኑም በጋብቻ መዝገቡ ውስጥ የሚመዘገቡ መረጃዎችን መዝጋቢው ከዚህ በታች ስለጋብቻ ምዝገባ የተሰጡትን አጠቃላይ መመሪያዎችና የምዝገባ ሕጉን መሠረት በማድረግ መረጃዎቹን በትክክል መመዝገብ ይጠበቅበታል። በተጨማሪም የጋብቻ ኩነትን በተመለከተ የሚከተሉት ጉዳዮች ትኩረት ሊያገኙ ይገባል።

1ኛ/ የጋብቻው ሥነ-ሥርዓት የተከናወነው በሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም ፊት የሆነ እንደሆነ የኩነቱ ተጓዳኝ መረጃዎች በጋብቻ የሕዝብ የክብር መዝገብ ውስጥ አስቀድመው ይሰፍራሉ። በሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም ፊት (የሲቪል ጋብቻው) የተፈፀመው ጋብቻ ከምዝገባ ቀበሌው (ከባል/ሙሽራው መደበኛ መኖሪያ) ውጭ ከሆነ ጋብቻውን ያስፈፀመው አካል ሙሽራው ወይም ሙሽሪት (በአንዳቸው ቢሆን ይመረጣል) በመደበኛነት ለሚኖሩበት ቀበሌ የሕዝብ የክብር መዝገብ የሥራ ክፍል ማሳወቅ አለባቸው። በዚህም ወቅት የጋብቻ ኩነቱን መዝገብ ቅጂ ከጋብቻ ምስክር ወረቀት ጋር በማያያዝ ለቀበሌው የሕዝብ የክብር መዝገብ የሥራ ክፍል መላክ ይገባል።

2ኛ/ የጋብቻው ሥነ-ሥርዓት የተከናወነው በሃይማኖት ተቋም በሃይማኖታዊ ሥርዓት የሆነ እንደሆነ የተቋሙ ኃላፊ የጋብቻ ኩነት መከሰቱን በፊርማቸውና የተቋሙ ማህተም ባረፈበት ማስረጃ አስደግፈው ተቋሙ ለሚገኝበት ቀበሌ የሕዝብ የክብር መዝገብ የሥራ ክፍል የምስክር ወረቀቱን መላክ አለባቸው። በተመሳሳይ ተጋቢዎቹ ከሃይማኖት ተቋሙ የተሰጣቸውን የጋብቻ የምስክር ወረቀት በመያዝ ሙሽራው ወይም ሙሽሪት (በአንዳቸው ቢሆን ይመረጣል) በመደበኛነት ለሚኖሩበት ቀበሌ የሕዝብ የክብር መዝገብ የሥራ ክፍል ቀርበው ጋብቻውን ማስመዝገብ አለባቸው።

3ኛ/ የጋብቻው ሥነ-ሥርዓት የተከናወነው በባህል ወይም በአካባቢው ልማድ በሽማግሌዎች የሆነ እንደሆነ ሥርዓቱን ያከናወኑት ሽማግሌዎች ስምና ፊርማ ያለበት የጽሑፍ ማስረጃ (የጋብቻ ውል ቅጂ) ተዘጋጅቶ የጋብቻ ሥርዓቱን ባስፈፀሙ ሽማግሌዎች ዋና ኃላፊ አማካይነት ሙሽራው ወይም ሙሽሪት (በአንዳቸው ቢሆን ይመረጣል) በመደበኛነት

ለሚኖሩበት ቀበሌ የሕዝብ የክብር መዝገብ የሥራ ክፍል ጋብቻውን ማሳወቅ ያስፈልጋል። በተመሳሳይ ተጋቢዎቹ በባህላዊ ሥርዓቱ የተሰጣቸውን የጋብቻ ማስረጃ በመያዝና በሙሽራው ወይም ሙሽሪት መደበኛ መኖሪያ ቀበሌ የሕዝብ የክብር መዝገብ የሥራ ክፍል ቀርበው ጋብቻውን ማስመዝገብ ይኖርባቸዋል።

በመሆኑም መዝጋቢው ከላይ የተገለጹትንና *በምዝገባ ሕጉ* በዝርዝር የሚደነገጉትን የአመዘጋገብ ሥርዓቶች ተከትሎ በጋብቻ የሕዝብ የክብር መዝገቡ ውስጥ ተፈላጊዎቹን መረጃዎች መመዝገብ ይጠበቅበታል።

መዝጋቢው በጋብቻ የሕዝብ የክብር መዝገቡ ውስጥ ላሰፈራቸው መረጃዎች ትክክለኛነት በሕግ ተጠያቂነት ስላለበት በምዝገባው ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅበታል።

## ክፍል 1 <u>የምዝገባ አካባቢ መለያ</u>

በዚህ ክፍል ጋብቻው በሕዝብ የክብር መዝገብ የሚመዘገብበት ቀበሌ የሕዝብ የክብር መዝገብ የሥራ ክፍል የሚገኝበት ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ከተማ፣ የቀበሌ ስም ወይም ቁጥር እና የምዝገባ ጽ/ቤቱ የሚገኝበት ቤት የቤት ቁጥር ወይም በገጠር የቤት ቁጥር ከሌለው የመንደሩ ልዩ ስም ይመዘገባል።

### 1.1 <u>የክልል ስም</u>

"የክልል ስም" በሚለው ክፍት ቦታ ምዝገባው የሚካሄድበት ቀበሌ የሚገኝበት ክልል ስም ይመዘገባል።

### 1.2 <u>የዞን ስም</u>

"የዞን ስም" በሚለው ሥር ምዝገባው የሚካሄድበት ቀበሌ የሚገኝበት ዞን ስም በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል።

### 1.3 <u>የወረዳ ስም</u>

"የወረዳ ስም" በሚለው ክፍት ቦታ ላይ ምዝገባው የሚካሄድበት ቀበሌ የሚገኝበት ወረዳ ስም ይመዘገባል።

### 1.4 <u>የከተማ ስም</u>

ምዝገባው የሚካሄድበት ቀበሌ የሚገኘው በከተማ ሥር ከሆነ በተሰጠው ክፍት ቦታ "የከተማው ስም" ይመዘገባል።

1.5 የከተማ ቀበሌ ስም ወይም ቁጥር

ምዝገባው የሚካሄድበት የከተማ ቀበሌ ነዋሪዎች ማህበር ስም ወይም ቁጥር በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል።

1.6 የገጠር ቀበሌ (ገ/ማህበር) ስም ወይም ቁጥር

ምዝገባው የሚካሄድበት ቀበሌ የሚገኘው በገጠር ከሆነ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ የገጠር ቀበሌው ስም ወይም ቁጥር ይመዘገባል።

1.7 የምዝገባ ጽ/ቤት የቤት ቁጥር (በከተማ)

የቀበሌው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የሥራ ክፍል የሚገኝበት ቤት የቤት ቁጥር ይመዘገባል። በከተማ ቤቱ የሚለየው ለቤቱ የቀበሌው መስተዳድር በሰጠው የቤት ቁጥር አማካይነት ነው። በዚሁም መሠረት ቀበሌው ለቤቶች ሥርዓትን ተከትሎ የቤት ቁጥር እንዲሰጥ "በሚያዘው መመሪያ" መሠረት የምዝገባ የሥራ ክፍሉ ለሚገኝበት ጽ/ቤት የተሰጠው የቤት ቁጥር ይመዘገባል። ቤቱ ንዑስ ቁጥር ወይም ፊደል ካለው ከቤቱ ቁጥር ጋር አብሮ ይመዘገባል።

1.8 የምዝገባ ጽ/ቤት የሚገኝበት የመንደር ልዩ ስም እና የቤት ቁጥር (በገጠር)

በገጠር መኖሪያ ቤቶችም ሆኑ የድርጅት ቤቶች የመለያ የቤት ቁጥር ላይሰጣቸው ይችላል። ሆኖም የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባን በማከናወን ቤተሰቦችን ለመለየትና አድራሻቸውን ለማወቅ አልፎም የምዝገባ ጽ/ቤቶችን ለመለየት ለቤቶች ሥርዓትን የተከተለ የቤት ቁጥር መስጠት አስፈላጊ ነው። ስለሆነም ቤቶችን በሥርዓት የቤት ቁጥር የመስጠት አሰራርን በገጠር ቀበሌዎች ማስፈጸን የምዝገባው አንድ አካል አድርጎ መውሰድ ያስፈልጋል። በዚሁም መሠረት ቀበሌው ለቤቶች ሥርዓትን ተከትሎ የቤት ቁጥር እንዲሰጥ "በሚያዘው መመሪያ" መሠረት የምዝገባ የሥራ ክፍሉ ለሚገኝበት ጽ/ቤት የተሰጠው የቤት ቁጥር እና የመንደሩ ልዩ ስም ይመዘገባል።

## ክፍል 2 ጋብቻውን የሚመለከት

በዚህ ክፍል ጋብቻውን የሚመለከቱ መረጃዎች ተጋቢዎችን በመጠየቅና ከተለያዩ ተቋማት የተገኙ መረጃዎችን በመመርመር ይመዘገባሉ።

2.1 ጋብቻው የተፈጸመበት ቀን

ተጋቢዎቹ በሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም ፊት ቀርበው የሲቪል ጋብቻ ወይም በሃይማኖታቸው (በሁለቱም ወይም በአንዳቸው የሃይማኖት ሥርዓት በሃይማኖት አባቶች ፊት ቀርበው) ወይም በባህላቸው (በሁለቱም ወይም በአንዳቸው ባህል በሽማግሌዎች ፊት ቀርበው) መሠረት የጋብቻውን ሥርዓት የፈፀሙበት ቀን፣ ወር እና ዓመተ ምሕረት በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል።

2.2 የጋብቻው ዓይነት /ሲቪል፣ ሃይማኖታዊ ወይስ ባህላዊ/

ተጋቢዎቹ በየትኛው የጋብቻ ሥርዓት እንደተጋቡ በመጠየቅና የሚያቀርቡትን ማስረጃ በመመርመር የጋብቻው ዓይነት በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል።

- ሲቪል/ብሔራዊ ጋብቻ
- ሐይማኖታዊ ጋብቻ
- ባህላዊ ጋብቻ

በኢትዮጵያ ፍትሀ-ብሄር ሕግ በቁጥር 577 መሠረት ሦስቱም የጋብቻ ዓይነቶች በሕግ ፊት እኩል ተቀባይነት አላቸው።

2.3 ጋብቻው የተፈጸመበት ቦታ

ተጋቢዎቹ የጋብቻ ሥነ ሥርዓታቸውን ያከበሩበት ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ከተማ እና ቀበሌ ስም ወይም ቁጥር እንዲሁም የቤት ቁጥር ይመዘገባል። የጋብቻ ሥርዓት አፈፃፀምና አከባበር እንደ ባህሉ፣ ሃይማኖቱና የጋብቻው ዓይነት ይለያያል። በሲቪል ጋብቻ አፈፃፀም ተጋቢዎች በሕዝብ የክብር ሹም ፊት ቀርበው የቀለበት ልውውጥ ሥርዓቱ የተፈፀመበት ቦታ ጋብቻ የተፈፀመበት ቦታ ተደርጎ ይወሰዳል። በተመሳሳይ የተለያየ ባህልና የሃይማኖት ሥርዓት በመከተል የቀለበት ሥርዓት ወይም የጋብቻ ውል በመፈፀም ጋብቻቸውን ላከበሩ ተጋቢዎች ጋብቻው የተፈፀመበት ሥፍራ የሚባለው የቀለበት ሥርዓቱ ወይም የጋብቻ ውል የተፈፀመበት ተደርጎ ይወሰዳል። ሆኖም የቀለበት ሥርዓት ሳይፈጽሙ ጋብቻቸውን በጽሁፍ ፊርማ ያከናወኑ ወይም እንደ ባህሉ በሽማግሌዎች ፊት ቃል ኪዳን የተለዋወጡ ተጋቢዎች ጋብቻ የተፈፀመበት ሥፍራ የሚባለው ፊርማው ወይም በሽማግሌዎች ፊት ሙሽሮች ቃልኪዳን የተለዋወጡበት ተቋም ወይም መኖሪያ ቤት ወይም ሌላ ቦታ ይሆናል።

2.4 ጋብቻው የተመዘገበበት ቀን

ጋብቻው በሕዝብ የክብር መዝገብ የተመዘገበበት ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት በቅደም ተከተል በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባሉ።

2.5 የጋብቻ ምዝገባ መለያ ቁጥር

የጋብቻው ኩነት በሕዝብ የክብር መዝገብ ውስጥ በሚመዘገብበት ጊዜ ለኩነቱ የተሰጠው የምዝገባ መለያ ቁጥር ይመዘገባል። መዝጋቢው በዓመቱ መጀመሪያ ምዝገባ በሚጀመርበት ጊዜ በጋብቻ የክብር መዝገቡ ውስጥ መጀመሪያ ለመዘገበው የጋብቻ ኩነት "0001" በሚል ተራ ቁጥር ጀምሮ ሌሎችን ኩነቶች በቅደም ተከተል "0002"፣ "0003" . . . ወዘተ ተራ ቁጥር ይሰጣቸዋል። ከዚህ ተራ ቁጥር በኋላ ጋብቻው የተከሰተበትን ዓመት ሊያመለክት በሚችል መልክ ጋብቻው የተፈጸመበት ዓመተ ምህረት ተከትሎ ይመዘገባል። በመሆኑም ለምሳሌ በ1997 ዓ.ም በቀበሌው የጋብቻ የክብር መዝገብ መጀመሪያ ለተመዘገበ ጋብቻ "0001-97"፣ ለሁለተኛው ጋብቻ "0002-

97፤ ለሶስተኛው ጋብቻ "0003-97"፣ ... ወዘተ በማለት የጋብቻ የምዝገባ መለያ ቁጥር በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል።

## ክፍል 3. ሙሽራውን የሚመለከት

በዚህ ክፍል ሙሽራውን የሚመለከቱ መረጃዎች ሙሽራውን በመጠየቅና ከተለያዩ ተቋማት የተገኙ መረጃዎችን በመመርመር ይመዘገባሉ።

### 3.1 የሙሽራው ሙሉ ስም

የሙሽራው የግል ስም፣ የአባት ስምና የአያት ስም በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባሉ። ሙሽራው የግል የመለያ ስም ሊወሰድ ይገባ የነበረው ሙሽራው ሲወለድ ከተመዘገበ የልደት የምስክር ወረቀት ላይ ነበር። ሆኖም ከዚህ በፊት ተደጋግሞ እንደተገለጸው እስከተወሰኑ ዓመታት በአግባባዊው አሠራር የተዘጋጁ የልደት የምስክር ወረቀቶች የማይኖሩ በመሆኑ ያለው አማራጭ በወቅቱ ሙሽራው በቀበሌ መስተዳድር ጽ/ቤት በሚሰጠው የነዋሪነት መታወቂያ ላይ የተጠቀሰውን ስም ወስዶ መመዝገብ ነው። ይሽም ሲሆን በቀበሌ ነዋሪነት መታወቂያ ላይ የተገለጸው መለያ ስም ትክክል ለመሆኑ ሙሽራውን መጠየቅ አልፎም አጠራጣሪ ሁኔታዎች ከታዩ መታወቂያውን የሰጠውን አካል በመጠየቅ ማጣራት ያስፈልጋል።

### 3.2 የሙሽራው ዕድሜ

ሙሽራው ጋብቻውን በፈጸመበት/በሚፈጽምበት ጊዜ የነበረው ትክክለኛ ዕድሜ በሙሉ ዓመት (በጨረሰው ዓመት) በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። ከዚህ በፊት በተለያዩ ቦታዎች እንደተገለጸው የማንኛውም ሰው ትክክለኛ ዕድሜ ሊታወቅ የሚችለው ግለሰቡ በተወለደበት ጊዜ በኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት አማካይነት በተሰጠው የምስክር ወረቀት አማካይነት ነበር። ይህ ሁኔታ የተሟላ ከሆነ ዕድሜው ከተፈለገበት ቀን ላይ የተወለደበትን ቀን በማቀናነስ ትክክለኛ የዕድሜ መረጃ ማግኘት ይቻላል። በኩነቶች ምዝገባ አማካይነት የተገኘ የልደት የምስክር ወረቀት ለሌላቸው ግለሰቦች የተወለዱበትን ትክክለኛ ዕድሜ ጠይቆና እንዲያስታውሱ በማድረግ ዕድሜአቸውን ማግኘት ያስፈልጋል። በዚህ መንገድ የሚገኘው የዕድሜ መረጃ ትክክለኛነት በግለሰቡ የልደት ቀኑን በጽሑፍ ማስታወሻ መያዝ ልምድና የማስታወስ ችሎታ ላይ ይመሠረታል። ዕድሜ በሙሉ ዓመት ማለት ከሙሉ ዓመት በተጨማሪ ያሉትን ወሮችንና ቀኖችን በመተው ዓመቱን ብቻ በመውሰድ ዕድሜውን መመዝገብ ነው። ለምሳሌ የሙሽራው ዕድሜ በጋብቻው ዕለት 20 ዓመት ከ6 ወራት ከ29 ቀናት ከሆነ መመዝገብ ያለበት 20 ዓመት ብቻ ነው።

ዕድሜውን በትክክል ለማያውቅ ሙሽራ በተወለደበት ጊዜ/አካባቢ በብሔራዊ ደረጃ ወይም በሚኖርበት አካባቢ የተፈጸሙ ታሪካዊ ድርጊቶች እንዳሉና ሙሽራው ድርጊቱ በተፈጸመበት

ጊዜ ዕድሜው ስንት እንደነበረ ወይም ከድርጊቱ በኋላ/በፊት ምን ያህል ጊዜ ቆይቶ እንደተወለደ ጠይቆ በሚገኘው መረጃ ዕድሜውን በማስላት መመዝገብ ያስፈልጋል።

ከዚህም ሌላ ሙሽራው የአንዳንድ የቤተሰቡን አባላት ወይም የአካባቢ ነዋሪዎች ዕድሚ በትክክል ሊያውቅ ከቻለ ከነዚህ ግለሰቦች ዕድሜ ጋር በማነጻጸር ዕድሜውን መገመት ይቻላል።

### 3.3 የሙሽራው ብሔረሰብ

የሙሽራው ብሔረሰብ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። ሙሽራው የብሔረሰብን ትርጉም በትክክል እንዲረዳ ትውልድ፣ ነገድ፣ ዘር፣ ጎሳ፣ . . . በማለት ማብራራት ሊያስፈልግ ይችላል። የዋና ዋና እና የቅርንጫፍ ብሔረሰቦች ስም ዝርዝር በዕዝል 1 ተያይዞ ቀርቧል።

### 3.4 የሙሽራው ሃይማኖት

የሙሽራው እምነት ወይም የመንፈሳዊ ድርጅት አባልነት ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። በኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ የሃይማኖት ዓይነቶች ይታወቃሉ። አመዳደባቸውም ከታች ተመልክቷል።

- ኦርቶዶክስ (ተዋህዶ፣ ቅባት፣ ፀጋ)
- ፕሮቴስታንት (ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት፣ ሙሉወንጌል፣ ሉትራን፣ መካነ ኢየሱስ፣ ባፕቲስት፣ ሜኖናይት፣ አንግሊካን፣ ፕሪስፒተሪያን፣ ...ወዘተ)
- ካቶሊክ
- ሙስሊም (እስላም)
- ባህላዊ አምልኮ
- ሌላ (ሂንዱ፣ ይሁዲ፣ በሃይ፣ ጀሆባ፣ ቡድሂስት፣ ኢቴስት፣ ...ወዘተ)

ሙሽራው ከላይ ከተጠቀሱት እምነቶች የየትኛው ዕምነት ተከታይ እንደሆነ ተጣርቶ ትክክለኛውን የሃይማኖት ስም መመዝገብ ያስፈልጋል። በአመዘጋገብ ወቅት በተለይ ዕምነታቸው ፕሮቴስታንት ለሆኑ በርከት ያሉ የዕምነቱ የአጠራር ዓይነቶች ስለሚኖሩ የቅርንጫፍ ስሙን በመግለጽ መፃፍ ያስፈልጋል። ለምሳሌ ሙሽራው ሃይማኖቱ ሙሉ ወንጌል ነው ካለ መመዝገብ ያለበት ፕሮቴስታንት ሳይሆን "ሙሉ ወንጌል" ይሆናል።

### 3.5 የሙሽራው መደበኛ መኖሪያ ቦታ

የሙሽራው መደበኛ መኖሪያ ቦታ ማለትም ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ከተማ፣ ቀበሌ እና የቤት ቁጥር እንዲሁም በገጠር የቤት ቁጥር በሌለበት የመንደሩ ልዩ ስም ይመዘገባል።

### 3.6 የሙሽራው ዜግነት

የአንድ ግለሰብ የኢትዮጵያዊ ዜግነት ጉዳይ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የዜግነት ህግን መሠረት በማድረግና በመለየት ይመዘገባል።

## 3.7 የሙሽራው ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ

የሙሽራው የትምህርት ደረጃ ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። በቅድሚያ ሙሽራው ማንበብና መጻፍ መቻል አለመቻሉ ተጠይቆ ማንበብና መጻፍ አልችልም ካለ ማንበብና መፃፍ የማይችል" ተብሎ ይመዘገባል። አንድ ግለሰብ የማንበብና የመፃፍ ችሎታ አለው የሚባለው ቢያንስ በአንድ ቋንቋ አንብቦ መረዳትና እንዲሁም መፃፍ ሲችል ነው። የራሳቸውን ስም ወይንም ቁጥሮችን ብቻ ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ግለሰቦች የትምህርት ችሎታ እንዳላቸው አይቆጠሩም። እንዲሁም ሃይማኖት ነክ የሆኑና ቀደም ብለው በቃል የተጠኑ ዐረፍተ ነገሮችን ብቻ መድገም የሚችሉ የማንበብና የማፃፍ ችሎታ እንዳላቸው አይቆጠሩም። ሆኖም ግን መደበኛ በሆነ ት/ቤት ሳይገቡ በመሰረተ ትምህርት ፕሮግራም፣ በቄስ፣ በቁርዓንና በመሳሰሉት በመከታተል እንዲሁም በራሳቸው ጥረት የግለሰቦችን እርዳታ እየጠየቁ ማንበብና መፃፍ የቻሉ ሰዎች ማንበብና መፃፍ እንደሚችሉ በመውሰድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ "መደበኛ ያልሆነ ትምህርት የተከታተለ" ተብሎ ይመዘገባል። ሙሽራው የጨረሰው ከፍተኛ ክፍል አመዘጋገብ እንደ ሙሽራው የትምህርት ደረጃ ወይም በወቅቱ በትምህርት ላይ መሆን አለመሆን ሊለያይ ይችላል። ይኸም ሲባል ባለው የትምህርት ስርዓት በመደበኛ ትምህርት እየተማረ ያለ ወይም የጨረሰ ወይንም ያቋረጠ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ሙሽራው 6ኛ ክፍል እየተማረ ከሆነ ያጠናቀቀው ከፍተኛ ክፍል "5ኛ ያጠናቀቀ" ተብሎ ይመዘገባል። በተመሳሳይ ሙሽራው የዲግሪ ትምህርት ተከታትሎ ዲግሪ ያለው ከሆነ የሚመዘገበው "ዲግሪ ያለው" በማለት ነው። ለአመዘጋገብ ያመች ዘንድ የከፍተኛ ትምህርት ደረጃ ዝርዝር ከታች ተመልክቷል።

- ማንበብና መፃፍ አይችልም
- መደበኛ ያልሆነ ትምህርት የተከታተለ
- አንደኛ ክፍል ያጠናቀቀ
- ሁለተኛ ክፍል ያጠናቀቀ
- ሶስተኛ ክፍል ያጠናቀቀ
- አራተኛ ክፍል ያጠናቀቀ
- አምስተኛ ክፍል ያጠናቀቀ
- ስድስተኛ ክፍል ያጠናቀቀ
- ሰባተኛ ክፍል ያጠናቀቀ
- ስምንተኛ ክፍል ያጠናቀቀ
- ዘጠናኛ ክፍል ያጠናቀቀ
- አስረኛ ክፍል ያጠናቀቀ
- አስራ አንደኛ ክፍል ያጠናቀቀ
- 10+2
- 10+3
- 12ኛ ክፍል ያጠናቀቀ
- ሰርተፊኬት ያለው
- ዲፕሎም ያልጨረሰ
- ዲግሪ ያልጨረሰ
- ዲፕሎም ያለው
- የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው
- የማስተርስ ዲግሪ ያላጠናቀቀ
- የዶክትሬት ዲግሪ ያላጠናቀቀ
- የማስተርስ ዲግሪ ያለው
- የዶክትሬት ዲግሪ ያለው
- ፕሮፌሰር

3.8 የሙሽራው የቀድሞ የጋብቻ ሁኔታ

ሙሽራው ይህንን ጋብቻ ከመፈፀሙ በፊት የነበረው የጋብቻ ሁኔታ ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። ሙሽራው ከዚህ በፊት ፈፅሞ ያላገባ ከሆነ "ያላገባ"፣ የፈታ ከሆነ "ፈት" እንዲሁም የቀድሞ ባለቤቱ ሞታበት ከሆነ "የሞተበት" ተብሎ ይመዘገባል። ሙሽራው በወቅቱ ካገባት ሚስት በተጨማሪ ሌላ ሚስት (በህይወት ያለች) ያለው ከሆነ የቀድሞ የጋብቻ ሁኔታው "ፈት" ወይም "ሚስት የሞተበት" ተብሎ አይመዘገብም።

## ክፍል 4 ሙሽራይቱን የሚመለከት

በዚህ ክፍል ሙሽራይቱን የሚመለከቱ መረጃዎች ሙሽራይቱን በመጠየቅና ከተለያዩ ተቋማት የተገኙ መረጃዎችን በመመርመር ይመዘገባሉ።

4.1 የሙሽራይቱ ሙሉ ስም

የሙሽራይቱ የግል ስም፣ የአባትና የአያት ስም በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባሉ። የሙሽራይቱ የግል የመለያ ስም ሊወሰድ ይገባ የነበረው ሙሽራይቱ ስትወለድ ከተመዘገበ የልደት የምስክር ወረቀት ላይ ነበር። ሆኖም ከዚህ በፊት ተደጋግሞ እንደተገለጸው እስከተወሰኑ ዓመታት በአግባባዊው አሠራር የተዘጋጁ የልደት ኩነት የምስክር ወረቀቶች የማይኖሩ በመሆኑ ያለው አማራጭ በወቅቱ ሙሽራይቱ በቀበሌ መስተዳድር ጽ/ቤት በሚሰጠው የነዋሪነት የመታወቂያ ወረቀት ላይ የተጠቀሰውን ስም ወስዶ መመዝገብ ነው። ይኸም ሲሆን በቀበሌ ነዋሪነት መታወቂያ ላይ የተገለጸው መለያ ስም ትክክል ለመሆኑ ሙሽራይቱን መጠየቅ አልፎም አጠራጣሪ ሁኔታዎች ከታዩ መታወቂያውን የሰጠውን አካል በመጠየቅ ማጣራት ያስፈልጋል።

4.2 የሙሽራይቱ ዕድሜ

ሙሽራይቱ ጋብቻውን በፈጸመችበት/በምትፈጽምበት ጊዜ የነበራት/ያላት ትክክለኛ ዕድሜ በሙሉ ዓመት (በጨረሰችው ሙሉ ዓመት) በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። ከዚህ በፊት በተለያዩ ቦታዎች እንደተገለጸው የማንኛውም ሰው ትክክለኛ ዕድሜ ሊታወቅ የሚችለው ግለሰቡ በተወለደበት ጊዜ በኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት አማካይነት በተሰጠው የልደት የምስክር ወረቀት መረጃ አማካይነት ነበር። ይህ ሁኔታ የተሟላ ከሆነ ዕድሜው ከተፈለገበት ቀን ላይ የተወለደችበትን ቀን በማቀናነስ ትክክለኛ የዕድሜ መረጃ ማግኘት ይቻላል። በኩነቶች ምዝገባ አማካይነት የተገኘ የልደት የምስክር ወረቀት ለሌላቸው ግለሰቦች የተወለዱበትን ትክክለኛ ዕድሜ ጠይቆና እንዲያስታውሱ በማድረግ ዕድሜአቸውን ማግኘት ያስፈልጋል። በዚህ መንገድ የሚገኘው የዕድሜ መረጃ ትክክለኛነት ግለሰቡ የልደት ቀንን በጽሑፍ ማስታወሻ የመያዝ ልምድና የማስታወስ ችሎታ ላይ ይመሠረታል። ዕድሜ በሙሉ ዓመት ማለት ከሙሉ ዓመት በተጨማሪ ያሉትን ወሮችንና ቀኖችን በመተው ዓመቱን ብቻ በመውሰድ ዕድሜውን መመዝገብ ነው። ለምሳሌ የሙሽራይቱ ዕድሜ 20 ዓመት ከ6 ወራት ከ29 ቀናት ቢሆን መመዝገብ ያለበት 20 ዓመት ብቻ ነው።

ዕድሜዋን በትክክል ለማታውቅ ሙሽራ በተወለችበት ጊዜ በብሔራዊ ደረጃ ወይም በምትኖርበት አካባቢ የተፈጸሙ ታሪካዊ ድርጊቶች እንዳሉና ድርጊቱ በተፈጸመበት ጊዜ ዕድሜዋ ስንት እንደነበረ ወይም ከድርጊቱ በኋላ/በፊት ምን ያህል ጊዜ ቆይታ እንደተወለደች ጠይቆ በሚገኘው መረጃ የሙሽራይቱን ዕድሜ በማስላት መመዝገብ ያስፈልጋል።

ከዚህም ሌላ ሙሽራይቱ የአንዳንድ የቤተሰቡን አባላት ወይም የአካባቢ ነዋሪዎች ዕድሜ በትክክል ልታውቅ ከቻለች ከነዚህ ግለሰቦች ዕድሜ ጋር በማነጻጸር የሙሽራይቱን ዕድሜ መገመት ይቻላል።

4.3 የሙሽራይቱ ብሔረሰብ

የሙሽራይቱ ብሔረሰብ ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። ሙሽራይቱ የብሔረሰብን ትርጉም በትክክል እንድትረዳ ትውልድ፣ ነገድ፣ ዘር፣ ጎሳ፣ ... በማለት ማብራራት ሊያስፈልግ ይችላል። የዋና ዋና እና የቅርንጫፍ ብሔረሰቦች ስም ዝርዝር በዕዝል 1 ተያይዞ ቀርቧል።

4.4 የሙሽራይቱ ሃይማኖት

ሙሽራይቱ የምትከተለው እምነት ወይም የመንፈሳዊ ድርጅት አባልትነት በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። በኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ የሃይማኖት ዓይነቶች ይታወቃሉ። አመዳደባቸውም ከታች ተመልክቷል።

- ኦርቶዶክስ (ተዋህዶ፣ ቅባት፣ ፀጋ)
- ፕሮቴስታንት (ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት፣ ሙሉ ወንጌል፣ ሉትራን፣ መካነ ኢየሱስ፣ ባፕቲስት፣ ሜኖናይት፣ አንግሊካን፣ ፕሪስፒተሪያን፣ ...ወዘተ)
- ካቶሊክ
- ሙስሊም (እስላም)
- ባህላዊ አምልኮ
- ሌላ (ሂንዱ፣ ይሁዲ፣ በሃይ፣ ጀሆባ፣ ቡድሂስት፣ ኢቴስት፣...ወዘተ)

ሙሽራይቱ ከላይ ከተጠቀሱት እምነቶች የየትኛው ዕምነት ተከታይ እንደሆነች ተጣርቶ ትክክለኛውን የሃይማኖት ስም መመዝገብ ያስፈልጋል። በአመዘጋገብ ወቅት በተለይ ዕምነታቸው ፕሮቴስታንት ለሆኑ በርከት ያሉ የዕምነቱ የአጠራር ዓይነቶች ስለሚኖሩ የቅርንጫፍ ስሙን በመግለጽ መፃፍ ያስፈልጋል። ለምሳሌ የሙሽራይቱ ዕምነት ሙሉ ወንጌል ከሆነ መመዝገብ ያለበት ፕሮቴስታንት ሳይሆን "ሙሉ ወንጌል" ይሆናል።

### 4.5 የሙሽራይቱ መደበኛ መኖሪያ ቦታ

የሙሽራይቱ መደበኛ መኖሪያ ቦታ የሚገኝበት ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ከተማ፣ ቀበሌ እና የቤት ቁጥር እንዲሁም የቤት ቁጥር በሌለበት የገጠር አካባቢ የመንደሩ ልዩ ስም ይመዘገባል።

### 4.6 የሙሽራይቱ ዜግነት

የሙሽራይቱ ዜግነት ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። የአንዲት ግለሰብ ኢትዮጵያዊ ዜግነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የዜግነት ህግን መሠረት በማድረግና በመለየት ይመዘገባል።

### 4.7 የሙሽራይቱ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ

ሙሽራይቱ በማናቸውም ቋንቋ ማንበብና መፃፍ ትችል እንደሆን፣ ከቻለችም ያጠናቀቀችው ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። በቅድሚያ ሙሽራይቱ ማንበብና መጻፍ መቻል አለመቻሏ ተጠይቆ ማንበብና መጻፍ አልችልም ካለች ማንበብና መፃፍ የማትችል” ተብሎ ይመዘገባል። አንድ ግለሰብ የማንበብና የመፃፍ ችሎታ አለው የሚባለው ቢያንስ በአንድ ቋንቋ አንብቦ መረዳትና እንዲሁም መፃፍ ሲችል ነው። የራሳቸውን ስም ወይንም ቁጥሮችን ብቻ ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ግለሰቦች የትምህርት ችሎታ እንዳላቸው አይቆጠሩም። እንዲሁም ሃይማኖት ነክ የሆኑና ቀደም ብለው በቃል የተጠኑ ዐረፍተ ነገሮችን ብቻ መድገም የሚችሉ የማንበብና የመፃፍ ችሎታ እንዳላቸው አይቆጠሩም። ሆኖም ግን መደበኛ በሆነ ት/ቤት ሳይገቡ በመሰረተ ትምህርት ፕሮግራም፣ በቄስ፣ በቁርዓንና በመሳሰሉት በመከታተል እንዲሁም በራሳቸው ጥረት የግለሰቦችን እርዳታ እየጠየቁ ማንበብና መፃፍ የቻሉ ሰዎች ማንበብና መፃፍ እንደሚችሉ በመወሰድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ “መደበኛ ያልሆነ ትምህርት የተከታተለች” ተብሎ ይመዘገባል። ሙሽራይቱ ማንበብና መጻፍ የምትችል ከሆነ የጨረሰችው ከፍተኛ ክፍል አመዘጋገብ እንደ ሙሽራይቱ የትምህርት ደረጃ ወይም በወቅቱ በትምህርት ላይ መሆን ያለመሆን ሊለያይ ይችላል። ይህም ሲባል ባለው የትምህርት ስርዓት በመደበኛ ትምህርት እየተማረች ከሆነ ወይም የጨረሰች ወይንም ያቋረጠች ከሆነ ያጠናቀቀችውን ከፍተኛ የትምህርት ክፍል አመዘጋገብ እንደክፍል ደረጃዋና በወቅቱ ትምህርት እየተከታተለች መሆን ያለመሆኗ ይለያያል። ለምሳሌ 7ኛ ክፍል እየተማረች ከሆነ ያጠናቀቀችው ከፍተኛ ክፍል 6ኛ ያጠናቀቀች ተብሎ መመዝገብ አለበት። በተመሳሳይ ሙሽራይቱ የዲፕሎም ትምህርት ተከታትላ ዲፕሎም ያላት ከሆነ የሚመዘገበው “ዲፕሎም ያላት” በማለት ነው። ለአመዘጋገብ ያመች ዘንድ የከፍተኛ ትምህርት ደረጃ ዝርዝር ከታች ተመልክቷል።

- ማንበብና መፃፍ አትችልም
- መደበኛ ያልሆነ ትምህርት የተከታተለች
- አንደኛ ክፍል ያጠናቀቀች
- ሁለተኛ ክፍል ያጠናቀቀች
- ሶስተኛ ክፍል ያጠናቀቀች
- አራተኛ ክፍል ያጠናቀቀች
- አምስተኛ ክፍል ያጠናቀቀች

- ስድስተኛ ክፍል ያጠናቀቀች
- ሰባተኛ ክፍል ያጠናቀቀች
- ስምንተኛ ክፍል ያጠናቀቀች
- ዘጠነኛ ክፍል ያጠናቀቀች
- አስረኛ ክፍል ያጠናቀቀች
- አስራ አንደኛ ክፍል ያጠናቀቀች
- 10+2
- 10+3
- 12ኛ ክፍል ያጠናቀቀች
- ዲፕሎም ያልጨረሰች
- ዲግሪ ያልጨረሰች
- የመጀመሪያ ዲፕሎም ያላት
- ዲግሪ ያላት
- የማስተርስ ዲግሪ ያላጠናቀቀች
- የዶክትሬት ዲግሪ ያላጠናቀቀች
- የማስተርስ ዲግሪ ያላት
- የዶክትሬት ዲግሪ ያላት
- ፕሮፌሰር

### 4.8 የሙሽራይቱ የቀድሞ ጋብቻ ሁኔታ

ሙሽራይቱ ይህንን ጋብቻ ከመፈፀሟ በፊት የነበራት የጋብቻ ሁኔታ ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ የጋብቻው ዓይነት ይመዘገባል። ከዚህ በፊት ፈጽሞ ያላገባች ከሆነች "ያላገባች"፣ የፈታች ከሆነ "ፈት" እና የቀድሞ ባለቤቷ ሞቶባት የነበረ ከሆነ "የሞተባት" ተብሎ ይመዘገባል።

## ክፍል 5 ለጋብቻው ማረጋገጫ የቀረበ ማስረጃ

በዚህ ክፍል ጋብቻው መፈጸሙን ለማረጋገጥ የቀረቡ ማስረጃዎች ዓይነት ተለይቶ ይመዘገባል። ጋብቻ መፈፀሙን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች በሃይማኖት ተቋማት የተሰጠ የምስክር ወረቀት ወይም በባህላዊ መንገድ ጋብቻ መፈፀሙን የሚያረጋግጥ የጽሁፍ ውል እንዲሁም የዓይን ምስክሮች ሊሆኑ ይችላሉ። የጋብቻውን መፈፀም በዓይን ምስክሮች ማረጋገጥ ያስፈልጋል። በሌላ በኩል ጋብቻው ሲፈፀም የምስክር ወረቀት ወይም ውል ሳይዘጋጅ ሥርዓቱ የተፈፀመ ከሆነ የጋብቻው መከሰት በዓይን ምስክሮች ይረጋገጣል።

### 5.1 የጋብቻ ምስክር ወረቀት ወይም ውል

ተጋቢዎቹ የጋብቻ ሥነ ሥርዓታቸውን በሃይማኖታዊ ሥነ ሥርዓት ፈጽመው ከሆነ ሥነ ሥርዓቱን ካስፈጸሙት ተቋማት የተሰጣቸው የጋብቻ ምስክር ወረቀት ቅጂ የምዝገባ ቁጥር እና ጋብቻውን ያስፈፀመው ተቋም ስም በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። ይኸው ለቀበሌው የኩነቶች ምዝገባ የሥራ ክፍል የተላከው የጋብቻ ምስክር ወረቀት ቅጂ ከኩነቱ መዝገብ ጋር ተያይዞ በቋሚነት ይቀመጣል።

### 5.2 የዓይን ምስክሮችን በሚመለከት

ሁለቱ ተጋቢዎች የጋብቻቸውን ሥነ ሥርዓት ፈጽመው በተፈራረሙበት ወቅት በሥነ ሥርዓቱ ላይ በእማኝነት ተገኝተው የፈረሙ ሦስት የዓይን ምስክሮች ሙሉ ስም (የግል ስም፣ የአባት ስምና የአያት ስም) በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። የሲቪል ጋብቻ የፈፀሙ ተጋቢዎችም በሲቪል ጋብቻ ወቅት የዓይን ምስክሮችን እንዲያቀርቡ ይደረጋል። የምስክሮች መደበኛ መኖሪያ ቦታ ማለትም ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ከተማ፣ ቀበሌ፣ የቤት ቁጥር እንዲሁም የቤት ቁጥር በሌለበት የገጠር መንደር ልዩ ስም ይመዘገባል። በተጨማሪም የአይን ምስክሮች ጋብቻ

ለመከሰቱ የሰጡት ቃል ትክክል ስለመሆኑ በፊርማቸው በማረጋገጥና ቀን፣ ወሩንና ዓመተ ምህረቱን በመፃፍ ይገልፃሉ።

## ክፍል 6 <u>አስተያየት</u>

የጋብቻውን ኩነት ምዝገባ በተመለከተ ጠቃሚ ናቸው ተብለው የሚገመቱና በሌላ ቦታ ያልተጠቀሱ ተጨማሪ መረጃዎችና የመዝጋቢው የግል አስተያየት በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይጻፋሉ።

## ክፍል 7. <u>የሙሽራውና የሙሽሪት ስም፣ ፊርማና ቀን</u>

ሙሽራው እና ሙሽራይቱ በሕዝብ የክብር መዝገቡ የተመዘገበው መረጃ ትክክል መሆኑን ሙሉ ስማቸውን፣ ፊርማና ቀኑን በመግለጽ ይመዘግባሉ።

### 7.1 <u>የሙሽራውና የሙሽሪት ሙሉ ስም</u>

የሙሽራውና የሙሽሪት ሙሉ ስም (የግል ስም፣ የአባት ስም እና የአያት ስም) በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል።

### 7.2 <u>የሙሽራውና የሙሽሪት ፊርማና ቀን</u>

በጋብቻ መዝገቡ የተመዘገቡት መረጃዎች ለሙሽራውና ለሙሽሪት ከመዝገቡ እየተነበቡ ከተገለፁ በኋላ ሙሽሮች የሰጡት መረጃ ትክክል ስለመሆኑ በፊርማቸው በማረጋገጥና ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ በመፃፍ ይገልፃሉ።

## ክፍል 8 <u>የመዝጋቢ ስም፣ ፊርማና ቀን</u>

በዚህ ክፍል የጋብቻ ኩነቱ ተከናውኖ አስፈላጊው ማጣራት ተደርጎ መረጃዎቹ ተሟልተው የተመዘገቡ መሆናቸውን መዝጋቢው የሚያረጋግጥበት ነው።

### 8.1 <u>የመዝጋቢ ሙሉ ስም</u>

የመዝጋቢው የግል ስም፣ የአባት ስምና የአያት ስም በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባሉ።

### 8.2 <u>የመዝጋቢ ፊርማና ቀን</u>

መዝጋቢው አስፈላጊዎቹ መረጃዎች ተሟልተው ምዝገባው በትክክል ለመከናወኑ ፊርማውን በማስቀመጥ ያረጋግጣል። በተጨማሪም መዝጋቢው ምዝገባውን ያጠናቀቀበትን ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት በመጥቀስ ያሰፍራል።

## 3.4 የፍቺ ወሳኝ ኩነት መረጃ አመዘጋገብ

በፍቺ የሕዝብ የክብር መዝገብ ውስጥ የሚሠፍሩት መረጃዎች ከዚህ በታች የተመለከተውን የአመዘጋገብ መመሪያ መሠረት በማድረግ ይመዘገባሉ። መዝጋቢው ከአስመዝጋቢዎች፣ ከፍርድ ቤት፣ ከተለያዩ ተቋማትና ከጠቋሚዎች ባገኘው መረጃና በራሱ ያወቃቸውን የፍቺ ኩነቶች ይመዘግባል።

የፍቺውን ኩነት መከሰት ቀርበው የማስመዝገብ ግዴታ የተጣለባቸው ሁለቱ ተፋቺዎች ወይም የፍቺ ጥያቄ ያቀረበው ወገን ነው። ፍ/ቤት፣ የሃይማኖት ተቋማትና የአገር ሽማግሌዎችም ያስፈፀሙትን የፍቺ ኩነት መከሰት የማስታወቅና የማስመዝገብ ግዴታ አለባቸው። በመሆኑም በፍቺ መዝገቡ ውስጥ የሚመዘገቡ መረጃዎችን መዝጋቢው ከዚህ በታች ስለፍቺ አመዘጋገብ የተሰጡትን አጠቃላይ መመሪያዎችና የምዝገባውን ሕግ መሠረት በማድረግ መረጃዎቹን በትክክል መመዝገብ ይጠበቅበታል። በተጨማሪም የፍቺ ኩነት ምዝገባን በተመለከተ የሚከተሉት ጉዳዮች ትኩረት ሊያገኙ ይገባል።

1ኛ/ በመደበኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ፍቺ የተፈጸመ እንደሆነ ተፋቺዎች በመደበኛነት ይኖሩበት ለነበረ ቀበሌ የሕዝብ የክብር መዝገብ የሥራ ክፍል ፍቺውን ያስፈፀመው ፍ/ቤት ፍቺ ስለመፈፀሙ የሰጠውን መረጃ መላክ አለበት። በተመሳሳይ ተፋቺዎች በፍርድ ቤት ስለፍቺው መፈፀም የተሰጣቸውን ማስረጃ በመያዝ ከመፋታታቸው በፊት በመደበኛነት ይኖሩበት ወደነበረ ቀበሌ የሕዝብ የክብር መዝገብ የሥራ ክፍል ቀርበው ፍቺውን ማስመዝገብ አለባቸው።

2ኛ/ ፍቺው የተፈፀመው በሃይማኖታዊ ሥርዓት በሃይማኖታዊ ተቋም የሆነ እንደሆነ የተቋሙ ኃላፊ ፊርማና የተቋሙ ማህተም ያረፈበት የጽሑፍ ማስረጃ ተቋሙ ለሚገኝበት ቀበሌ የሕዝብ የክብር መዝገብ የሥራ ክፍል የመላክ ግዴታ አለበት። በተመሳሳይ ተፋቺዎቹ ከሃይማኖት ተቋሙ ስለፍቺው መፈፀም የተሰጣቸውን ማስረጃ በመያዝ ከመፋታታቸው በፊት በመደበኛነት ይኖሩበት ወደነበረ ቀበሌ የሕዝብ የክብር መዝገብ የሥራ ክፍል ቀርበው ፍቺውን ማስመዝገብ አለባቸው።

3ኛ/ ፍቺው የተፈፀመው በአገር ባህል ወይም ልማድ የሆነ እንደሆነ ፍቺውን ያስፈፀሙት ሽማግሌዎች ስምና ፊርማ ያረፈበት የጽሑፍ ማስረጃ በተፋቺዎች አማካይነት ለቀበሌ የህዝብ የክብር መዝገብ የሥራ ክፍል መቅረብ አለበት። ሽማግሌዎችም የፍቺውን መከሰት ለቀበሌ የሕዝብ የክብር መዝገብ የሥራ ክፍል የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው።

ስለሆነም መዝጋቢው ከላይ የተገለጹትንና በምዝገባ ሕጉ በዝርዝር የሚደነገጉትን የአመዘጋገብ ሥርዓቶች ተከትሎ በፍቺ የሕዝብ የክብር መዝገቡ ውስጥ ተፈላጊዎቹን መረጃዎች በጥንቃቄ መመዝገብ ይጠበቅበታል።

መዝጋቢው በፍቺ የሕዝብ የክብር መዝገቡ ውስጥ ላሰፈራቸው መረጃዎች ትክክለኛነትና እውነተኛነት በሕግ ተጠያቂነት ስላለበት በምዝገባው ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል።

## ክፍል 1 <u>የምዝገባ አካባቢ መለያ</u>

በዚህ ክፍል የፍቺ የሕዝብ የክብር መዝገብ ምዝገባ የሚመዘገብበት ቀበሌ የሕዝብ የክብር መዝገብ የሥራ ክፍል የሚገኝበት ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ከተማ፣ የቀበሌ ስም ወይም ቁጥር እና የቤት ቁጥር ወይም በገጠር የቤት ቁጥር ከሌለ የመንደሩ ልዩ ስም ይመዘገባል።

1.1 <u>የክልል ስም</u>

"የክልል ስም" በሚለው ክፍት ቦታ ላይ ምዝገባው የሚካሄድበት ቀበሌ የሚገኝበት ክልል ስም ይመዘገባል።

1.2 <u>የዞን ስም</u>

"የዞን ስም" በሚለው ክፍት ቦታ ላይ ምዝገባው የሚካሄድበት ቀበሌ የሚገኝበት ዞን ስም ይመዘገባል።

1.3 <u>የወረዳ ስም</u>

"የወረዳ ስም" በሚለው ክፍት ቦታ ላይ ምዝገባው የሚካሄድበት ቀበሌ የሚገኝበት ወረዳ ስም ይመዘገባል።

1.4 <u>የከተማ ስም</u>

ምዝገባው የሚካሄድበት ቀበሌ የሚገኘው በከተማ ሥር ከሆነ በተሰጠው ክፍት ቦታ "የከተማው ስም" ይመዘገባል።

1.5 <u>የከተማ ቀበሌ ስም ወይም ቁጥር</u>

ምዝገባው የሚካሄድበት የከተማ ቀበሌ ነዋሪዎች ማህበር ስም ወይም ቁጥር ይመዘገባል።

1.6 <u>የገጠር ቀበሌ (ገ/ማህበር) ስም ወይም ቁጥር</u>

ምዝገባው የሚካሄድበት ቀበሌ የሚገኘው በገጠር ከሆነ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ የገጠር ቀበሌው ስም ወይም ቁጥር ይመዘገባል።

1.7 <u>የምዝገባ ጽ/ቤት የቤት ቁጥር (በከተማ)</u>

የቀበሌው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የሥራ ክፍል የሚገኝበት ቤት የቤት ቁጥር ይመዘገባል። በከተማ ቤቱ የሚለየው ለቤቱ የቀበሌው መስተዳድር በሰጠው የቤት ቁጥር

አማካይነት ነው። በዚሁም መሠረት ቀበሌው ለቤቶች ሥርዓትን ተከትሎ የቤት ቁጥር እንዲሰጥ "በሚያዘው መመሪያ" መሠረት የምዝገባ የሥራ ክፍሉ ለሚገኝበት ጽ/ቤት የተሰጠው የቤት ቁጥር ይመዘገባል። ቤቱ ንዑስ ቁጥር ወይም ፊደል ካለው ከቤቱ ቁጥር ጋር አብሮ ይመዘገባል።

1.8 **የምዝገባ ጽ/ቤት የሚገኝበት የመንደር ልዩ ስም እና የቤት ቁጥር (በገጠር)**

በገጠር መኖሪያ ቤቶችም ሆኑ የድርጅት ቤቶች የመለያ የቤት ቁጥር ላይሰጣቸው ይችላል። ሆኖም የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባን በማከናወን ቤተሰቦችን ለመለየትና አድራሻቸውን ለማወቅ አልፎም የምዝገባ ጽ/ቤቶችን ለመለየት ለቤቶች ሥርዓትን የተከተለ የቤት ቁጥር መስጠት አስፈላጊ ነው። ስለሆነም ቤቶችን በሥርዓት የቤት ቁጥር የመስጠት አሰራርን በገጠር ቀበሌዎች ማስፈንን የምዝገባው አንድ አካል አድርጎ መውሰድ ያስፈልጋል። በዚሁም መሠረት ቀበሌው ለቤቶች ሥርዓትን ተከትሎ የቤት ቁጥር እንዲሰጥ "በሚያዘው መመሪያ" መሠረት የምዝገባ የሥራ ክፍሉ ለሚገኝበት ጽ/ቤት የተሰጠው የቤት ቁጥር እና የመንደሩ ልዩ ስም ይመዘገባል።

## ክፍል 2 ፍቺውን የሚመለከት

በዚህ ክፍል ፍቺውን የሚመለከቱ መረጃዎች ተፋቺዎችን በመጠየቅና ከተለያዩ ተቋማት የተሰጡ ማስረጃዎችን በመመርመር ይመዘገባሉ።

2.1 **ፍቺው የተፈጸመበት ቀን**

ተፋቺዎች በመደበኛ ፍ/ቤት የሲቪል ፍቺ ወይም በሃይማኖታቸው (በሁለቱም ወይም በአንዳቸው የሃይማኖት ሥርዓት በሃይማኖት አባቶች ፊት ቀርበው) ወይም በባህላቸው (በሁለቱም ወይም በአንዳቸው/ባህል በሽማግሌዎች ፊት ቀርበው) መሠረት ፍቺውን የፈፀሙበት ቀን፣ ወር እና ዓመት ምሕረት ይመዘገባል።

2.3 **ፍቺው የተመዘገበበት ቀን**

ፍቺው በፍቺ የሕዝብ የክብር መዝገብ የተመዘገበበት ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት በቅደም ተከተል ይመዘገባሉ።

2.3 **ፍቺው የተፈፀመበት ቦታ**

ፍቺው የተፈፀመበት ቦታ ማለትም ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ከተማ፣ ቀበሌ እንዲሁም የቤት ቁጥር ይመዘገባል። የቤት ቁጥር በሌለበት የገጠር ክፍል የመንደሩ ልዩ ስም ይመዘገባል። በፍርድ ቤት ወይም ከፍርድ ቤት ውጪ ፍቺን በሃይማኖታዊ ሥርዓት ወይም እንደ አካባቢው ባህል የፈፀሙ እንደሆነ ፍቺው የተፈፀመበት ቦታ የሚባለው የሃይማኖት ተቋሙ ወይም ባህላዊው የፍቺ ሥርዓት የተፈፀመበት መኖሪያ ቤት ወይም ቦታ ይሆናል።

## 2.4 የፍቺው ዓይነት

ተፋቺዎቹ ፍቺውን የፈጸሙበት ሥርዓት ዓይነት ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ውስጥ ይመዘገባል።

- ብሔራዊ/ሲቪል ፍቺ
- ሐይማኖታዊ ፍቺ
- ልማዳዊ/ባህላዊ ፍቺ

ከላይ የተገለፁት የፍቺ አፈፃፀም ሥርዓቶችን የሀገሪቱ የፍትሀ-ብሄር ህግ የሚሰጣቸው የዕውቅና ደረጃ ይለያያል። በመሆኑም የምዝገባ ህጉ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባን ለማስፈፀም በሚያስችልና ሁሉም ፍቺዎች የሚያዙበትን መንገድ በሚቀይስ መልኩ ህጉ ተሻሽሎ መደንደግን ይጠይቃል።

## 2.5 የፍቺው ምዝገባ መለያ ቁጥር

ፍቺው በሕዝብ የክብር መዝገብ ውስጥ በሚመዘገብበት ጊዜ ለኩነቱ የተሰጠው የምዝገባ መለያ ቁጥር ይመዘገባል። መዝጋቢው በዓመቱ መጀመሪያ ምዝገባ በሚጀመርበት ጊዜ በፍቺው የክብር መዝገብ ውስጥ መጀመሪያ ለመዘገበው የፍቺ ኩነት "0001" በሚል ተራ ቁጥር ጀምሮ ሌሎችን ኩነቶች በቅደም ተከተል "0002"፣ "0003" ፣ … ወዘተ እንዳመዘጋገባቸው ተራ ቁጥር ይሰጣቸዋል። ከዚህ ቁጥር በኋላም ፍቺው የተከሰተበትን ዓመት ሊያመለክት በሚችል መልኩ ፍቺው የተከሰተበት ዓመት ምህረት ተከትሎ ይመዘገባል። በመሆኑም ለምሳሌ በ1997 ዓ.ም በቀበሌው በፍቺ የክብር መዝገብ በመጀመሪያ ለተመዘገበው ፍቺ "0001-97"፣ ለሁለተኛው ፍቺ "0002-97"፣ ለሶስተኛው ፍቺ "0003-97"፣ … ወዘተ በማለት የፍቺ የምዝገባ መለያ ቁጥር በክፍት ቦታው ላይ ይመዘገባል።

## 2.6 የፍቺው ምክንያት

ሁለቱ ተፋችዎች ወይም ተበደልኩ ብሎ ለፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረበው ወገን ባቀረበው ምክንያት ላይ ተንተርሶ ፍ/ቤቱ ፍቺውን ያፀደቀበት ዋነኛ የፍቺ ምክንያት በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። ከፍርድ ቤት ውጪ በሃይማኖት ተቋማት ወይም በአካባቢው ባሕል መሠረት በአገር ሽማግሌዎች የተፈፀመ ፍቺ ከሆነ ደግሞ ፍቺውን ያስፈፀመው ተቋም ወይም የሽማግሌዎቹ ተጠሪ የፍቺውን ምክንያት በጽሑፍ እንዲያስታውቁ ማድረግ ያስፈልጋል። በዚህ ሁኔታ ለተከናወነ ፍቺም በተለያዩ አካላት የተሰጠው የፍቺ ምክንያት ይመዘገባል።

በምሳሌነት እንዲያገለግሉ ዋና ዋና የፍቺ ምክንያቶች ከታች ተመልክተዋል።

- ልጅ መውለድ አለመቻል
- ቤተሰብን እንደሚገባ አለመምራት
- የጤና ችግር
- የዕድሜ ልዩነት

- የሃይማኖት ልዩነት
- የዘር/ብሔረሰብ ልዩነት
- ድህነት
- ሌላ ለማግባት ፍላጎት (አለመጣጣም)
- አብሮ መኖር አለመቻል
- ሌላ (ይገለጻል)

2.7 ከ18 ዓመት በታች በህይወት የሚኖሩ ልጆች ብዛት

ሁለቱ ተፋቺዎች በዚህ ጋብቻቸው ወቅት በጋራ የወለዷቸው ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑና በህይወት የሚኖሩ የጋራ ልጆች ብዛት በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። ዕድሜአቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑና በህይወት የሚኖሩ ልጆች ከባልና ሚስቱ ጋር የሚኖሩትንም ሆነ የማይኖሩትን ተደምሮ የሚመዘገብ ነው። የባልና ሚስት መፋታት በተለይ በታዳጊ ሕጻናት ላይ የሚያደርሰው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ስነ-ልቡናዊ ተጽእኖ ከፍተኛ በመሆኑ ስለችግሩ ጥልቀት ያለው ጥናት አድርጎ መፍትሔ ለመፈለግ ስለሚረዳ በትክክል መረጃውን መሙላት አስፈላጊ ነው።

2.8 ጋብቻው የቆየበት ጊዜ

ተፋቺዎቹ በዚህ ጋብቻ አብረው የቆዩበት ጊዜ ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ የጊዜው ርዝመት በሙሉ ዓመት ይመዘገባል። በጋብቻ የቆዩት ከ1 ዓመት በታች ከሆነ በተሰጠው ክፍት ቦታ 00 ይመዘገባል። ለምሳሌ ባልና ሚስቱ አብረው የቆዩት 5 ዓመት ከ7 ወር ቢሆን በተሰጠው ክፍት ቦታ “05” ተብሎ ይመዘገባል።

## ክፍል 3. ባልን የሚመለከት

በዚህ ክፍል ተፋቺውን የሚመለከቱ መረጃዎች ባልየውን (ተፋቺውን) በመጠየቅና ከሌሎች አካላት የሚቀርቡ ማስረጃዎችን በመመርመር ይመዘገባል።

3.1 የባል ሙሉ ስም

የባልየው የግል ስም፣ የአባት ስምና የአያት ስም ይመዘገባሉ። የባልየው የግል የመለያ ስም ሊወሰድ ይገባ የነበረው ባልየው ሲወለድ ከተመዘገበ የልደት የምስክር ወረቀት ላይ ነበር። ሆኖም ከዚህ በፊት እንደተገለጸው እስከተወሰኑ ዓመታት በአግባባዊው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አሠራር የተዘጋጁ የልደት የምስክር ወረቀቶች የማይኖሩ በመሆኑ ያለው አማራጭ በወቅቱ ባልየው በቀበሌ መስተዳድር ጽ/ቤት በሚሰጠው የነዋሪነት መታወቂያ ላይ የተጠቀሰውን ስም ወስዶ መመዝገብ ነው። ይኸም ሲሆን በቀበሌ ነዋሪነት መታወቂያ ወረቀት ላይ የተገለጸው መለያ ስም ትክክል ለመሆኑ ባልየውን በመጠየቅ አልፎም አጠራጣሪ ሁኔታዎች ከታዩ መታወቂያውን የሰጠውን አካል በመጠየቅ ማጣራት ያስፈልጋል።

### 3.2 የባል ዕድሜ

ባልየው ይህንን ፍቺ በፈጸመበት/በሚፈጽምበት ጊዜ የነበረው ትክክለኛ ዕድሜ በሙሉ ዓመት (በጨረሰው ዓመት) ይመዘገባል። ከዚህ በፊት በተለያዩ ቦታዎች እንደተገለጸው የማንኛውም ሰው ትክክለኛ ዕድሜ ሊታወቅ የሚችለው ግለሰቡ በተወለደበት ጊዜ በኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት አማካይነት በተሰጠው የምስክር ወረቀት አማካይነት ነበር። ይህ ሁኔታ የተሟላ ከሆነ ዕድሜው ከተፈለገበት ቀን ላይ የተወለደበትን ቀን በማቀናነስ ትክክለኛ የዕድሜ መረጃ ማግኘት ይቻላል። በኩነቶች ምዝገባ አማካይነት የተገኘ የልደት የምስክር ወረቀት ለሌላቸው ግለሰቦች የተወለዱበትን ትክክለኛ ዕድሜ ጠይቆና እንዲያስታውሱ በማድረግ ዕድሜአቸውን ማግኘት ያስፈልጋል። በዚህ መንገድ የሚገኘው የዕድሜ መረጃ ትክክለኛነት በግለሰቡ የልደት ቀንን በጽሑፍ ማስታወሻ በመያዝ ልምድና የማስታወስ ችሎታ ላይ ይመሠረታል። ዕድሜ በሙሉ ዓመት ማለት ከሙሉ ዓመት በተጨማሪ ያሉትን ወሮችንና ቀኖችን በመተው ዓመቱን ብቻ በመውሰድ ዕድሜውን መመዝገብ ነው። ለምሳሌ የባልየው ዕድሜ በፍቺው ዕለት 52 ዓመት ከ6 ወራት ከ29 ቀናት ከሆነ መመዝገብ ያለበት 52 ዓመት ብቻ ነው።

ዕድሜውን በትክክል ለማያውቅ ባል በተወለደበት ጊዜ በብሔራዊ ደረጃ ወይም በሚኖርበት አካባቢ የተፈጸመ ታሪካዊ ድርጊት እንዳለና ባልየው ድርጊቱ በተፈጸመበት ጊዜ ዕድሜው ስንት እንደነበረ ወይም ከድርጊቱ በኋላ/በፊት ምን ያህል ጊዜ ቆይቶ እንደተወለደ ባልየውን በመጠየቅና ዕድሜውን በማስላት መመዝገብ ያስፈልጋል።

ከዚህም ሌላ ባልየው የአንዳንድ የቤተሰቡን አባላት ወይም የአካባቢ ነዋሪዎች ዕድሜ በትክክል ሊያውቅ ከቻለ ከነዚህ ግለሰቦች ዕድሜ ጋር በማነጻጸር የባልየውን ዕድሜ መገመት ይቻላል።

### 3.3 የባል ብሔረሰብ

የባልየው ብሔረሰብ ተጠይቆ በተዘጋጀው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። ባልየው የብሔረሰብን ትርጉም በትክክል እንዲረዳ ትውልድህ፣ ነገድህ፣ ዘርህ፣ ጎሳህ፣ …ወዘተ በማለት ማብራራት ሊያስፈልግ ይችላል። የዋና ዋና እና የቅርንጫፍ ብሔረሰቦች ስም ዝርዝር በዕዝል 1 ተያይዞ ቀርቧል።

### 3.4 የባል ሃይማኖት

ባልየው የሚከተለው እምነት ወይም የመንፈሳዊ ድርጅት አባልነት ተጠይቆ ይመዘገባል። በኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ የሃይማኖት ዓይነቶች ይታወቃሉ። አመዳደባቸውም ከታች ተመልክቷል።

- ኦርቶዶክስ (ተዋህዶ፣ ቅባት፣ ፀጋ)
- ፕሮቴስታንት (ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት፣ ሙሉ ወንጌል፣ ሉትራን፣ መካነ ኢየሱስ፣ ባፕቲስት፣ ሜኖናይት፣ አንግሊካን፣ ፕሪስቢተሪያን፣ …ወዘተ)
- ካቶሊክ
- ሙስሊም (እስላም)
- ባህላዊ አምልኮ
- ሌላ (ሂንዱ፣ ይሁዲ፣ በሃይ፣ ጀሆባ፣ ቡድሂስት፣ ኢቴስት፣…ወዘተ)

ባልየው ከላይ ከተጠቀሱት እምነቶች የየትኛው ዕምነት ተከታይ እንደሆነ ተጠይቆና ተጣርቶ ትክክለኛውን የሃይማኖት ስም መመዝገብ ያስፈልጋል። በአመዘጋገብ ወቅት በተለይ ዕምነታቸው ፕሮቴስታንት ለሆኑ በርከት ያሉ የዕምነቱ የአጠራር ዓይነቶች ስለሚኖሩ የቅርንጫፍ ስሙን በመግለጽ መመዝገብ ያስፈልጋል። ለምሳሌ ሙሉ ወንጌል ከሆነ መመዝገብ ያለበት ፕሮቴስታንት ሳይሆን "ሙሉ ወንጌል" ይሆናል።

### 3.5 <u>የባል መደበኛ መኖሪያ ቦታ</u>

ባልየው በፍቺ የሕዝብ የክብር መዝገብ ፍቺው በሚመዘገብበት ወቅት የሚኖርበት መደበኛ መኖሪያ ቦታ ማለትም ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ከተማ፣ ቀበሌ እና የቤት ቁጥር እንዲሁም በገጠር የቤት ቁጥር በሌለበት የመንደሩ ልዩ ስም ይመዘገባል።

### 3.6 <u>የባል ዜግነት</u>

የአንድ ግለሰብ የኢትዮጵያ የዜግነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የዜግነት ህግን መሠረት በማድረግ በመለየት ይመዘገባል።

### 3.7 <u>የባል ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ</u>

ባልየው በማናቸውም ቋንቋ ማንበብና መፃፍ ይችል እንደሆን፣ ከቻለም ያጠናቀቀው ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። በቅድሚያ ባልየው ማንበብና መጻፍ መቻል አለመቻሉ ተጠይቆ ማንበብና መጻፍ አልችልም ካለ "ማንበብና መፃፍ የማይችል" ተብሎ ይመዘገባል። አንድ ግለሰብ የማንበብና የመፃፍ ችሎታ አለው የሚባለው ቢያንስ በአንድ ቋንቋ አንብቦ መረዳትና እንዲሁም መፃፍ ሲችል ነው። የራሳቸውን ስም ወይንም ቁጥሮችን ብቻ ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ግለሰቦች የትምህርት ችሎታ እንዳላቸው አይቆጠሩም። እንዲሁም ሃይማኖት ነክ የሆኑና ቀደም ብለው በቃል የተጠኑ ዐረፍተ ነገሮችን ብቻ መድገም የሚችሉ የማንበብና የማፃፍ ችሎታ እንዳላቸው አይቆጠሩም። ሆኖም ግን መደበኛ በሆነ ት/ቤት ሳይገቡ በመሰረተ ትምህርት ፕሮግራም፣ በቄስ፣ በቁርዓንና በመሳሰሉት በመከታተል እንዲሁም በራሳቸው ጥረት የግለሰቦችን እርዳታ እየጠየቁ ማንበብና መፃፍ የቻሉ ሰዎች ማንበብና መፃፍ እንደሚችሉ በመወሰድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ "መደበኛ ያልሆነ ትምህርት የተከታተለ" ተብሎ ይመዘገባል። ባልየው ማንበብና መጻፍ የሚችል ከሆነ የጨረሰው ከፍተኛ የክፍል ደረጃ

ይመዘገባል። የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል አመዘጋገብ እንደባልዬው የትምህርት ደረጃ ወይም በወቅቱ በትምህርት ላይ መሆን ያለመሆኑ ሊለያይ ይችላል። ይህም ሲባል ባልየው ባለው የትምህርት ስርዓት በመደበኛ ትምህርት እየተማረ ወይም የጨረሰ ወይንም ያቋረጠ ሊሆን ይችላል። ስለሆነም ባልዬው ያጠናቀቀው ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ አመዘጋገብ ባልዬው በወቅቱ ትምህርት እየተከታተለ በመሆኑ ወይም ባለመሆኑ ሊለያይ ይችላል። ለምሳሌ 5ኛ ክፍል እየተማረ ከሆነ ያጠናቀቀው ከፍተኛ ክፍል "4ኛ ያጠናቀቀ" ተብሎ መመዝገብ አለበት። ለአመዘጋገብ ያመች ዘንድ የከፍተኛ ትምህርት ደረጃ ዝርዝር ከታች ተመልክቷል።

| | |
|---|---|
| - ማንበብና መፃፍ አይችልም | - 10+2 |
| - መደበኛ ያልሆነ ትምህርት የተከታተለ | - 10+3 |
| - አንደኛ ክፍል ያጠናቀቀ | - 12ኛ ክፍል ያጠናቀቀ |
| - ሁለተኛ ክፍል ያጠናቀቀ | - ሰርተፊኬት ያለው |
| - ሶስተኛ ክፍል ያጠናቀቀ | - ዲፕሎም ያልጨረሰ |
| - አራተኛ ክፍል ያጠናቀቀ | - ዲግሪ ያልጨረሰ |
| - አምስተኛ ክፍል ያጠናቀቀ | - ዲፕሎም ያለው |
| - ስድስተኛ ክፍል ያጠናቀቀ | - ዲግሪ ያለው |
| - ሰባተኛ ክፍል ያጠናቀቀ | - የማስተርስ ዲግሪ ያላጠናቀቀ |
| - ስምንተኛ ክፍል ያጠናቀቀ | - የዶክትሬት ዲግሪ ያላጠናቀቀ |
| - ዘጠናኛ ክፍል ያጠናቀቀ | - የማስተርስ ዲግሪ ያለው |
| - አስረኛ ክፍል ያጠናቀቀ | - የዶክትሬት ዲግሪ ያለው |
| - አስራ አንደኛ ክፍል ያጠናቀቀ | - ፕሮፌሰር |

### 3.8 የፍቺ ብዛት

ባልየው ከዚህኛው ጭምር ስንት ጊዜ ፍቺ እንደፈጸመ ተጠይቆ ብዛቱ ይመዘገባል።

## ክፍል 4 ሚስትን የሚመለከት

በዚህ ክፍል ተፋቺዋን የሚመለከቱ መረጃዎች ሚስትዬዋን (ተፋቺዋን) በመጠየቅና ከሌሎች አካላት የሚቀርቡ ማስረጃዎችን በመመርመር ይመዘገባል።

### 4.1 የሚስት ሙሉ ስም

የሚስትየዋ የግል ስም፣ የአባት ስም እና የአያት ስም በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባሉ። የሚስትየዋ የግል የመለያ ስም ሊወሰድ ይገባ የነበረው ሚስትየዋ ስትወለድ ከተመዘገበ የልደት የምስክር ወረቀት ላይ ነበር። ሆኖም ከዚህ በፊት ተደጋግሞ እንደተገለጸው እስከተወሰኑ ዓመታት በአግባባዊው አሠራር የተዘጋጁ የልደት ኩነት የምስክር ወረቀቶች የማይኖሩ በመሆኑ ያለው አማራጭ በወቅቱ ሚስትዮዋ በቀበሌ መስተዳድር ጽ/ቤት በሚሰጠው የነዋሪነት መታወቂያ ላይ

የተጠቀሰውን ስም ወስዶ መመዝገብ ነው። ይኸም ሲሆን በቀበሌ ነዋሪነት መታወቂያ ላይ የተገለጸው መለያ ስም ትክክል ለመሆኑ ሚስትዬዋን መጠየቅ አልፎም አጠራጣሪ ሁኔታዎች ከታዩ መታወቂያውን የሰጠውን አካል በመጠየቅ ማጣራትና ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

4.2 <u>የሚስት ዕድሜ</u>

ሚስት ፍቺውን በፈጸመችበት ጊዜ የነበራት ትክክለኛ ዕድሜ በሙሉ ዓመት (በጨረሰችው ዓመት) ይመዘገባል። ከዚህ በፊት በተለያዩ ቦታዎች እንደተገለጸው የማንኛውም ሰው ትክክለኛ ዕድሜ ሊታወቅ የሚችለው ግለሰቡ በተወለደበት ጊዜ በኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት አማካይነት በተሰጠው የምስክር ወረቀት አማካይነት ነበር። ይህ ሁኔታ የተሟላ ከሆነ ዕድሜው ከተፈለገበት ቀን ላይ የትውልድ ቀንን በማቀናነስ ትክክለኛ የዕድሜ መረጃ ማግኘት ይቻላል። በኩነቶች ምዝገባ አማካይነት የተገኘ የልደት የምስክር ወረቀት ለሌላቸው ግለሰቦች የተወለዱበትን ትክክለኛ ዕድሜ ጠይቆና እንዲያስታውሱ በማድረግ ዕድሜአቸውን ማግኘት ያስፈልጋል። በዚህ መንገድ የሚገኘው የዕድሜ መረጃ ትክክለኛነት በግለሰቡ በጽሑፍ ማስታወሻ የልደት ቀንን በመያዝ ልምድና የማስታወስ ችሎታ ላይ ይመሠረታል። ዕድሜ በሙሉ ዓመት ማለት ከሙሉ ዓመት በተጨማሪ ያሉትን ወሮችንና ቀኖችን በመተው ዓመቱን ብቻ በመውሰድ ዕድሜውን መመዝገብ ነው። ለምሳሌ የሚስትዬዋ ዕድሜ ፍቺውን በፈፀመችበት ዕለት 44 ዓመት ከ11 ወራትና ከ15 ቀናት ከሆነ መመዝገብ ያለበት 44 ዓመት ብቻ ነው።

ዕድሜዋን በትክክል ለማታውቅ ሴት በተወለደችበት ጊዜ በብሔራዊ ደረጃ ወይም በምትኖርበት አካባቢ የተፈጸመ ታሪካዊ ድርጊት እንዳለና ሚስትዬዋ ድርጊቱ በተፈጸመበት ጊዜ ዕድሜዋ ስንት እንደነበረ ወይም ከድርጊቱ በኋላ/በፊት ምን ያህል ጊዜ ቆይታ እንደተወለደች በመጠየቅና ዕድሜዋን በማስላት መመዝገብ ያስፈልጋል።

ከዚህም ሌላ ሚስትየዋ የአንዳንድ የቤተሰቧን አባላት ወይም የአባባቢ ነዋሪዎች ዕድሜ በትክክል ልታውቅ ከቻለች ከነዚህ ግለሰቦች ዕድሜ ጋር በማነጻጸር የሚስትዬዋን ዕድሜ መገመት ይቻላል።

4.3 <u>የሚስት ብሔረሰብ</u>

የሚስትየው ብሔረሰብ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። ሚስትየው የብሔረሰብን ትርጉም በትክክል እንድትረዳ ትውልድ፣ ነገድ፣ ዘር፣ ጎሳ፣...ወዘተ በማለት ማብራራት ሊያስፈልግ ይችላል። የዋና ዋና እና የቅርንጫፍ ብሔረሰቦች ስም ዝርዝር በዕዝል 1 ተያይዞ ቀርቧል።

4.4 <u>የሚስት ሃይማኖት</u>

ሚስትየው የምትከተለው እምነት ወይም የመንፈሳዊ ድርጅት አባልነት ይመዘገባል። በኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ የሃይማኖት ዓይነቶች ይታወቃሉ። አመዳደባቸውም ከታች ተመልክቷል።

- ኦርቶዶክስ (ተዋህዶ፣ ቅባት፣ ፀጋ)
- ፕሮቴስታንት (ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት፣ ሙሉ ወንጌል፣ ሉትራን፣ መካነ ኢየሱስ፣ ባፕቲስት፣ ሜኖናይት፣ አንግሊካን፣ ፕሪስፒተሪያን፣ ...ወዘተ)
- ካቶሊክ
- ሙስሊም (እስላም)
- ባህላዊ አምልኮ
- ሌላ (ሂንዱ፣ ይሁዲ፣ በሃይ፣ ጀሆባ፣ ቡድሂስት፣ ኢቴስት፣...ወዘተ)

ሚስትየዋ ከላይ ከተጠቀሱት እምነቶች የየትኛው ዕምነት ተከታይ እንደሆነች ተጣርቶ ትክክለኛውን ሃይማኖት መመዝገብ ያስፈልጋል። በአመዘጋገብ ወቅት በተለይ ዕምነታቸው ፕሮቴስታንት ለሆኑ በርከት ያሉ የዕምነቱ የአጠራር ዓይነቶች ስለሚኖሩ የቅርንጫፍ ስሙን በመግለጽ መፃፍ ያስፈልጋል። ለምሳሌ ሙሉ ወንጌል ከሆነ በዓምዱ መሞላት ያለበት ፕሮቴስታንት ሳይሆን "ሙሉ ወንጌል" ይሆናል።

## 4.5 <u>የሚስት መደበኛ መኖሪያ ቦታ</u>

የሚስትየዋ መደበኛ መኖሪያ ማለትም ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ከተማ፣ ቀበሌ እና የቤት ቁጥር እንዲሁም በገጠር የቤት ቁጥር በሌለበት የምትኖርበት መንደር ልዩ ስም ይመዘገባል።

## 4.6 <u>የሚስት ዜግነት</u>

የሚስትየዋ ዜግነት ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። የአንዲት ግለሰብ ኢትዮጵያዊ ዜግነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የዜግነት ህግን መሠረት በማድረግና በመለየት ይመዘገባል።

## 4.7 <u>የሚስት ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ</u>

ሚስትየዋ በማንኛውም ቋንቋ ማንበብና መፃፍ ትችል እንደሆን፣ ከቻለችም ያጠናቀቀችው ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። በቅድሚያ አስመዝጋቢው ሚስትዬው ማንበብና መጻፍ መቻል አለመቻሏን ጠይቆ ማንበብና መጻፍ አትችልም ካተባለ "ማንበብና መፃፍ የማትችል" ተብሎ ይመዘገባል። አንድ ግለሰብ የማንበብና የመፃፍ ችሎታ አለው የሚባለው ቢያንስ በአንድ ቋንቋ አንብቦ መረዳትና እንዲሁም መፃፍ ሲችል ነው። የራሳቸውን ስም ወይንም ቁጥሮችን ብቻ ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ግለሰቦች የትምህርት ችሎታ እንዳላቸው አይቆጠሩም። እንዲሁም ሃይማኖት ነክ የሆኑና ቀደም ብለው በቃል የተጠኑ ዐረፍተ ነገሮችን ብቻ መድገም የሚችሉ የማንበብና የመፃፍ ችሎታ እንዳላቸው አይቆጠሩም። ሆኖም ግን መደበኛ በሆነ ት/ቤት ሳይገቡ በመሰረተ ትምህርት ፕሮግራም፣ በቄስ፣ በቁርዓንና በመሳሰሉት በመግባት እንዲሁም በራሳቸው ጥረት የግለሰቦችን እርዳታ እየጠየቁ ማንበብና መፃፍ የቻሉ ሰዎች ማንበብና መፃፍ እንደሚችሉ በመወሰድ በተሰጠው ክፍት ቦታ

ላይ "መደበኛ ያልሆነ ትምህርት የተከታተለች" ተብሎ ይመዘገባል። ሚስትየዋ ማንበብና መጻፍ የምትችል ከሆነ የጨረሰችው ከፍተኛ የክፍል ደረጃ ይመዘገባል። የጨረሰችው ከፍተኛ ክፍል አመዘጋገብ እንደ ሚስትዬዋ የትምህርት ደረጃ ወይም በወቅቱ በትምህርት ላይ መሆን ያለመሆን ሊለያይ ይችላል። ይህም ሲባል ግለሰቦች ባለው የትምህርት ስርዓት በመደበኛ ትምህርት እየተማሩ ያሉ ሊሆኑ ይችላሉ፣ የጨረሱ ወይንም ያቋረጡ ሊሆኑም ይችላሉ። ስለሆነም ሚስትዬዋ ከዚህ በፊት ተምራ ያጠናቀቀችው ከፍተኛ የትምህርት ክፍል አመዘጋገብ እንደ ክፍል ደረጃዋና በወቅቱ ትምህርት የተከታተለች መሆን ወይም ያለመሆኗ ይለያያል። ለምሳሌ 11ኛ ክፍል እየተማረች ላለች ሴት ያጠናቀቀችው ከፍተኛ ክፍል "10ኛን ያጠናቀቀች" ተብሎ መመዝገብ አለበት። በተመሳሳይ ሚስትዬዋ የዲፕሎማ ትምህርት ተከታትላ ዲፕሎም ያላት ከሆነ የሚመዘገበው "ዲፕሎም ያላት" በማለት ነው። ለአመዘጋገብ ያመች ዘንድ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ዝርዝር ከታች ተመልክቷል።

| | |
|---|---|
| - ማንበብና መፃፍ አትችልም | - 10+2 |
| - መደበኛ ያልሆነ ትምህርት የተከታተለች | - 10+3 |
| - አንደኛ ክፍል ያጠናቀቀች | - 12ኛ ክፍል ያጠናቀቀች |
| - ሁለተኛ ክፍል ያጠናቀቀች | - ሰርተፊኬት ያላት |
| - ሶስተኛ ክፍል ያጠናቀቀች | - ዲፕሎም ያልጨረሰች |
| - አራተኛ ክፍል ያጠናቀቀች | - ዲግሪ ያልጨረሰች |
| - አምስተኛ ክፍል ያጠናቀቀች | - ዲፕሎም ያላት |
| - ስድስተኛ ክፍል ያጠናቀቀች | - ዲግሪ ያላት |
| - ሰባተኛ ክፍል ያጠናቀቀች | - የማስተርስ ዲግሪ ያላጠናቀቀች |
| - ስምንተኛ ክፍል ያጠናቀቀች | - የዶክትሬት ዲግሪ ያላጠናቀቀች |
| - ዘጠነኛ ክፍል ያጠናቀቀች | - የማስተርስ ዲግሪ ያላት |
| - አስረኛ ክፍል ያጠናቀቀች | - የዶክትሬት ዲግሪ ያላት |
| - አስራ አንደኛ ክፍል ያጠናቀቀች | - ፕሮፌሰር |

4.8 <u>የፍቺ ብዛት</u>

ሚስትየው ከዚህኛው ጭምር ስንት ጊዜ ፍቺ እንደፈጸመች ተጠይቆ ብዛቱ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል።

## ክፍል 5 <u>ለፍቺው ማረጋገጫ የቀረበ ማስረጃ</u>

በዚህ ክፍል ፍቺው በእርግጥ ለመፈጸሙ የሚያረጋግጡት ማስረጃዎች ዓይነት የሚገለጽበት ነው።

### 5.1 የፍ/ቤት የፍቺ ትዕዛዝ ወይም ምስክር ወረቀት ወይም ውል

በፍቺው ኩነት ምዝገባ ወቅት ፍቺው በርግጥ ለመፈጸሙ ካጸደቀው አካል (ፍ/ቤት፣ የሃይማኖት ተቋም፣ ሽማግሌዎች፣ ...ወዘተ) ከቀረበው ማስረጃ ማለትም ምስክር ወረቀት ወይም የጽሁፍ መረጃ ይረጋገጣል። የዚሁ መረጃ የምዝገባ/ደብዳቤ ቁጥር እና ያስፈፀመው ተቋም ወይም አካል ስም በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል። ይኸው ፍቺውን ባስፈፀመው ተቋም ወይም ሽማግሌዎች የተዘጋጀው መረጃ ቅጂ ከኩነቱ መዝገብ ጋር ተያይዞ በቀበሌው ምዝገባ የሥራ ክፍል በቋሚነት መቀመጥ አለበት።

### 5.2 የዓይን ምስክሮችን የሚመለከት

ፍቺው መፈጸሙ የተረጋገጠው በሦስት የዓይን ምስክሮች የሆነ እንደሆነ በፍቺው ኩነት ምዝገባ ወቅት በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ የሦስቱም የዓይን ምስክሮች የግል፣ የአባትና የአያት ስም ይመዘገባል። በፍርድ ቤት ፍቺ ለመፈፀሙ የዓይን ምስክር ማቅረብ አስፈላጊ አይሆንም። የምስክሮች መደበኛ መኖሪያ ማለትም ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ከተማ፣ ቀበሌ፣ የቤት ቁጥር እንዲሁም የቤት ቁጥር በሌለበት የገጠር ቀበሌ የመንደሩ ልዩ ስም በተዘጋጀው ቦታ ይመዘገባል። በተጨማሪም የአይን ምስክሮች ፍቺው ስለመፈፀሙ የሰጡት ቃል ትክክል ስለመሆኑ በፊርማቸው በማረጋገጥ ዕለቱን (ቀኑን) በመፃፍ ይገልፃሉ።

## ክፍል 6 አስተያየት

በዚህ ክፍል ፍቺውን በሚመለከት በሌሎች ክፍሎች ያልተመዘገቡና ጠቃሚነት አላቸው ተብለው የሚገመቱ መረጃዎችና የመዝጋቢው የግል አስተያየት ይመዘገባሉ።

## ክፍል 7 የባልና የሚስት ስም፣ ፊርማና ቀን

በዚህ ክፍል የባልና የሚስት የግል ስም፣ የአባት ስም፣ የአያት ስም፣ ፊርማቸውና የፈረሙበት ቀን ይመዘገባሉ።

### 7.1 የባል ሙሉ ስም፣ ፊርማና ቀን

የባል ሙሉ ስም፣ ፊርማና ቀን በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል።

### 7.2 የሚስት ሙሉ ስም፣ ፊርማና ቀን

የሚስት ሙሉ ስም፣ ፊርማና ቀን በተዘጋጀው ክፍት ቦታ ላይ ይሠፍራል።

*ማስታወሻ፡*

*በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ በተለይም በገጠሩ ክፍል ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ብዙ ሰዎች ማንበብና መፃፍ አይችሉም። ስለሆነም ማንበብና መፃፍ የማይችሉ ባልና ሚስት እንዲሁም የዓይን ምስክሮች ለመዝጋቢ የሰጡዋቸው*

መረጃዎች ከተነበቡላቸው በኋላ በኩነቱ ጽሑፍ ስር ለመፈረም ይችገሩ ይሆናል። የዚህ ዓይነት ሁኔታ በሚያጋጥም ጊዜ የግለሰቦቹን አውራ ወይም አመልካች ጣት ቀለም በመቀባት በጣት አስፈርሞ ከግርጌው የግለሰቡን ሙሉ ስም፣ የፈረመበትን ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት መፃፍ ያስፈልጋል።

## ክፍል 8. <u>የመዝጋቢ ስም፣ ፊርማና ቀን</u>

በዚህ ክፍል መዝጋቢው በፍቺ መዝገቡ የመዘገበው መረጃ ትክክል መሆኑን ሙሉ ስሙን (የግል፣ የአባትና የአያት ስም)፣ ፊርማና ቀኑን በመግለጽ ይመዘግባል።

### 8.1 <u>የመዝጋቢው ሙሉ ስም</u>

መዝጋቢው የግል ስሙን፣ የአባትና የአያት ስም በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘግባል።

### 8.2 <u>የመዝጋቢ ፊርማና ቀን</u>

መዝጋቢው አስፈላጊዎቹ መረጃዎች ተሟልተው ምዝገባው በትክክል ለመከናወኑ ፊርማውን በማስቀመጥ ያረጋግጣል። በተጨማሪም መዝጋቢው ምዝገባውን ያጠናቀቀበትን ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት በመጥቀስ ያሰፍራል።

# ምዕራፍ አራት

## ስለ ወሳኝ ኩነቶች የምስክር ወረቀቶች አዘገጃጀት

ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓት ዐበይት ተግባራት አንዱ ወሳኝ ኩነቶች (ልደት፣ ሞት፣ ጋብቻና ፍቺ) ለመመዝገባቸው ማረጋገጫና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ግለሰቦች ህጋዊ መረጃ የሚሆኑ የምስክር ወረቀቶችን ማዘጋጀትና መስጠት ነው። ኩነቱን ለመመዝገብ በተሰጠው የጊዜ ገደብና የአመዘጋገብ መመሪያ መሠረት ለተመዘገበ ወሳኝ ኩነት የተሰጠ የምስክር ወረቀት በሕግ ፊትና በማናቸውም የአስተዳደር ቦታዎች የግለሰቡን ማንነትና ህጋዊ አቋም ማረጋገጫ ብቸኛው የህጋዊ መረጃ ምንጭ ነው። እነዚህ የኩነት የምስክር ወረቀቶች በምዝገባ ህጉ በሚደነገገው መሠረት በህግ መብት ለተሰጠው ግለሰብ እንዲሰጡ ይደረጋል። እነዚህንም የምስክር ወረቀቶች ግለሰቦቹ ከልደት እስከ ዕለተ ሞት ድረስ ለሕግ፣ ለአስተዳደርና ለተለያዩ ጉዳዮች ያለተጨማሪ የሰው ወይም የአስተዳደር መረጃ በህግና በአስተዳደር እንዲሁም በኢኮኖሚና ማህበራዊ አገልግሎቶች መስጫ ቦታዎች በማስረጃነት ይገለገሉባቸዋል።

የወሳኝ ኩነት ምስክር ወረቀቶች በሕዝብ የክብር መዝገቦች ላይ ከተመዘገቡ የወሳኝ ኩነት መረጃዎች እንዳሉ ወይም በከፊል ተወራርሰው የሚዘጋጁ ህጋዊ ሰነዶች ናቸው። እነዚህ ሰነዶች በምዝገባ ህጉ በሚደነግገው መሠረት የወሳኝ ኩነት መዝገቡ ተዘጋጅቶ እንደተጠናቀቀ የሚዘጋጁ ወይም በባለጉዳዩ ወይም በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል እንዲዘጋጁ ጥያቄ ሲቀርብ በመዝጋቢው የሚዘጋጁ ናቸው። በኢትዮጵያ የሚሰጡት የወሳኝ ኩነት የምስክር ወረቀቶች የሚይዙት መረጃ በመዝገብ ከተመዘገቡት የወሳኝ ኩነቶች መረጃዎች ከፊሉን ብቻ የሚያካትቱ ይሆናሉ።

## 4.1 <u>የወሳኝ ኩነቶች የምስክር ወረቀት ዓይነቶችና የሚሰጡት ጥቅም</u>

የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና የፍቺ ኩነት ክስተት ወይም ክንውን ከተመዘገበ በኋላ ይህንኑ የሚያስረዳ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና የፍቺ የምስክር ወረቀቶች ለባለጉዳዩ ወይም ለወኪሉ ይሰጣል። እነዚህም የምስክር ወረቀቶች የሚከተሉትን ዋና ዋና ጥቅሞች በግለሰብ ደረጃ ያስገኛሉ።

### 4.1.1 <u>የልደት ምስክር ወረቀት</u>

አንድ ህፃን በተወለደ ጥቂት ቀናት ውስጥ ከማን፣ የት፣ መቼ፣ ... ወዘተ እንደተወለደ በአስመዝጋቢው በኩል ለመዝጋቢው ተገልጾ የምዝገባ ህጉ በሚፈቅደው የጊዜ ገደብ በልደት የሕዝብ የክብር መዝገብ ተመዝግቦ የልደት ምስክር ወረቀት ሊዘጋጅለት ይገባል። የልደት ምስክር ወረቀት በዋነኛነት ከልደት ጀምሮ እስከ ዕለተ ሞት የግለሰብን ህጋዊ ማንነት ለማረጋገጥ መሠረት የሆኑትን መረጃዎች ለማግኘት ያስችላል። በተለይም ግለሰቡ በህይወት ዘመኑ በአገሪቱ

ሕገ-መንግሥት፣ በዓለም አቀፍ ድንጋጌዎችና ደንቦች የተረጋገጡለትን የሰብዓዊ፣ የፖለቲካና የማህበራዊ መብቶችን ለማስከበርና ለማስጠበቅ ወሳኝ የሆኑ መረጃዎችን በማስገኘት ትልቁን ድርሻ ይይዛል። በተጨማሪም የአንድን ግለሰብ የዕድሜ ዕድገት ተከትሎ ማለትም ት/ቤት ለመግባት፣ የነዋሪነት/ማንነት መታወቂያና ፓስፖርት ለማግኘት፣ ጋብቻ ለመፈፀም፣ የህክምና አገልግሎት ለማግኘት፣ በህዝባዊ ምርጫ በመራጭነት ወይም ተመራጭነት ለመመዝገብ፣ በውትድርና አገልግሎት ለመቀጠር ወይም ከውትድርና አገልግሎት ለመገለል፣ ለውርስ ጥያቄ፣ ለኢንሹራንስ፣ ለጡረታ፣ ...ወዘተ አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችሉ ህጋዊ ማስረጃዎች የሚገኙት ከልደት ምስክር ወረቀት ነው። ከዚህም በላይ እንደየአገሩ የኢኮኖሚና ማህበራዊ የዕድገት ደረጃና የአስተዳደር ሥርዓት ቢለያይም በተለያዩ ምክንያቶች ቤተሰቦች ከመንግስት ድጎማ ለማግኘት፣ የታክስ ቅናሽ፣ የራሽን ዕደላ፣ ... ወዘተ የመሳሰሉ አገልግሎቶችን ለማግኘትና የመብት ጥያቄውን ለማቅረብ የልደት የምስክር ወረቀት ወሳኝ የመረጃ ምንጭ ነው። በሌላም በኩል የልደት ምስክር ወረቀት ከላይ የተጠቀሱትን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ግልጋሎቶችን በትክክል ለሚመለከታቸው ለማቅረብ፣ መንግስት ከዕቅድ ዝግጅት ጀምሮ ግልጋሎቱን በግለሰብና በማህበራዊ ተቋማት አማካይነት ለመስጠት በሚያደርገው የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ የአፈፃፀም/አተገባበር ምሪት የሚሰጡ መረጃዎች ምንጭ ነው። ስለሆነም የልደት ምስክር ወረቀት በግለሰቦች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ እስከ ዕለተ ሞት የሚያገለግል ወሳኝ ህጋዊ ማስረጃ ነው።

### 4.1.2 <u>የሞት ምስክር ወረቀት</u>

የአንድ ግለሰብ ሞት በወቅቱ ታውቆ ወይም በሕጋዊ መንገድ ተረጋግጦ ከተመዘገበ በኋላ የሚገኘው ሕጋዊ የሞት የምስክር ወረቀት ለሟች ቀሪ ዘመዶች/ቤተሰቦች ከፍተኛ አገልግሎትና ጥቅም ይሰጣል። እነዚህም የቀብር ፈቃድና አስከሬን ከቦታ ወደ ቦታ ለማጓጓዝ ፈቃድ ከማግኘት ጀምሮ ለቀሪ ዘመዶች የኢንሹራንስ ክፍያ፣ ውርስ፣ ጡረታ፣ ...ወዘተ መብቶቻቸውን ለማስከበር በሞት የምስክር ወረቀት ላይ የሰፈሩ ግለሰባዊ መረጃዎች ትልቅ ጠቀሜታ አላቸው። በተጨማሪም በነዚህ መረጃዎች ላይ በመመሥረት የመንግሥትና መሰል የማህበራዊ ግልጋሎት ሰጪ ተቋማት የጡረታ ክፍያ፣ የቤተሰብ ገቢ ድጎማ፣ የራሽን ዕደላ፣ ...ወዘተ አገልግሎቶችን እንዲያቆሙ/እንዲጀምሩ ለማድረግ ያስችላቸዋል።

### 4.1.3 <u>የጋብቻ ምስክር ወረቀት</u>

ጋብቻ በሕጋዊ መንገድ ተከናውኖ ከተመዘገበ በኋላ ለተጋቢዎቹ የሚሰጠው የጋብቻ ምስክር ወረቀት ለተጋቢዎቹ፣ ለልጆቻቸውና ሌሎች ዘመዶቻቸው በህይወት እያሉና ከሞት በኋላ በርካታ ግለሰባዊ መብቶችን ለማስጠበቅ፣ የማህበራዊና አስተዳደራዊ ግልጋሎቶችን ለማግኘት ያስችላል። በተለይም ከሁለቱ ተጋቢዎች የሚወለዱት ልጆች በሕጋዊ ጋብቻ ከተሳሰሩ ጥንዶች የመወለዳቸው ማረጋገጫ፣ የልጆች ጥበቃ መብት፣ ንብረትን በጋራ የመጠቀም መብት፣

የኢንሹራንስ፣ የቤተሰብ ተቆራጭ፣ ጡረታ፣ ውርስ፣ የዜግነት ጥያቄ፣ ... ወዘተ የማስከበር መብቶችን ለማስጠበቅ የጋብቻ ምስክር ወረቀት በህግና በአስተዳደር ቦታዎች ወሳኝ ነው። በተጨማሪም በጋብቻ ላይ ለሚነሱ ክርክሮች መፍቻነት ወሳኙ ቋሚ መረጃ የጋብቻ ምስክር ወረቀት ነው።

### 4.1.4 የፍቺ ምስክር ወረቀት

ፍቺ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ወይም በሃይማኖት ተቋም ወይም በባህላዊ መንገድ ከተፈጸመ በኋላ በምዝገባ ጽ/ቤት ተመዝግቦ የሚሰጠው የፍቺ ምስክር ወረቀት ለሁለቱም ወገኖች የተለያዩ ጥቅሞች ያስገኛል። እነዚህም በጋራ ያፈሩትን ንብረት ክፍያ፣ የልጆች ጥበቃ መብት፣ ሌላ የማግባት መብት፣... ወዘተ መብቶችን ለማስጠበቅ ወሳኝ መረጃ ነው።

## 4.2 በኩነቶች ምስክር ወረቀቶች የሚካተቱ መረጃዎች ዓይነት

የኩነቶች መረጃ በሕዝብ የክብር መዝገብ ከተመዘገበ በኋላ ለባለጉዳዩ ወይም ለወኪሉ የምስክር ወረቀት ይሰጣል። እያንዳንዱ የምስክር ወረቀት የሚከተሉትን መረጃዎች ይይዛል። የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና ፍቺ ምስክር ወረቀቶች ናሙና በዕዝል 3 ተያይዞ ቀርቧል።

### 4.2.1 የልደት ምስክር ወረቀት

- የምዝገባ መለያ ቁጥር
- የመዝገብ ቅጽ ቁጥር
- የሕጻኑ/ኗ ሙሉ ስም
- የሕጻኑ/ኗ ጾታ
- የተወለደበት/ችበት ቀን
- የተወለደበት/ችበት ቦታ
- የህፃኑ/ኗ ዜግነት
- የህጻኑ/ኗ የአባት ስም እና ዜግነት
- የህጻኑ/ኗ የእናት ስም እና ዜግነት
- ምስክር ወረቀት የተሰጠበት ቀን
- ምስክር ወረቀት የተሰጠበት ቦታ
- አስተያየት
- የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም ስምና ፊርማ፣ ማህተም

### 4.2.2 የሞት ምስክር ወረቀት

- የምዝገባ መለያ ቁጥር
- የመዝገብ ቅጽ ቁጥር
- የሟች ሙሉ ስም
- የሟች ዕድሜ
- የሞተበት/ችበት ቀን
- የሞተበት/ችበት ቦታ
- የሞት ምክንያት
- የምስክር ወረቀት የተሰጠበት ቀን
- ምስክር ወረቀት የተሰጠበት ቦታ
- ዜግነት
- የጋብቻ ሁኔታ
- አስተያየት
- የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም ስምና ፊርማ
- ማህተም

### 4.2.3 የጋብቻ ምስክር ወረቀት

- የምዝገባ መለያ ቁጥር
- የመዝገብ ቅጽ ቁጥር
- የሙሽራውና የሙሽሪት ሙሉ ስም
- የሙሽራውና ሙሽሪት ዕድሜ
- ሙሽራውና ሙሽሪት የተወለዱበት ቀን
- የሙሽራውና የሙሽሪት ዜግነት
- የሙሽራውና የሙሽሪት የቀድሞ የጋብቻ ሁኔታ
- ጋብቻው የተፈፀመበት ቀን
- ጋብቻው የተፈፀመበት ቦታ
- ምስክር ወረቀቱ የተሰጠበት ቀን
- ምስክር ወረቀቱ የተሰጠበት ቦታ
- አስተያየት
- የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም ስምና ፊርማ
- ማህተም

### 4.2.4 የፍቺ ምስክር ወረቀት

- የምዝገባ መለያ ቁጥር
- የመዝገብ ቅጽ ቁጥር
- የባልና የሚስት (የተፋቺዎች) ሙሉ ስም
- የባልና የሚስት ዕድሜ
- ባልና ሚስት የተወለዱበት ቦታ
- የባልና የሚስት ዜግነት
- ፍቺው የተፈፀመበት ቦታ
- ፍቺው የተፈፀመበት ቀን
- የምስክር ወረቀቱ የተሰጠበት ቀን
- ምስክር ወረቀቱ የተሰጠበት ቦታ
- አስተያየት
- የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም ስምና ፊርማ
- ማህተም

## 4.3 የኩነቶች ምስክር ወረቀቶች አዘገጃጀት

አንድ ኩነት ለመመዝገቡ የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች ለግለሰቡ መሰጠት ይገባቸዋል። ይኸውም መረጃ የምስክር ወረቀት ይባላል። መዝጋቢው ከአስመዝጋቢው ባገኘው መረጃ መሠረት ኩነቱን የሚመለከቱ መረጃዎችን በተገቢው የሕዝብ የክብር መዝገብ ውስጥ ካሰፈረ በኋላ የኩነቶች የምስክር ወረቀት ላይ ከሕዝብ የክብር መዝገቡ መረጃዎችን ያወራርሳል።

የኩነቶች የምስክር ወረቀቶች ወጥነት ባለው ሁኔታ በማዕከል የሚዘጋጁ ሊሆኑ ይገባል። መዝጋቢው የምስክር ወረቀቱ የሚጠይቃቸውን መረጃዎች ከመዝገቡ ውስጥ ለቅሞ በሁለት ቅጂ በተነባቢ የእጅ ጽሑፍ ወይም በታይፕ ወይም በኮምፒውተር መዝግቦ ለሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም ለፊርማ ያቀርባል። የምዝገባ ሹሙም ትክክለኛነቱን ካረጋገጠ በኋላ ፊርማውን፣ ቀኑንና የጽ/ቤቱን ማህተም በማስፈር የመረጃውን ህጋዊነት ያረጋግጣል። የኩነቶች ምስክር ወረቀት አንዱ ቅጂ ለባለጉዳዩ ወይም በህጉ ስልጣን ለተሰጠው ወኪል ሲሰጥ ሌላኛው ቅጂ በዘመንና በፊደል ተራ ቅደም ተከተል ተጠርዞ በምዝገባው ጽ/ቤት መዝገብ ቤት ይቀመጣል።

## 4.4 የምስክር ወረቀቶች ለባለጉዳዮች የሚሰጡበት ሥርዓት

የመዝገቡን ጽሑፍ ክፊል የያዘው የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ የሚጠየቀው በጉዳዩ ባለቤት ወይም በወኪሉ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ነው። በዚህን ጊዜ መዝጋቢው የጠያቂዎቹን ማንነት አጣርቶ በጥያቄያቸው መሠረት የምስክር ወረቀቱን አዘጋጅቶና የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹሙን አስፈርሞ በከተማ በ15 ቀናት፣ በገጠር በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለባለጉዳዩ ወይም ለወኪሉ ይሰጣል። ጠያቂዎቹ እንደጉዳዩ ሁኔታ የባለጉዳዩ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመዶች ማለትም ባለቤት፣ አባት፣ እናት፣ እህት፣ ወንድም ወይም ሌላ ሕጋዊ ጠያቂ ሊሆኑ ይችላሉ። መዝጋቢው የምስክር ወረቀቱ ጥያቄ ከምን እንደመነጨና በእርግጥም ምክንያታቸው ትክክለኛ መሆኑንና ሕጋዊ መብት እንዳላቸው አረጋግጦ የምስክር ወረቀቱን ይሰጣል።

## 4.5 የኩነቶች የምስክር ወረቀቶች እርማት አደራረግ

የወሳኝ ኩነቶች የምስክር ወረቀቶች በመዝጋቢው ተመዝግበው በምዝገባ ሹሙ ትክክለኛነታቸው ተረጋግጦ፣ ተፈርሞና የጽ/ቤቱ ማህተም ተደርጎባቸው ለባለጉዳዩ ወይም ለወኪሉ ከተሰጡ በኋላ እርማት ወይም ማስተካከያ ሊደረግላቸው የሚችለው በህግ ሥልጣን በተሰጠው ባለሥልጣን ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ ብቻ ነው። ይህም የሚደረገው የምስክር ወረቀቶቹን ህጋዊነት ለመጠበቅና ከጥንቃቄ ጉድለት ሊመጡ የሚችሉ ሕገ ወጥ አሠራሮችን ለመከላከል ነው። በምስክር ወረቀቱ ላይ እርምት ወይም ማስተካከያ እንዲደረግ በጉዳዩ ባለቤት ወይም በወኪሉ ወይም በወራሾቹ ወይም በሌሎች የግለሰቡ ሕጋዊ የዘር ሐረግ ተዋረዶች ሊጠየቅ ይችላል።

ከላይ የተጠቀሰው አባባል እንደተጠበቀ ሆኖ መዝጋቢው የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም በህግ ስልጣን የተሰጠውን የበላይ አካል መመሪያ ሳይጠብቅ ከዚህ የሚከተሉትን ጥቃቅን (Clerical) እርማቶች በምስክር ወረቀቱ ላይ ሊያደርግ ይችላል።

1ኛ/ ከመዝገብ ወደ ምስክር ወረቀቱ ጽሑፍ ሲገለበጥ የተፈጸመ የፊደል ግድፈት ከሆነ፣

2ኛ/ በመዝገቡ ጽሑፍ ላይ እርማት ተደርጎ ከሆነና የምስክር ወረቀቱ በዚያ መነሻነት መታረም ካለበት ናቸው።

ከዚህ ያለፉ እርማቶች ወይም ማስተካከያዎች ሊደረጉ የሚችሉት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም በህግ ስልጣን በተሰጠው የበላይ ኃላፊ ውሳኔ ብቻ ነው። የምስክር ወረቀቶቹን ጥራትና ንጽሕና ለመጠበቅ ሲባል እርማት ወይም ማስተካከያ ከተደረገ በኋላ ቀደም ብሎ የተሰጠው

መዝጋቢው በምስክር ወረቀቱ ላይ እርማት ለማድረግ ወይም ለማስተካከል የተገደደበትን ምክንያት ጽፎ ከቀሪው ጋር አያይዞ ማስቀመጥ አለበት።

## 4.6 የኩነቶች የምስክር ወረቀቶች አያያዝና አቀማመጥ

የወሳኝ ኩነት የምስክር ወረቀቶች ሕጉ በሚያዘው የጊዜ ገደብ ውስጥ መመዝገባቸውን ወይም አለመመዝገባቸውን (የዘገዩ ምዝገባዎች) በሚገልጹ (በሚያሳዩ) ሕጋዊ አሠራር ሊዘጋጁ ይችላሉ። ይኸም ሲሆን በህጉ በተሰጠው የምዝገባ የጊዜ ገደብ ውስጥ ሳይመዘገቡ በመቅረታቸው በተለየ አኳኋን የተዘጋጁ የምስክር ወረቀቶች የተዘጋጁላቸው ግለሰቦች በህጉ በተገለፀው የአሠራር መመሪያ መሠረት በሂደት የምስክር ወረቀቱን ደረጃ ማስቀየር ይጠበቅባቸዋል። በአጠቃላይ የምስክር ወረቀቶች በግለሰቡና በመንግስት ሥር በከፍተኛ ጥንቃቄ መያዝና መጠበቅ አለባቸው። የእነዚህ ህጋዊ ሰነዶች ጥቅም ለግሰሰቡ በህይወት ዘመን በሙሉ ከማገልገል አልፊው ለተከታይ ትውልዶች የሚጠቅሙ በመሆናቸው የሚታተሙበት ወረቀት ጥራት ያለውና ለረጅም ጊዜ ሳይበላሽ የሚቆይ ሆኖ የተዘጋጀ ሊሆን ይገባል። ስለሆነም የሚጻፍበትም ቀለም በሂደት የማይደበዝዝና የማይለቅ መሆኑ መረጋገጥ አለበት።

የማንኛውም ኩነት የምስክር ወረቀት በሁለት ቅጂ ይዘጋጃል። አንደኛው ቅጂ ለባለጉዳዩ ወይም ለወኪሉ ይሰጣል። ሁለተኛው ቅጂ በቀበሌው የምዝገባ የሥራ ክፍል በመዝገብ ቤት በፊደል እና ዘመን ቅደም ተከተል ተጠርዞ ይቀመጣል።

የምስክር ወረቀቶቹ ከአያያዝ ጉድለትና በእርጅና ከጥቅም ውጪ እንዳይሆኑ ተገቢው ጥንቃቄ ሊደረግላቸው ይገባል። ወረቀቶቹ በእርጥበት፣ በውሃ፣ በእሳት፣ በቀበኛ እንስሳት፣ በአይጦች፣ በበራሪ ነፍሳት፣ ... ወዘተ እንዳይበላሹ የሚቀመጡበት ቦታ በሥርዓት የተሰናዳና የተያዘ መሆን አለበት። የቀለም መልቀቅን፣ የጽሑፍ መጥፋትንና መደብዘዝን፣ ማርጀትንና ከጥቅም ውጭ መሆንን ለመከላከል የመዝገብ ቤቱን የብርሃንና የአየር ሁኔታ በተመለከተ በቂ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። በተጨማሪም ጉዳዩ በማይመለከታቸው ሰዎች እጅ ገብተው ሕገ ወጥ ድርጊት እንዳይፈጸምባቸው ከስርቆት መጠበቅ አለባቸው።

| የመዝገብ ቁጥር | |
|---|---|
| የቅጽ ቁጥር | |

# በኢትዮጵያ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ
# የልደት የሕዝብ የክብር መዝገብ ቅጽ

## ክፍል 1 የምዝገባ አካባቢ መለያ

| 1.1 የክልል ስም | 1.2 የዞን ስም | 1.3 የወረዳ ስም | 1.4 የከተማ ስም | 1.5 የከተማ ቀበሌ ስም/ቁጥር | 1.6 የገጠር ቀበሌ ስም/ ቁጥር | 1.7 የምዝገባ ጽ/ቤት የቤት ቁጥር - በከተማ | 1.8 የምዝገባ ጽ/ቤት የሚገኝበት የመንደር ልዩ ስም - በገጠር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | |

## ክፍል 2 ህፃኑን/ኗን የሚመለከት

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.1 የህፃኑ/ኗ ሙሉ ስም | | | | 2.5 ህፃኑ/ኗ የተወለደበት/ችበት ቦታ | ክልል | ዞን | ወረዳ | 2.7 የልደት ምዝገባ መለያ ቁጥር | |
| 2.2 የህፃኑ/ኗ ፆታ | | | | | | | | 2.8 ልደቱ የተመዘገበበት ቀን | |
| 2.3 ህፃኑ/ኗ የተወለደበት/ችበት ቀን | ቀን | ወር | ዓ.ም. | | ከተማ | ቀበሌ (ከተማ/ገጠር) | የቤት ቁጥር | 2.9 የልደቱ አይነት | |
| | | | | | | | | 2.10 በልደቱ ጊዜ የህፃኑ/ኗ ክብደት (በግራም) | |
| 2.4 ህፃኑ/ኗ የተወለደበት/ችበት ሰፍራ (ተቋም) | | | | 2.6 በልደት ጊዜ የተደረገ እርዳታ | | | | 2.11 ልደቱ የተከሰተው በጋብቻ ውስጥ ወይስ ከጋብቻ ውጪ | |

## ክፍል 3 የህፃኑን/ኗን እናት ባህርያት የሚመለከት

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3.1 የእናት ስም | | 3.4 የእናት መደበኛ መኖሪያ ቦታ | ክልል | ዞን | ወረዳ | 3.5 ሐይማኖት | | የወላጅ እናት ፊርማ |
| 3.2 የእናት እድሜ | | | | | | 3.6 ዜግነት | | |
| | | | ከተማ | ቀበሌ (ከተማ/ገጠር) | የቤት ቁጥር | 3.7 ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ | | |
| 3.3 የእናት ብሄረሰብ | | | | | | 3.8 የጋብቻ ሁኔታ | | |

## ክፍል 4 የህፃኑ/ኗ አባት ባህርያት

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4.1 የአባት ስም | | 4.4 የአባት መደበኛ መኖሪያ ቦታ | ክልል | ዞን | ወረዳ | 4.5 ሐይማኖት | | የወላጅ አባት ፊርማ |
| 4.2 የአባት እድሜ | | | | | | 4.6 ዜግነት | | |
| | | | ከተማ | ቀበሌ (ከተማ/ገጠር) | የቤት ቁጥር | 4.7 ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ | | |
| 4.3 የአባት ብሄረሰብ | | | | | | 4.8 የጋብቻ ሁኔታ | | |

## ክፍል 5 አስመዝጋቢውን የሚመለከት

| 5.1 የአስመዝጋቢ ሙሉ ስም | 5.2 አስመዝጋቢው ለህፃኑ/ኗ ያለው የዝምድና ዓይነት | 5.3 የአስመዝጋቢው መደበኛ መኖሪያ ቦታ | | | | | | 5.4 የአስመዝጋቢው ፊርማና ቀን | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ክልል | ዞን | ወረዳ | ከተማ | ቀበሌ | የቤት ቁጥር | ፊርማ | ቀን | ወር | ዓ.ም |
| | | | | | | | | | | | |

## ክፍል 6 ለልደት ማረጋገጫ የቀረበ ማስረጃ

6.1 የሐኪም የልደት የምስክር ወረቀት

| 6.1.1 የመዝገብ ቁጥር | | | 6.1.2 መረጃውን የሰጠው ተቋም ስም | |
|---|---|---|---|---|

6.2 የአይን ምስክሮችን የሚመለከት

| 6.2.1 የአይን ምስክሮች ሙሉ ስም | | 6.2.2 የአይን ምስክሮች መደበኛ መኖሪያ ቦታ | | | | | | 6.2.3 የአይን ምስክሮች ፊርማና ቀን | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ክልል | ዞን | ወረዳ | ከተማ | ቀበሌ | የቤት ቁጥር | ፊርማ | ቀን | ወር | ዓ.ም |
| 1ኛ | | | | | | | | | | | |
| 2ኛ | | | | | | | | | | | |
| 3ኛ | | | | | | | | | | | |

## ክፍል 7 አስተያየት

አስተያየት

## ክፍል 8 የመዝጋቢ ሙሉ ስም፣ ፊርማና ቀን

| 8.1 የመዝጋቢ ሙሉ ስም | 8.2 የመዝጋቢ ፊርማና ቀን | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ፊርማ | ቀን | ወር | ዓ.ም |

| የመዝጋቢ መለያ ቁጥር |
|---|
| |

## ለስታቲስቲክስ ሥራ ብቻ (በቢሮ የሚሞላ)

| 1.1 ክልል | 1.2 ዞን | 1.3 ወረዳ |
|---|---|---|
| | | |
| 1.4 ከተማ | 1.5 ከተማ ቀበሌ | 1.6 ገጠር ቀበሌ |
| | | |

| 2.2 ፆታ | 2.3 የትውልድ ቀን | | | 2.4 የትውልድ ሥፍራ (ተቋም) | 2.6 ዕርዳታ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቀን | ወር | ዓመት | | |

| 2.5 የትውልድ ቦታ | | |
|---|---|---|
| ክልል | ዞን | ወረዳ |
| | | |
| ከተማ | ቀበሌ (ከተማ/ገጠር) | |
| | | |

| 2.7 የምዝገባ መለያ ቁጥር | 2.8 የተመዘገበበት ቀን | | |
|---|---|---|---|
| | ቀን | ወር | ዓመት |

| 2.9 የልደቱ አይነት | 2.10 ክብደት (በግራም) | 2.11 በጋብቻ ወይስ ከጋብቻ ውጪ |
|---|---|---|
| | | |

| 3.2 ዕድሜ | 3.3 ብሄረሰብ | 3.5 ሐይማኖት | 3.6 ዜግነት | 3.7 የትምህርት ደረጃ | 3.8 የጋብቻ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |

| 3.4 የእናት መደበኛ መኖሪያ ቦታ | | |
|---|---|---|
| ክልል | ዞን | ወረዳ |
| | | |
| ከተማ | ቀበሌ (ከተማ/ገጠር) | |
| | | |

| 4.2 ዕድሜ | 4.3 ብሄረሰብ | 4.5 ሐይማኖት | 4.6 ዜግነት | 4.7 የትምህርት ደረጃ | 4.8 የጋብቻ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |

| 4.4 የአባት መደበኛ መኖሪያ ቦታ | | |
|---|---|---|
| ክልል | ዞን | ወረዳ |
| | | |
| ከተማ | ቀበሌ (ከተማ/ገጠር) | |
| | | |

# በኢትዮጵያ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ
# የሞት የሕዝብ የክብር መዝገብ ቅጽ

| የመዝገብ ቁጥር | |
|---|---|
| የቅጽ ቁጥር | |

## ክፍል 1 የምዝገባ አካባቢ መለያ

| 1.1 የክልል ስም | 1.2 የዞን ስም | 1.3 የወረዳ ስም | 1.4 የከተማ ስም | 1.5 የከተማ ቀበሌ ስም/ቁጥር | 1.6 የገጠር ቀበሌ ስም/ቁጥር | 1.7 የምዝገባ ጽ/ቤት የቤት ቁጥር - በከተማ | 1.8 የምዝገባ ጽ/ቤት የሚገኝበት የመንደር ልዩ ስም - በገጠር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | |

## ክፍል 2 ሟችን በሚመለከት

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.1 የሟች ሙሉ ስም | | 2.7 የሟች መደበኛ መኖሪያ ቦታ | ክልል | ዞን | ወረዳ | 2.11 የሞት ምክንያት | : | | |
| 2.2 የሟች ዕድሜ | | | | | | 2.12 ሟች የሞተበት/ችበት ቀን | ቀን | ወር | ዓ.ም. |
| 2.3 የሟች ፆታ | | | ከተማ | ቀበሌ (ከተማ/ገጠር) | የቤት ቁጥር | | | | |
| 2.4 የሟች ብሔረሰብ | | | | | | 2.13 ሟች የሞተበት/ችበት ሥፍራ (ተቋም) | | | |
| 2.5 የሟች ሐይማኖት | | 2.8 የሟች ከፍተኛ የትምህርት ሁኔታ | | | | 2.14 ሞቱ የተመዘገበበት ቀን | | | |
| 2.6 የሟች ዜግነት | | 2.9 የሟች የጋብቻ ሁኔታ | | | | 2.15 የሞት ምዝገባ መለያ ቁጥር | | | |
| | | 2.10 የሟች መደበኛ የስራ ዓይነት | | | | 2.16 በሞት ጊዜ የተደረገ ዕርዳታ | | | |

## ክፍል 3 አስመዝጋቢን የሚመለከት

| 3.1 የአስመዝጋቢ ሙሉ ስም | 3.2 አስመዝጋቢ ለሟች ያለው የዝምድና ዓይነት | 3.3 የአስመዝጋቢ መደበኛ መኖሪያ ቦታ | | | | | | 3.4 የአስመዝጋቢ ፊርማና ቀን | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ክልል | ዞን | ወረዳ | ከተማ | ቀበሌ | የቤት ቁጥር | ፊርማ | ቀን | ወር | ዓ.ም |
| | | | | | | | | | | | |

## ክፍል 4 ለሞት ማረጋገጫ የቀረበ ማስረጃ

4.1 የሐኪም የሞት የሚዲካል የምስክር ወረቀት

| 4.1.1 የመዝገብ ቁጥር | | | 4.1.2 መረጃውን የሰጠው ተቋም ስም | |
|---|---|---|---|---|

4.2 የአይን ምስክሮችን የሚመለከት

| ተራ ቁጥር | 4.2.1 የአይን ምስክሮች ሙሉ ስም | 4.2.2 የአይን ምስክሮች መደበኛ መኖሪያ ቦታ | | | | | | 4.2.3 የአይን ምስክሮች ፊርማና ቀን | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ክልል | ዞን | ወረዳ | ከተማ | ቀበሌ | የቤት ቁጥር | ፊርማ | ቀን | ወር | ዓ.ም |
| 1ኛ | | | | | | | | | | | |
| 2ኛ | | | | | | | | | | | |
| 3ኛ | | | | | | | | | | | |

## ክፍል 5 አስተያየት

አስተያየት

## ክፍል 6 የመዝጋቢ ሙሉ ስም፣ ፊርማና ቀን

| 6.1 የመዝጋቢ ሙሉ ስም | 6.2 የመዝጋቢ ፊርማና ቀን | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ፊርማ | ቀን | ወር | ዓ.ም |
| | | | | |

የመዝጋቢ መለያ ቁጥር

## ለስታቲስቲክስ ሥራ ብቻ (በቢሮ የሚሞላ)

| 1.1 ክልል | 1.2 ዞን | 1.3 ወረዳ |
|---|---|---|
| | | |
| 1.4 ከተማ | 1.5 ከተማ ቀበሌ | 1.6 ገጠር ቀበሌ |
| | | |

| 2.2 ዕድሜ | 2.3 ፆታ | 2.4 ብሄረሰብ | 2.5 ሐይማኖት | 2.6 ዜግነት | 2.8 የትምህርት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |

| 2.7 መደበኛ መኖሪያ ቦታ | | |
|---|---|---|
| ክልል | ዞን | ወረዳ |
| | | |
| ከተማ | ቀበሌ (ከተማ/ገጠር) | |
| | | |

| 2.9 የጋብቻ ሁኔታ | 2.10 የሥራ ዓይነት | 2.11 የሞት ምክንያት |
|---|---|---|
| | | |

| 2.12 የሞተበት ቀን | | | 2.13 የሞት ሥፍራ (ተቋም) |
|---|---|---|---|
| ቀን | ወር | ዓመት | |
| | | | |

| 2.14 የተመዘገበበት ቀን | | | 2.15 የምዝገባ መለያ ቁጥር | 2.16 ዕርዳታ |
|---|---|---|---|---|
| ቀን | ወር | ዓመት | | |
| | | | | |

| የመዝገብ ቁጥር | |
|---|---|
| የቅጽ ቁጥር | |

# በኢትዮጵያ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ
# የጋብቻ የሕዝብ የክብር መዝገብ ቅጽ

## ክፍል 1 የምዝገባ አካባቢ መለያ

| 1.1 የክልል ስም | 1.2 የዞን ስም | 1.3 የወረዳ ስም | 1.3 የከተማ ስም | 1.4 የከተማ ቀበሌ ስም/ቁጥር | 1.5 የገጠር ቀበሌ ስም ቁጥር | 1.7 የምዝገባ ጽ/ቤት የቤት ቁጥር - በከተማ | 1.8 የምዝገባ ጽ/ቤት የሚገኝበት የመንደር ልዩ ስም - በገጠር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | |

## ክፍል 2 ጋብቻውን በሚመለከት

| | ቀን | ወር | ዓ.ም. | | ክልል | ዞን | ወረዳ | | ቀን | ወር | ዓ.ም. |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.1 ጋብቻው የተፈፀመበት ቀን | | | | 2.3 ጋብቻው የተፈፀመበት ቦታ | | | | 2.4 ጋብቻው የተመዘገበበት ቀን | | | |
| | | | | | ከተማ | ቀበሌ (ከተማ/ገጠር | የቤት ቁጥር | | | | |
| 2.2 የተፈፀመው የጋብቻ አይነት | | | | | | | | 2.5 የጋብቻ ምዝገባ መለያ ቁጥር | | | |

## ክፍል 3 ሙሽራውን በሚመለከት

| | | | | ክልል | ዞን | ወረዳ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3.1 የሙሽራው ሙሉ ስም | | | 3.5 የሙሽራው መደበኛ መኖሪያ ቦታ | | | | 3.6 የሙሽራው ዜግነት | |
| 3.2 የሙሽራው ዕድሜ | | | | | | | 3.7 የሙሽራው ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ | |
| 3.3 የሙሽራው ብሄረሰብ | | | | ከተማ | ቀበሌ (ከተማ/ገጠር) | የቤት ቁጥር | 3.8 የሙሽራው የቀድሞ የጋብቻ ሁኔታ | |
| 3.4 የሙሽራው ሐይማኖት | | | | | | | | |

## ክፍል 4 ሙሽራይቱን በተመለከት

| | | | | ክልል | ዞን | ወረዳ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4.1 የሙሽራይቱ ሙሉ ስም | | | 4.5 የሙሽራይቱ መደበኛ መኖሪያ ቦታ | | | | 4.6 የሙሽራይቱ ዜግነት | |
| 4.2 የሙሽራይቱ ዕድሜ | | | | | | | 4.7 የሙሽራይቱ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ | |
| 4.3 የሙሽራይቱ ብሄረሰብ | | | | ከተማ | ቀበሌ (ከተማ/ገጠር) | የቤት ቁጥር | 4.8 የሙሽራይቱ የቀድሞ የጋብቻ ሁኔታ | |
| 4.4 የሙሽራይቱ ሐይማኖት | | | | | | | | |

## ክፍል 5 ለጋብቻው ማረጋገጫ የቀረበ ማስረጃ

5.1 የጋብቻ የምስክር ወረቀት (ውል)

| 5.1 የመዝገብ ቁጥር | | | 5.1.2 መረጃውን የሰጠው ተቋም/ አካል ስም | |
|---|---|---|---|---|

5.2 የአይን ምስክሮችን የሚመለከት

| ተራ ቁጥር | 5.2.1 የአይን ምስክሮች ሙሉ ስም | 5.2.2 የአይን ምስክሮች መደበኛ መኖሪያ ቦታ | | | | | | 5.2.3 የአይን ምስክሮች ፊርማና ቀን | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ክልል | ዞን | ወረዳ | ከተማ | ቀበሌ (ከተማ/ገጠር) | የቤት ቁጥር | ፊርማ | ቀን | ወር | ዓ.ም |
| 1ኛ | | | | | | | | | | | |
| 2ኛ | | | | | | | | | | | |
| 3ኛ | | | | | | | | | | | |

## ክፍል 6 አስተያየት

አስተያየት

## ክፍል 7 የሙሽራውና የሙሽራይቱ (አስመዝጋቢዎች) ስም፣ ፊርማና ቀን

| 7.1 የሙሽራው ሙሉ ስም | ፊርማ | ቀን | ወር | ዓ.ም. | 7.2 የሙሽሪት ሙሉ ስም | ፊርማ | ቀን | ወር | ዓ.ም. |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | |

## ክፍል 8 የመዝጋቢ ስም፣ ፊርማና ቀን

| 8.1 የመዝጋቢ ሙሉ ስም | 8.2 የመዝጋቢ ፊርማና ቀን | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ፊርማ | ቀን | ወር | ዓ.ም |
| | | | | |

| የመዝጋቢ መለያ ቁጥር |
|---|
| |

## ለስታቲስቲክስ ሥራ ብቻ (በቢሮ የሚሞላ)

| 1.1 ክልል | 1.2 ዞን | 1.3 ወረዳ |
|---|---|---|
| | | |
| 1.4 ከተማ | 1.5 ከተማ ቀበሌ | 1.6 ገጠር ቀበሌ |
| | | |

| 2.1 የተፈጸመበት ቀን | | | 2.2 የጋብቻው ዓይነት |
|---|---|---|---|
| ቀን | ወር | ዓመት | |
| | | | |

| 2.3 የተፈጸመበት ቦታ | | |
|---|---|---|
| ክልል | ዞን | ወረዳ |
| | | |
| ከተማ | ቀበሌ (ከተማ/ገጠር) | |
| | | |

| 2.4 የተመዘገበበት ቀን | | | 2.5 የምዝገባ መለያ ቁጥር |
|---|---|---|---|
| ቀን | ወር | ዓመት | |
| | | | |

| 3.2 ዕድሜ | 3.3 ብሄረሰብ | 3.4 ሐይማኖት | 3.6 ዜግነት | 3.7 የትምህርት ደረጃ | 3.8 የጋብቻ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |

| 3.5 መደበኛ መኖሪያ ቦታ | | |
|---|---|---|
| ክልል | ዞን | ወረዳ |
| | | |
| ከተማ | ቀበሌ (ከተማ/ገጠር) | |
| | | |

| 4.2 ዕድሜ | 4.3 ብሄረሰብ | 4.4 ሐይማኖት | 4.6 ዜግነት | 4.7 የትምህርት ደረጃ | 4.8 የጋብቻ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |

| 4.5 መደበኛ መኖሪያ ቦታ | | |
|---|---|---|
| ክልል | ዞን | ወረዳ |
| | | |
| ከተማ | ቀበሌ (ከተማ/ገጠር) | |
| | | |

| የመዝገብ ቁጥር | |
|---|---|
| የቅጽ ቁጥር | |

# በኢትዮጵያ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ
# የፍቺ የሕዝብ የክብር መዝገብ ቅጽ

## ክፍል 1 የምዝገባ አካባቢ መለያ

| 1.1 የክልል ስም | 1.2 የዞን ስም | 1.3 የወረዳ ስም | 1.3 የከተማ ስም | 1.4 የከተማ ቀበሌ ስም/ቁጥር | 1.5 የገጠር ቀበሌ ስም ቁጥር | 1.7 የምዝገባ ጽ/ቤት የቤት ቁጥር- በከተማ | 1.8 የምዝገባ ጽ/ቤት የሚገኝበት የመንደር ልዩ ስም - በገጠር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | |

## ክፍል 2 ፍቺውን በሚመለከት

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.1 ፍቺው የተፈፀመበት ቀን | ቀን | ወር | ዓ.ም. | 2.3 ፍቺው የተፈፀመበት ቦታ | ክልል | ዞን | ወረዳ | 2.4 የፍቺው ዓይነት | |
| | | | | | | | | 2.5 የፍቺ ምዝገባ መለያ ቁጥር | |
| 2.2 ፍቺው የተመዘገበበት ቀን | ቀን | ወር | ዓ.ም. | | ከተማ | ቀበሌ (ከተማ/ገጠር) | የቤት ቁጥር | 2.6 የፍቺው ምክንያት | |
| | | | | | | | | 2.7 ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች | |
| | | | | | | | | 2.8 ጋብቻው የቆየበት ጊዜ | |

## ክፍል 3 ባልን በሚመለከት

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3.1 የባል ሙሉ ስም | | 3.5 የባል መደበኛ መኖሪያ ቦታ | ክልል | ዞን | ወረዳ | 3.6 የባል ዜግነት | |
| 3.2 የባል ዕድሜ | | | | | | 3.7 የባል ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ | |
| 3.3 የባል ብሔረሰብ | | | ከተማ | ቀበሌ (ከተማ/ገጠር) | የቤት ቁጥር | 3.8 የፍቺ ብዛት | |
| 3.4 የባል ሐይማኖት | | | | | | | |

## ክፍል 4 ሚስትን በሚመለከት

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4.1 የሚስት ሙሉ ስም | | 4.5 የሚስት መደበኛ መኖሪያ ቦታ | ክልል | ዞን | ወረዳ | 4.6 የሚስት ዜግነት | |
| 4.2 የሚስት ዕድሜ | | | | | | 4.7 የሚስት ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ | |
| 4.3 የሚስት ብሔረሰብ | | | ከተማ | ቀበሌ (ከተማ/ገጠር) | የቤት ቁጥር | 4.8 የፍቺ ብዛት | |
| 4.4 የሚስት ሐይማኖት | | | | | | | |

## ክፍል 5 ለፍቺው ማረጋገጫ የቀረበ ማስረጃ

5.1 የፍቺው የፍርድ ቤት ትዕዛዝ የምስክር ወረቀት (ው-ል)

| 5.1.1 የመዝገብ ቁጥር | | | 5.1.2 መረጃውን የሰጠው ተቋም/ አካል ስም | |
|---|---|---|---|---|

5.2 የአይን ምስክሮችን የሚመለከት

| ተራ ቁጥር | 5.2.1 የአይን ምስክሮች ሙሉ ስም | 5.2.2 የአይን ምስክሮች መደበኛ መኖሪያ ቦታ: ክልል | ዞን | ወረዳ | ከተማ | ቀበሌ (ከተማ/ገጠር) | የቤት ቁጥር | 5.2.3 የአይን ምስክሮች ፊርማና ቀን: ፊርማ | ቀን | ወር | ዓ.ም |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1ኛ | | | | | | | | | | | |
| 2ኛ | | | | | | | | | | | |
| 3ኛ | | | | | | | | | | | |

## ክፍል 6 አስተያየት

አስተያየት

## ክፍል 7 የባልና የሚስት (የአስመዝጋቢዎች) ስም፣ ፊርማና ቀን

| 7.1 የባል ሙሉ ስም | ፊርማ | ቀን | ወር | ዓ.ም. | 7.2 የሚስት ሙሉ ስም | ፊርማ | ቀን | ወር | ዓ.ም. |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | |

## ክፍል 8 የመዝጋቢ ሙሉ ስም፣ ፊርማና ቀን

| 8.1 የመዝጋቢ ሙሉ ስም | 8.2 የመዝጋቢ ፊርማና ቀን: ፊርማ | ቀን | ወር | ዓ.ም. |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |

| የመዝጋቢ መለያ ቁጥር |
|---|
| |

## ለስታቲስቲክስ ሥራ ብቻ (በቢሮ የሚሞላ)

| 1.1 ክልል | 1.2 ዞን | 1.3 ወረዳ |
|---|---|---|
| | | |
| 1.4 ከተማ | 1.5 ከተማ ቀበሌ | 1.6 ገጠር ቀበሌ |
| | | |

| 2.1 የተፈጸመበት ቀን | | | 2.2 የተመዘገበበት ቀን | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ቀን | ወር | ዓመት | ቀን | ወር | ዓመት |
| | | | | | |

| 2.3 የተፈጸመበት ቦታ | | |
|---|---|---|
| ክልል | ዞን | ወረዳ |
| | | |
| ከተማ | ቀበሌ (ከተማ/ገጠር) | |
| | | |

| 2.4 ዓይነት | 2.5 የምዝገባ መለያ ቁጥር | 2.6 ምክንያት | 2.7 ልጆች | 2.8 የቆየበት ጊዜ |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |

| 3.2 ዕድሜ | 3.3 ብሔረሰብ | 3.4 ሐይማኖት | 3.6 ዜግነት | 3.7 የትምህርት ደረጃ | 3.8 የፍቺ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |

| 3.5 መደበኛ መኖሪያ ቦታ | | |
|---|---|---|
| ክልል | ዞን | ወረዳ |
| | | |
| ከተማ | ቀበሌ (ከተማ/ገጠር) | |
| | | |

| 4.2 ዕድሜ | 4.3 ብሔረሰብ | 4.4 ሐይማኖት | 4.6 ዜግነት | 4.7 የትምህርት ደረጃ | 4.8 የፍቺ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |

| 4.5 መደበኛ መኖሪያ ቦታ | | |
|---|---|---|
| ክልል | ዞን | ወረዳ |
| | | |
| ከተማ | ቀበሌ (ከተማ/ገጠር) | |
| | | |

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ

## የልደት ምስክር ወረቀት
## Birth Certificate

*የምዝገባ መለያ ቁጥር* ____________ *የመዝገብ ቁጥር* ____________
*Registration ID* *Registration No*

የህፃኑ/ኗ ስም ____________
Name of Child ____________
የህፃኑ/ኗ ፆታ ____________
Sex of Child ____________
የተወለደበት/ችበት ቀን ____________
Date of Birth ____________
የተወለደበት/ችበት ቦታ ____________
Place of Birth ____________
የህፃኑ/ኗ ዜግነት ____________
Citizenship ____________
የአባት ስም ____________ የአባት ዜግነት ____________
Name of Father ____________ Citizenship ____________
የእናት ስም ____________ የእናት ዜግነት ____________
Name of Mother ____________ Citizenship ____________

ምስክር ወረቀት የተሰጠበት ቀን ____________
Date of Issue ____________
ምስክር ወረቀት የተሰጠበት ቦታ ____________
Place of Issue ____________

ስም ፊ ር ማ
Name Signature

የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም ____________
Registrar ____________ ____________
ማህተም

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ**

**የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ**

## የሞት ምስክር ወረቀት
## Death Certificate

*የምዝገባ መለያ ቁጥር* ______________ *የመዝገብ ቁጥር* ______________
*Registration ID* *Registration No*

የሟች ስም
Name of Deceased ______________

የሟች ፆታ
Sex of deceased ______________

የሟች ዕድሜ
Age of Deceased ______________

ዜግነት
Citizenship ______________

የጋብቻ ሁኔታ
Marital status ______________

የሞተበት ቀን
Date of Death ______________

የሞተበት ቦታ
Death of Place ______________

የሞተበት ምክንያት
Cause of Death ______________

ምስክር ወረቀት የተሰጠበት ቀን
Date of Issue ______________

ምስክር ወረቀት የተሰጠበት ቦታ
Place of Issue ______________

| | ስም<br>Name | ፊ ር ማ<br>Signature |
|---|---|---|
| የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም<br>Registrar | ______________ | ______ |

ማኅተም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ

ፎቶ

# የጋብቻ ምስክር ወረቀት
## Marriage Certificate

ፎቶ

*የምዝገባ መለያ ቁጥር* ____________ *Registration ID*

*የመዝገብ ቁጥር* ____________ *Registration No*

የሙሽራው ስም ____________

Name of Groom ____________

የሙሽራው ዕድሜ ____________

Age of Groom ____________

ሙሽራው የተወለደበት ቦታ ____________

Place of Birth ____________

የሙሽራው ዜግነት ____________

Citizenship ____________

የቀድሞ የጋብቻ ሁኔታ ____________

Previous Marital status ____________

የሙሽሪት ስም ____________

Name of Bride ____________

የሙሽሪት ዕድሜ ____________

Age of Bride ____________

ሙሽሪት የተወለደችበት ቦታ ____________

Place of Birth ____________

የሙሽሪቷ ዜግነት ____________

Citizenship ____________

የቀድሞ የጋብቻ ሁኔታ ____________

Previous Marital status ____________

ጋብቻው የተፈጸመበት ቀን ____________

Date of Marriage ____________

ጋብቻው የተፈፀመበት ቦታ ____________

Place of Marriage ____________

ምስክር ወረቀት የተሰጠበት ቀን ____________

Date of Issue ____________

ምስክር ወረቀት የተሰጠበት ቦታ ____________

Place of Issue ____________

| | ስም Name | ፊርማ Signature |
|---|---|---|
| የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም Registrar | ____________ | ____________ |

ማህተም

## ኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ

# የፍቺ ምስክር ወረቀት
# Divorce Certificate

*የምዝገባ መለያ ቁጥር* ________________
*Registration ID*

*የመዝገብ ቁጥር* ________________
*Registration No*

የባል ስም ________________
Name of Husband ________________
የባል ዕድሜ ________________
Age of Husband ________________
የተወለደበት ቦታ ________________
Place of Birth ________________
ዜግነት ________________
Citizenship ________________
ፍቺው የተፈፀመበት ቦታ ________________
Place of Divorce ________________
ፍቺው የተፈፀመበት ቀን ________________
Date of Divorce ________________
ምስክር ወረቀት የተሰጠበት ቀን ________________
Date of Issue ________________
ምስክር ወረቀት የተሰጠበት ቦታ ________________
Place of Issue ________________

የሚስት ስም ________________
Name of Wife ________________
የሚስት ዕድሜ ________________
Age of Wife ________________
ሚስት የተወለደችበት ቦታ ________________
Place of Birth ________________
የሚስት ዜግነት ________________
Citizenship ________________

| | ስም<br>Name | ፊርማ<br>Signature |
|---|---|---|
| የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም<br>Registrar | ________________<br>________________ | ________________ |

ማህተም